# አዲስ ዘመን

ኢፕድ

ዓርብ

81ኛ ዓመት ቁጥር 329 ሐምሌ 29 ቀን 2014 ዓ.ም ዋጋ 10:00

ብዕራችን ለኢትዮጵያ ህዳሴ ይተጋል!



ደርባ ሚድሮክ ሲሚንቶ ኃ/የተ/የግል ማህበር



በልዩ የደርባ ሲሚንቶ መስመር 8688 ወይም
- 0111 26 26 27 - 0922 11 53 24/26
- 0111 26 26 28 - 0922 72 74 48/49
- 0111 26 26 29 - 0922 72 38 70
- 0111 26 26 30 - 0922 72 38 72
ፋክስ፡- 0111 26 23 45 እና 0111 26 23 18
ይዘዙን
ደረጃቸውን ጠብቀን የምናመርታቸውን ጥራት ያላቸው የሲሚንቶ ምርቶች ቤትዎ ወይም ፕሮጀክትዎ ደጃፍ ላይ ያለውጣ ውረድ በደርባ ትራንስፖርት ኃ.የተ.የግ.ማ አማካይነት እናቀርባለን።

ነገን ዛሬ እንሥራ


## “ኢትዮጵያ የተለያዩ ሃይማኖቶችን በውዴታ መቀበሏ ለአንድነቷና ለጥንካሬዋ አንዱ ምስጢር ነው”

-ፕሬዚዳንት ሣህለወርቅ ዘውዴ

ፋንታነሽ ክንዴ



አዲስ አበባ፡- ኢትዮጵያ የተለያዩ ሃይማኖቶችን በግዴታ ሳይሆን በውዴታ መቀበሏ ለአንድነቷና ለጥንካሬዋ አንዱ ምስጢር መሆኑን የኢፌዴሪ ፕሬዚዳንት ሣህለወርቅ ዘውዴ ገለጹ፡፡

ፕሬዚዳንት ሣህለወርቅ ዘውዴ በኢትዮጵያ የሃይማኖት ተቋማት ጉባኤ 14ኛ መደበኛ ጠቅላላ ጉባኤ ላይ ትናንት ተገኝተው ባስተላለፉት መልዕክት እንዳሉት፤ ከ90 በመቶ በላይ የሚሆነው የኢትዮጵያ ሕዝብ አማኝ ነው፡፡ ኢትዮጵያ የተለያዩ ሃይማኖቶችን በግዴታ ሳይሆን በውዴታ መቀበሏም ለአንድነቷና ለጥንካሬዋ አንዱ ምስጢር ነው፡፡

በኢትዮጵያ ያሉ የሃይማኖት ተቋማት ብዙ ክፍለ ዘመን ያስቆጠሩ እና አኩሪ ታሪክ ያላቸው መሆናቸውን የጠቀሱት ፕሬዚዳንቷ፤ የሃይማኖት አባቶች ተሰሚነት ከማንም በላይ እጅግ ከፍ ያለ ነው። በመሆኑም ያላቸውን ተቀባይነት ተጠቅመው ለምዕመናን ወቅቱን ያገናዘበ አስተምህሮ በማድረስ ዜጎች ሰብዓዊነትን እንዲላበሱና በሀገራችን የሚስተዋለው አሰቃቂ ድርጊት እንዳይደገም የድርሻቸውን እንዲወጡ ማድረግ አለባቸው ብለዋል።

በኢትዮጵያ ባልተለመደ ሁኔታ በዜጎች ላይ የሚደርሱ ሰቆቃዎች እየተበራከቱ መሆኑን አስታውሰው፤ የሃይማኖት ተቋማት ሰብዓዊነት የዕለት ተዕለት ተግባር

«ኢትዮጵያ ... ወደ ገጽ 4 ዞሯል

## ክልሉ የዘንድሮ የአረንጓዴ አሻራ መርሐ ግብሩን እቅድ 99 በመቶ ማሳካቱን አስታወቀ

አዲሱ ገረመው

አዲስ አበባ፡- የኦሮሚያ ክልል በአራተኛው ዙር የአረንጓዴ አሻራ መርሐ ግብር እስካሁን በሠራው ሥራ የዕቅዱን 99 በመቶ ማሳካት እንደቻለ አስታወቀ፡፡ በክልሉ አንድ ሚሊዮን 184 ሺህ 755 ሄክታር መሬት ላይ ከአራት ነጥብ ሁለት ቢሊዮን በላይ ችግኞች መተከላቸውን ገልጿል፡፡

የኦሮሚያ ግብርና ቢሮ የደን ልማትና እንክብካቤ ዳይሬክተር አቶ ከተማ አብዲሳ ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት እንዳስታወቁት፤ በአራተኛው ዙር የአረንጓዴ አሻራ በክልሉ ከአራት ነጥብ ሦስት ቢሊዮን በላይ ችግኝ ለመትከል ታቅዶ ከአራት ነጥብ ሁለት ቢሊዮን በላይ ችግኝ መትከል ተችሏል፡፡ ይህም መርሐ ግብሩ ሳይጠናቀቅ 99 በመቶ ያህሉን ማሳካት ተችሏል፡፡

አቶ ከተማ፤ ባለፉት ሦስት ዓመታት የነበሩ ጉድለቶችን በመለየት ለተከላ ብቁ የሆነ ችግኞችን ማዘጋጀት ላይ ትኩረት ተደርጎ ሲሠራ እንደነበር

ክልሉ የዘንድሮ ... ወደ ገጽ 4 ዞሯል



## “በበጀት ዓመቱ ከወጪ ንግድ፣ ከሬሚታንስና ቀጥተኛ ኢንቨስትመንት 20 ቢሊዮን ዶላር የሚጠጋ ገቢ ተገኝቷል”

- ጠቅላይ ሚኒስትር ዶክተር ዐቢይ አሕመድ

ውብሸት ሰንደቁ

አዲስ አበባ፡- በ2014 በጀት ዓመት ከአገልግሎት እና ሸቀጥ የወጪ ንግድ (ኤክስፖርት) እንዲሁም ከሬሚታንስና የውጭ ቀጥተኛ ኢንቨስትመንት 20 ቢሊዮን ዶላር የሚጠጋ ገቢ መገኘቱን የኢ.ፌ.ዴ.ሪ ጠቅላይ ሚኒስትር ዶክተር ዐቢይ አሕመድ ገለፁ፡፡

«በበጀት ዓመቱ ... ወደ ገጽ 4 ዞሯል

## ‹‹የጠላት ኃይሎች ዓላማ ኢትዮጵያን ማፍረስ፣ ሰላም መንሳትና የኢኮኖሚ ልማትን ማደናቀፍ ነው››

- ሜጀር ጄኔራል መርዳሳ ሌሊሳ
የቀድሞ ሠራዊት አዛዥ

ዘላለም ግዛው


አዲስ አበባ፡- ተመሳሳይ ዓላማ አንግበው በተቀናጀ መንገድ የሚንቀሳቀሱት የአሸባሪዎቹ ሕወሓት፣ ሸኔና አልሸባብ ዋና ዓላማቸው ኢትዮጵያን ማፍረስ፣ ሰላም መንሳትና የኢኮኖሚ ልማቷን ማደናቀፍ መሆኑን የቀድሞ ሠራዊት አዛዥ ሜጀር ጄኔራል መርዳሳ ሌሊሳ ገለጹ።

ሜጀር ጄኔራል መርዳሳ ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት እንደገለጹት፤ ተመሳሳይ ዓላማ አንግበው በተቀናጀ መንገድ የሚንቀሳቀሱት የጠላት ኃይሎች ዋና ዓላማቸው ኢትዮጵያን ማፍረስ ነው። ሀገራዊ ምክክሩን ማኮላሸት፣ የሀገርን ሰላም መንሳትና የኢኮኖሚ እንቅስቃሴን ማደናቀፍ ዋና ግባቸው አድርገው የባዕዳንን ተልዕኮ ለማስፈጸም እየተንቀሳቀሱ ነው።

በተለይ አሸባሪዎቹ ሕወሓትና ሸኔ የሚሠሩት የቅንጅት ሥራ ነው። ግዳጁን የሚቀበሉት ከውጭ በመሆኑ ሀገር ለማፍረስ የሚችሉትን ሁሉ ከማድረግ እንደማይመለሱም ነው የተናገሩት። ‹‹ኢትዮጵያውያን ለተመሳሳይ ዓላማ መቆም፣ ለአንድ ሀገር መሥራት ይገባናል›› ብለዋል።

እንደርሳቸው ማብራሪያ፤ የጠላት ኃይሎቹ ወደ ጎረቤት

«የጠላት ኃይሎች ... ወደ ገጽ 4 ዞሯል



ፎቶ፡ ሃዲሽ አብርሃ







# በተያዘው በጀት ዓመት 19 ሺህ ጊጋ ዋት ሰዓት የሚጠጋ ኃይል ለማመንጨት መታቀዱ ተገለጸ

**በጋዜጣው ሪፖርተር**



አዲስ አበባ፡- በ2015 በጀት ዓመት ከተለያዩ የኃይል ምንጮች 18 ሺህ 994 ጊጋ ዋት ሰዓት የኤሌክትሪክ ኃይል ለማመንጨት መታቀዱን የኃይል ማመንጫዎች ኦፕሬሽን ሥራ አስፈጻሚ ጽ/ቤት የፕላኒንግ ሥራ አስኪያጅ ወ/ሮ ጥሩወርቅ ሽፈራው ገለጹ።

በበጀት ዓመቱ ለማመንጨት ከታቀደው ውስጥ 18 ሺህ 228 ነጥብ 48 ጊጋ ዋት ሰዓቱ ከውሃ፣ 705 ነጥብ 8 ጊጋ ዋት ሰዓቱ ከነፋስ እንዲሁም 60 ነጥብ 54 ጊጋ ዋት ሰዓቱ ከደረቅ ቆሻሻ የሚመረት ነው ተብሏል።

ዕቅዱን ለማሳካትም የሰለጠነ የሰው ኃይል ለማሟላት፤ የውሃ ኃይል ማመንጫ ግድቦችን የውሃ አጠቃቀም እና አስተዳደር ለማሻሻል፣ የመለዋወጫ ዕቃዎች ግዢ እና አቅርቦትን ለማስተካከል እንዲሁም የፍተሻና ጥገና ሥራዎች በተያዘላቸው የጊዜ ሰሌዳ መሠረት እንዲከናወኑ ለማድረግ ትኩረት ተሰጥቶ እንደሚሠራ ወ/ሮ ጥሩወርቅ ሽፈራው ተናግረዋል።

ዩኒቶቻቸው ጥገና በሚፈልጉት በፊንጫ፣ በአመርቲ ነሼ፣ በቆቃና የአዋሽ እንዲሁም በረጲ ከደረቅ ቆሻሻ ኃይል ማመንጫ ጣቢያዎች አስፈላጊውን ጥገና በማከናወን በሙሉ አቅማቸው ኃይል እንዲያመነጩ ለማድረግ እንደሚሠራም ጠቁመዋል።

በበጀት ዓመቱ በሁሉም ኃይል ማመንጫ ጣቢያዎች የኢነርጂ አቅርቦትን አስተማማኝ ሊያደርግ የሚችል ደረጃውን የጠበቀ የቅድመ መከላከል፤ የፍተሻ፣ የትንተና እና የሁኔታዎች አመላካች የጥገና ሥራ ለማከናወን እቅድ መያዙንም አመልክተዋል።

እንደ ሥራ አስኪያጇ ገለፃ ለኬንያ ኃይል ለማቅረብ የሚያስችል ስምምነት መጠናቀቁ፣ በተያዘው ክረምት በሁሉም የውኃ ኃይል ማመንጫ ጣቢያዎች በቂ የውሃ መጠን እየገባ መሆኑ፤ እንዲሁም የህዳሴ 2ኛ ዩኒት እና አይሻ 2 የንፋስ ኃይል ማመንጫ ፕሮጀክትን ወደ ኦፕሬሽን ለማስገባት እየተሠራ ያለው ሥራ በበጀት ዓመቱ ለማመንጨት የታቀደውን ኃይል ለማሳካት እንደ መልካም አጋጣሚ የሚወሰዱ ናቸው።

በበጀት ዓመቱ 17 ማመንጫ ጣቢያዎች ኃይል ያመነጫሉ ተብለው ዕቅድ የተያዘላቸው ሲሆኑ ከእነዚህም በአማካይ 3 ሺህ 862 ሜጋ ዋት ዝግጁ የሆነ ኃይል የማመንጨት አቅም እንደሚኖር መታቀዱን የኢትዮጵያ ኤሌክትሪክ ኃይል መረጃ ያመለክታል።

በተያያዘ ዜና የአይሻ ሁለት የንፋስ ኃይል ማመንጫ ፕሮጀክት አጠቃላይ የግንባታ ሂደት 78 ነጥብ 8 በመቶ መድረሱን የኢትዮጵያ ኤሌክትሪክ ኃይል ኮርፖሬት አስታውቋል።

የኢትዮጵያ ኤሌክትሪክ ኃይል ኮርፖሬት ኮሙኒኬሽን ዳሬክተር አቶ ሞገስ መኮንን ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት እንደገለጹት፤ የአይሻ ሁለት የንፋስ ኃይል ማመንጫ ፕሮጀክት በአሁኑ ወቅት አጠቃላይ አፈጻፀሙ 78 ነጥብ 8 በመቶ መድረሱን ተናግረዋል።

ፕሮጀክቱ 48 የንፋስ ተርባይኖች ያሉት ሲሆን እያንዳንዳቸው 2 ነጥብ 5 ሜጋ ዋት በድምሩ 120 ሜጋ ዋት ወይም በዓመት በአማካይ 436 ጊጋ ዋት ሰዓት ኤሌክትሪክ የማመንጨት አቅም ይኖረዋል። ከ48ቱ ውስጥ የ32ቱ ተርባይኖች ተከላ ሙሉ በሙሉ ተጠናቋል ብለዋል።

ከነዚህ ከተጠናቀቁት ተርባይኖች መካከል ደግሞ የ16ቱ ተርባይኖች የፍተሻ ሥራ ተሠርቷል። የቀሪዎቹ 16ቱ ደግሞ የፍተሻ ሥራዎች ተሰርቶ ከግሪድ ጋር የማገናኘት ሥራ ይጠብቃቸዋል ብለዋል።

የአይሻ ሁለት የንፋስ ኃይል ማመንጫ ፕሮጀክት ከአዲስ አበባ በሰባት መቶ ኪሎ ሜትር፣ ከድሬዳዋ ከተማ በሰሜን ምስራቅ 170 ኪሎ ሜትር እንዲሁም ከጅቡቲ በሰሜን ምዕራብ 150 ኪሎ ሜትር ርቀት ላይ በሶማሌ ክልል አይሻ ደወሌ ወረዳ እንደሚገኝ አቶ ሞገስ ገልጸዋል።

# "ከወጪ ንግድና በተለያዩ ዘርፎች የተመዘገበው ስኬት ለማክሮ ኢኮኖሚ አፈጻጸም መሻሻል ጉልህ ሚና ተጫውቷል"

### -የብሔራዊ ማክሮ ኢኮኖሚ ኮሚቴ አባላት

**በጋዜጣው ሪፖርተር**



አዲስ አበባ፡- በተጠናቀቀው በጀት ዓመት ከወጪ ንግድ በተጨማሪ በተለያዩ ዘርፎች የተመዘገበው ስኬት ለማክሮ ኢኮኖሚ አፈጻጸም መሻሻል ጉልህ ሚና መጫወቱን የብሔራዊ ማክሮ ኢኮኖሚ ኮሚቴ አባላት ተናገሩ፡፡

የኢትዮጵያ የ2014 ዓ.ም ማክሮ ኢኮኖሚ አፈጻጸምና የቀጣይ የትኩረት አቅጣጫዎች ጠቅላይ ሚኒስትር ዶክተር ዐቢይ አሕመድ በተገኙበት ተገምግሟል፡፡

በዚህም በበርካታ የማክሮ ኢኮኖሚ አመላካቾች የተሻለ አፈጻጸም መመዝገቡ ተመዝግቧል። በተለይ የወጪ ንግድ አፈጻጸሙ ከፍተኛ መሻሻል ከታየበት ዘርፍ ዋነኛው መሆኑ ተገልጿል፡፡

የወጪ ንግድ በተጨማሪ በሰው ተኮር የልማት ሥራዎችም የተሻሉ ተግባራት መከናወናቸው ነው የተገለጸው፡፡

የገንዘብ ሚኒስትር ዴኤታና የብሔራዊ ማክሮ ኢኮኖሚ ኮሚቴ አባል ዶክተር ኢዮብ ተካልኝ ፤ "በተጠናቀቀው በጀት ዓመት በሁሉም የማክሮ ኢኮኖሚ ዘርፎች ላይ ትኩረት ተሰጥቶ ተሠርቷል፤ ይህም ፍሬ ማፍራቱ በተግባር ታይቷል" ነው ያሉት፡፡

በተለይ የወጪ ንግዱ በተወሰኑ ምርቶች ላይ ብቻ ጥገኛ እንዳይሆን የወጪ ምርቶችን በአይነት፣ ብዛትና ጥራት ለማሻሻል ከፍተኛ ተግባር መከናወኑን አብራርተዋል፡፡

በዚህም ከቡና ምርት ከተገኘው ገቢ ባሻገር በማዕድንና ሌሎች ዘርፎች የተሻለ ገቢ መገኘቱን ጠቅሰው፤ ለአብነትም በተጠናቀቀው በጀት ዓመት የማእድን ምርት ወጪ ንግድ በአማካኝ በ64 በመቶ ማደግ ችሏል ነው ያሉት፡፡

ይህም ኢትዮጵያ የገጠሟትን ውስጣዊና ውጫዊ ችግሮች ተቋቁማ የተሻለ የማክሮ ኢኮኖሚ አፈጻጸም እንድታስመዘግብ ጉልህ ሚና ተጫውቷል ሲሉ ተናግረዋል፡፡

ኢትዮጵያ አሁን ላይ ያለባትን እዳ በተገቢው መልኩ እየከፈለች መሆኑን በማስረዳት ይህም በማክሮ ኢኮኖሚ ዘርፍ የተፈጠረውን አቅም እንደሚያመላክት ነው የገለጹት፡፡

እንደ ኢዜአ ዘገባ የኢትዮጵያ ኢንቨስትመንት ሆልዲንግስ ዋና ሥራ አስፈጻሚና የብሔራዊ ማክሮ ኢኮኖሚ ኮሚቴ አባል አቶ ማሞ ምህረቱ በበኩላቸው ባለፈው አንድ ዓመት በወጪ ንግድ ከዚህ ቀደም ከተመዘገበው በ1 ነጥብ 2 ቢሊዮን ዶላር የሚበልጥ ገቢ ማግኘት መቻሉን አብራርተዋል፡፡

ኢትዮጵያ አሜሪካ ለአፍሪካ የሰጠችው ከቀረጥ ነጻ እድል (አጎዋ) ክልከላ ውስጥ ሆናም እንኳ የማኑፋክቸሪንግ ዘርፍ የወጪ ንግድ አፈጻጸም በ26 በመቶ ማደግ ችሏል ነው ያሉት፡፡

ከቡና ምርት በታሪክ ለመጀመሪያ ጊዜ ከ1 ነጥብ 4 ቢሊዮን ዶላር በላይ ገቢ መገኘቱን ጠቅሰው፤ በቀጣይም በማክሮ ኢኮኖሚ አመላካቾች ላይ የተመዘገበውን ስኬት ይበልጥ ለማጠናከር ይሠራል ብለዋል፡፡

የፕላንና ልማት ሚኒስትሯ ዶክተር ፍጹም አሰፋ፤ ባለፈው አንድ ዓመት ከመደበኛ የማክሮ ኢኮኖሚ ሥራዎች ባሻገር በበጎ ፈቃድ አገልግሎት በበርካታ ገንዘብ የሚገመቱ የልማት ሥራዎች መከናወናቸውን ተናግረዋል፡፡

ባለፈው አንድ ዓመት በበጎ ፈቃድ አገልግሎት በአገር አቀፍ ደረጃ 8 ሺህ የአዳዲስ ቤቶች ግንባታና የ70 ሺህ ቤቶች እድሳት መከናወኑን ጠቅሰው፤ ይህም የልማት ሥራዎች አካታች እንዲሆኑ ከፍተኛ ሚና መጫወቱን አብራርተዋል፡፡

በተጨማሪም መንግሥት ለልማት ሥራዎች የሚያወጣውን በቢሊዮኖች የሚቆጠር ገንዘብ ማስቀረት መቻሉን ተችሏል።

የአረንጓዴ አሻራን ጨምሮ በበጎ ፈቃድ የተከናወኑ ተግባራት በተባበሩት መንግሥታት የጸደቁ የዘላቂ የልማት ግቦችን በመደገፍ ረገድ ከፍተኛ ሚና እንዳበረከቱም ተናግረዋል፡፡

በማክሮ ኢኮኖሚ አመላካቾች የተመዘገቡ ጠንካራ ጎኖችን በማጠናከርና ሌሎች ተግባራትንም በመጨመር በ2015 በጀት ዓመት የተሻለ የማክሮ ኢኮኖሚ አፈጻጸም ለማስመዝገብ ከወዲሁ ሥራ መጀመሩንም ሚኒስትሯ አስገንዝበዋል፡፡

# ድርጅቱ የአየር ንብረት ለውጥ ለመቋቋም የአረንጓዴ አሻራ መርሐ ግብርን ተግባራዊ እያደረገ መሆኑን ገለጸ

### - ሸገር የብዙኃን ትራንስፖርት አገልግሎት ድርጅት 2 ሺህ አምስት መቶ ችግኞችን ተክሏል

**ሞገስ ጸጋዬ**



አዲስ አበባ፡- ሸገር የብዙኃን ትራንስፖርት አገልግሎት ድርጅት አውቶብሶቹ የሚለቁት ካርቦንዳይኦክሳይድ የሚያስከትለውን የአየር ንብረት ለውጥ ለመቋቋም አረንጓዴ አሻራ መርሐ ግብርን በስፋት ተግባራዊ እያደረገ መሆኑን አስታወቀ።

ሸገር የብዙኃን ትራንስፖርት አገልግሎት ድርጅት ዋና ሥራ አስኪያጅ አቶ ቢተው ደመላሽ እንደገለጹት፤ ሸገር የብዙኃን ትራንስፖርት አገልግሎት ድርጅት የችግኝ ተከላው ንቅናቄው ከተጀመረ ጊዜ አንስቶ ኢትዮጵያን እናልብሳት በሚል መርሐ ግብር በየዓመቱ በርካታ ችግኞችን ተክሏል። አውቶብሶቹ የሚለቁት ካርቦንዳይኦክሳይድ በአየር ንብረት ለውጥ ላይ የሚያስከትለውን ተጽዕኖ ከወዲሁ ለመቋቋም አረንጓዴ አሻራን የማሳረፍ ሥራ በስፋት ተግባራዊ እያደረገ ነው።

ካርቦንዳይኦክሳይድ የሚለቁ በርካታ መኪኖች በከተማችን በሥራ ላይ በመሆናቸው አመልክተው፤ በእነዚህ ምክንያት የሚመጣውን የአየር ንብረት ለውጥ ለመቋቋም የሚረዳ አረንጓዴ አሻራን በስፋት ተግባራዊ እያደረግን እንገኛለን። ከዚህ አንጻር ድርጅቱ የችግኝ ተከላ ንቅናቄን በተለዩ ሁኔታ ትርጉም ሰጥቶ እየተንቀሳቀሰ ይገኛል ብለዋል።

እንደ አቶ ቢተው ማብራሪያ፤ የድርጅቱ ሠራተኞች ሁለት ሺህ አምስት መቶ ችግኞችን ተክለዋል። የተተከሉት ችግኞች ለምግብነት የሚውሉ እንደ ማንጎ፣ አቮካዶ ሲሆኑ እንዲሁም አገር በቀል ችግኞች ናቸው። ድርጅቱ ከአሉት አራት ዴፖዎች በተጨማሪ የችግኝ መትከያ ቦታ ከአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ከአካባቢ ጥበቃ በተሰጠው ቦታ ላይ እየተከለ ይገኛል ።

በተለያዩ የከተማዋ ቦታዎች ላይ ባለፉት ዓመታት ከ5 ሺህ በላይ ችግኞችን ተክለናል ያሉት ሥራ አስኪያጁ፤ከመትከል ባሻገር የድርጅቱ ሠራተኞች ችግኞች እንዲጸድቁ እንክብካቤ እያደረጉ ነው። እንዲሁም ድርጅቱ የትራንስፖርት አገልግሎት ከመስጠት ባሻገር የክረምት ፓኬጆችን በማዘጋጀት ማኅበራዊ ኃላፊነቱን እየተወጣ መሆኑን ገልጸዋል።

ለአብነትም የአረንጋዴ አሻራ መርሐግብር፣የአቅመ ደካሞችን ቤት እድሳት ፣ ማዕድ የማጋራትና የደም ልገሳ ፕሮግራሞች ተጠቃሾች ናቸው ያሉት አቶ ቢተው፤ ማዕድ ማጋራትና የአቅመ ደካሞችን ቤት ማደስ ዓመቱን ሙሉ የሚቀጥል ሥራ መሆኑን ተናግረዋል።

የደሃ ደሃ የሆኑ ተማሪዎችንና ወላጅ አልባ ሕጻናትን የትምህርት ቤት ባሶች ላይ ነጻ አገልግሎት እንደሚያገኙ ገልጸዋል። በትናንትናው እለት 2ሺህ አምስት መቶ የሚሆኑ ሰራተኞች በሰሚትና በሸጎሌ ዴፖዎች ማዕከል የችግኝ ተከላ ፕሮግራም አካሂደዋል።

ዜና

# የአስረኛው የበጎ ሰው ሽልማት የመጨረሻዎቹ እጩዎች ይፋ ሆኑ

**ፍቃዱ ዴሬሳ**

አዲስ አበባ፡- በዚህ ዓመት መጨረሻ ለሚካሄደው አስረኛው የበጎ ሰው ሽልማት በሕዝብ ጥቆማ ከቀረቡ ከ700 በላይ ተጠቋሚዎች መካከል የመጨረሻዎቹ እጩዎች ይፋ ሆነዋል።

የበጎ ሰው ሽልማት ቦርድ ጸሐፊ አቶ ቀለመወርቅ ሚደክሳ በሚካሄደው የእውቅናና ሽልማት ሥነ-ሥርዓት ዙሪያ በሰጡት ጋዜጣዊ መግለጫ እንዳሉት፤ ለሀገርና ለማኅበረሰቡ አርአያነት ያለው ተግባር የፈፀሙ ኢትዮጵያውያን ዕውቅና የሚያገኙበት የዓመቱ የበጎ ሰው ሽልማት ነሐሴ 29 ቀን 2014 ዓ.ም ይካሄዳል።

በዘንድሮው የበጎ ሰው ሽልማት በአስር የሽልማት ዘርፎች ከየዘርፉ ሦስት ሦስት ሰዎች በአጠቃላይ 27 የመጨረሻ እጩዎች ለበጎ ሰው ሽልማት የቀረቡ መሆናቸውን ተናግረዋል። የዘንድሮው የበጎ ሰው ሽልማት በአስር ዘርፎች ላይ ያተኮረ ቢሆንም የማኅበራዊ ጥናት ዘርፍ ላይ በቂ እጩ ሊገኝ ባለመቻሉ ቦርዱ እንዲሰረዝ ማድረጉን ጠቅሰዋል፡፡

የኪነጥበብ ዘርፉ ሰፋ ያለ እንደመሆኑ መጠን በየዓመቱ ንዑስ ዘርፍ በማበጀት የሚሸልም ሆኖ በዚህ የኪነ-ጥበብ ሽልማት የፊልም ዳይሬክቲንግ ዘርፍ የሚሸልም መሆኑን አስታውቀዋል፡፡በዚህ ዘርፍም ሄኖክ አየለ፣ ዓለምጸሐይ በቀለና አብረሃም ገዛኸኝ ለእጩነት የቀረቡ መሆናቸውን ተናግረዋል፡፡

በሁለተኛ ደረጃ በመምህርነት ዘርፍ ሲሆን ከመንዝ አካባቢ ከ40 ዓመታት በላይ በመምህርነት ያገለገሉና ለማኅበረሰቡ በርካታ ሥራዎችን ሲያከናውኑ የቆዩ እውቅ መምህር ወልደሃና ወልደዮሐንስ ፣ ዶክተር ውብሸት ዝቅያለ ደግሞ በዩኒቨርሲቲ መምህርነት በርካታ የሚያስመሰግን ሥራዎችን ሲሠሩ የቆየ መሆኑን እንዲሁም የቀድሞው የአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ ፕሬዚዳንት ፕሮፌሰር እንድርያስ እሸቴ ለእጩነት መቅረባቸውን ተጠቅሷል።

በመንግሥታዊ የሥራ ኃላፊነትን በብቃት የመወጣት ዘርፍ በኢትዮጵያ አየር መንገድ ጉልህ አስተዋፅዖ ያደረጉት አቶ ግርማ ዋቄ፣ በአሁኑ ጊዜ የኢትዮጵያ ሰብዓዊ መብት ኮሚሽን ኮሚሽነር የሆኑት ዶክተር ዳንኤል በቀለና ከክልል አቃቤ ሕግነት ጀምረው እስከ አሁን በሕጉ ዘርፍ በጎ አስተዋፅዖ ያበረከቱት አቶ ተስፋዬ ነዋይ ለእጩነት ቀርበዋል፡፡

በሚዲያና ጋዜጠኝነት ዘርፍ የሸገር ኤፍ ኤም ጋዜጠኛ ግርማ ፍስሐ፣ አንጋፋው አቶ ሰለሞን ገብረሥላሴ እንዲሁም ሠይፉ ፋንታሁን እጩ ሆነው የቀረቡ መሆናቸው ተገልጿል፡፡

በቅርስና ባህል ዘርፍ ደግሞ በባህል ሙዚቃ መሣሪያ የሚታወቀው አቡ ገብሬ፣ በመንዙማ አገልግሎታቸው የሚታወቁት ሐጂ መሐመድ አወል ሀምዛና የግዕዝ ቋንቋን ለትውልድ በማስተማር እንዲሁም ከአስር በላይ መጽሐፍትን በመጻፍ የሚታወቁት መምህር ዜና ማርቆስ እንዳለው እጩ ሆነዋል፡፡

በበጎ አድራጎትና ሰብዓዊ መብት ዘርፍ ላይ አቶ ሚኪያስ መለሰ፣ ወይዘሮ ክብረ ከበደና አቶ ሄኖክ ፍቃዱ ሲሆኑ በንግድና ሥራ ፈጠራ ዘርፍ አቶ ሰይድ መሐመድ፣ አቶ ጠንክር ቴሪና ዶክተር ፍሰሐ እሸቱ እጩ ሆነው መቅረባቸው ታውቋል ፡፡

በስምንተኛው የዲያስፖራ ዘርፍ እጩዎች ሶስቱም ሴት ኢትዮጵያውያን ሲሆኑ ዶክተር መንበረ አክሊሉ፣ ርብቃ ጌታቸውና አና ጌታነህ ለሀገር ትልቅ ሥራ የሠሩ ዜጎች መሆናቸውን ተናግረዋል፡፡

በሳይንስ ዘርፉ ደግሞ ፕሮፌሰር ረዳ ተክለሃይማኖት፣ ዶክተር ምትኬ ሞላና ፕሮፌሰር በላይ ወልደየስ እጩ እንደሆኑ ጠቅሰዋል፡፡

በሌላ በኩል በድርጅቱ ቦርድ የሚመረጥ ልዩ ተሸላሚ እንደሚኖር የተገለፀ ሲሆን የመጨረሻውን ምርጫ የሚያደርጉ በእውቀታቸው፣ በሙያቸው አንቱ የተባሉና የረዥም ጊዜ ልምድ ያላቸው እንዲሁም ታማኝ ዳኞች መሆኑንም አስታውቀዋል፡፡



አቶ ቀለመወርቅ ሚደክሳ



ፎቶ - ገበዮ ገብሬ

# በፍቼ ከተማ በክረምት በጎ ፈቃድ አገልግሎት 20 የአቅመ ደካማ ቤቶች ይታደሳሉ

**ሞገስ ተስፋ**

ፍቼ፡- በኦሮሚያ ክልል ፍቼ ከተማ አስተዳደር በክረምት የበጎ ፈቃድ አገልግሎት 20 የአቅመ ደካማ ቤቶች እንደሚታደሱ የከተማ አስተዳደሩ አስታወቀ።

የኢፌዲሪ ትምህርትና ስልጠና ባለስልጣን አመራርና ሠራተኞች በፍቼ ከተማ የአቅመ ደካሞች ቤት እድሳትና የችግኝ ተከላ መርሐ ግብር አከናውነዋል፡፡

በወቅቱ የፍቼ ከተማ አስተዳደር ከንቲባ አቶ ክፍሉ ከበደ እንደገለጹት፣ በከተማ አስተዳደሩ የክረምት የአቅመ ደካሞች ቤት እድሳት፣ የችግኝ ተከላና የተለያዩ የበጎ ፈቃድ አገልግሎቶች ኅብረተሰቡን ባሳተፈ መልኩ እየተከናወኑ ይገኛል።

በክረምቱ የበጎ ፈቃድ አገልግሎት 20 የአቅመ ደካማ ቤቶች ለማደስ ዕቅድ ተይዟል። የአቅመ ደካማ ቤቶች የማደሱ ተግባር ከተለያዩ የመንግሥት ተቋማትና ከኅብረተሰቡ ጋር በመተባበር እየተከናወነ ይገኛል ብለዋል።

የፍቼ ከተማ አስተዳደር የቤት እድሳትና ሌሎች የክረምት በጎ ፈቃድ አገልግሎቶችን እንደ ዋና ሥራ በመያዝ በማስተባበር ላይ መሆኑን የገለጹት ከንቲባው፤ ተመሳሳይ የበጎ ፈቃድ አገልግሎቶችም በ2015 ዓ.ም እንደሚቀጥሉ አስታውቀዋል።

የኢፌዲሪ ትምህርትና ስልጠና ባለስልጣን አመራርና ሠራተኞች በፍቼ ከተማ የቤት እድሳት መርሐ ግብር አከናውነዋል። በተጨማሪም አበበች ጉበና በተሰኘው አካባቢ ተገኝተው ከከተማ አስተዳደሩ አመራሮች፣ ከአባገዳዎችና ከአካባቢው ነዋሪዎች ጋር በጋራ የችግኝ ተከላና የበጎ ፈቃድ አገልግሎት መርሐ ግብር አከናውነዋል፡፡

በወቅቱ የባለስልጣኑ ዋና ዳይሬክተር ዶክተር አንዱአለም አድማሴ፤ ባለስልጣኑ የአምስት አቅመ ደካሞችን ቤት እድሳት ድጋፍ ማድረጉን ጠቁመዋል።

በተጨማሪ የኢኮኖሚ አቅማቸው ዝቅተኛ ከሆኑ ቤተሰብ ለተገኙ 250 ተማሪዎች ከ200 ሺ ብር በላይ የሚገመት ደብተር፣ ቦርሳና የተለያዩ የትምህርት ቁሳቁሶች ድጋፍ መደረጉን ገልጸዋል።

የመማሪያ ቁሳቁስ ድጋፍ የተደረገላቸው ተማሪዎች ትምህርታቸውን ጠንክረው እንደሚማሩ ገልጸዋል። የባለስልጣኑ አመራሮችና ሠራተኞች ሰብዓዊ የሆነ የበጎ ፈቃድ አገልግሎት መስጠት ትልቅ ትርጉም አለው። ይህ አይነት ተግባር በሁሉም ኢትዮጵያዊ ዘንድ ተጠናክሮ መቀጠል አለበት ብለዋል።

የቤታቸው እድሳት ከተጀመረላቸው የፍቼ ከተማ አቅመ ደካሞች መካከል የሆኑት ወይዘሮ እሼቴ ደምሴ፤ ቤታቸው በበጎ ፈቃደኞች እየታደሰላቸው በመሆኑ ምስጋና አቅርበዋል።

ጧሪ ልጅ እንደሌላቸውና በሰው ቤት እየሠሩ የዕለት ጉርሳቸውን እንደሚያገኙ ገልጸው፤ ከዚህ ባለፈ ደሳሳ ቤታቸው በእርጅና ምክንያት ተጎድቶ ጣሪያውም ዝናብ እያፈሰሰ ያስቸግራቸው እንደነበር ተናግረዋል።

የከተማ አስተዳደሩ ችግራቸውን በመመልከት በጎ ፈቃደኞችን አስተባብሮ ሊያድስላቸው መሆኑን ሲያውቁ ደስታ እንደተሰማቸው ተመሳሳይ የበጎ ፈቃድ አገልግሎቶች ሊበራከቱ እንደሚገባ መልዕክት አስተላልፈዋል።

# ከግጭት ይልቅ ውይይትን የሚያስቀድም ትውልድ ለመፍጠር የንባብ ባህልን ማዳበር እንደሚገባ ተገለጸ

**አዲሱ ገረመው**




አዲስ አበባ፡- ከግጭት ይልቅ ውይይትን የሚያስቀድም ትውልድ ለመፍጠር የንባብ ባህልን ማዳበር እንደሚገባ ተገለጸ። ንባብ ለሕይወት የመጽሐፍትና የምርምር ተቋማት አውደ ርዕይ ትላንት በአዲስ አበባ ኤግዚቢሽን ማዕከል ተከፈቷል።

ንባብ ለሕይወት አውድ ርዕይ ትላንት በተከፈተበት ወቅት የኢትዮጵያ ቤተ መዛግብትና ቤተ መጽሐፍት አገልግሎት ዋና ዳይሬክተር አቶ ይኩኖአምላክ መዝገቡ፤ ለሥጋዊ ሕይወት መሠረታዊ ፍላጎት እንደሚያስፈልገው ሁሉ አዕምሮም የእውቀት ምግብ ያስፈልገዋል ሲሉ ተናግረዋል። ይህም ከመጽሐፍት ንባብ እንደሚገኝ ጠቁመዋል። ከግጭት ይልቅ ውይይትን የሚያስቀድም ትውልድ ለመፍጠር የንባብ ባህልን ማዳበር እንደሚገባም ነው የገለጹት።

የሚያነብ ማኅበረሰብ በራሱም ላይ ሆነ በሌላው ላይ ጉዳት አያደርስም ያሉት ዋና ዳይሬክተሩ፤ ንባብ አዕምሮን የሚገነባ ተግባር እንደመሆኑ የሚያነብ ኅብረተሰብ ማፍራት እንደሚገባ ገልጸዋል። ንባብ ስብዕናን የመገንባት ሥራን እንደሚሠራ፤ ስብዕናው የተገነባ ትውልድ ደግሞ ከግጭት ይልቅ ውይይትን እንዲሁም ከጥፋት ይልቅ ልማትን የሚያስቀድም እንደሆነ ጠቅሰዋል። ከዚህ አንጻር አውደ ርዕይው በውይይት የሚያምንና የሚገዛ እንዲሁም የሀሳብ ልዩነትን የሚያስተናግድ ትውልድ እንዲፈጠር ያስችላል ነው ያሉት።

"ንባብ ለሕይወት" በዓመት ክረምትን ጠብቆ ላለፉት ስድስት ዓመታት ሲካሄድ የነበረ መሆኑን አንስተው፤ ባለፉት ሁለት ዓመታት በኮሮና ቫይረስ ወረርሽኝ ምክንያት ቢቀርም ዳግም መጀመሩን ገልጸዋል። አውደ ርዕይው አንባቢው በየቤተ መጽሐፍቱ ሳይዞር በአንድ ቦታ አገልግሎት ለማግኘት እንደሚያስችለውና ከትምህርት ባሻገር የንባብ ባህልን ለማዳበር ትልቅ ፋይዳ ያለው ሁነት መሆኑን ጠቅሰዋል።

የንባብ ለሕይወት ፕሮጀክት ዳይሬክተር አቶ ቢንያም ከበደ በበኩላቸው፤ የአውደ ርዕይው ዓላማ የንባብ ንቅናቄን መፍጠር እንደሆነ ተናግረዋል። መጽሐፍትን በቅናሽና በዓይነት በማቅረብ ኅብረተሰቡ ገዝቶ እንዲጠቀም ትልቅ ፋይዳ እንዳለው ጠቅሰዋል።

ለኢትዮጵያ የሚበጃት ለሰው የሚራራ ትውልድ መፍጠር ነው ያሉት አቶ ቢንያም፤ ቤተሰብ ልጆቹን የንባብ ባህል ማስለመድ እንዳለበት መክረዋል። ወላጆች ልጆቻቸውን በአውደ ርዕይው በማሳተፍ ብቁ ዜጋ ለማፍራት በሚደረገው ተግባር ተባባሪ እንዲሆኑ ጥሪ አቅርበዋል። አውደ ርዕይው ልጆችን ታሳቢ ያደረገና የተሻለ ትውልድን ለመፍጠር የማንበብ ባህል ማሳደግ ላይ ትኩረቱን ያደረገ እንደሆነም አመልክተዋል።

ለአምስት ቀናት በሚቆየው አውደ ርዕይ ትምህርታዊ የመጽሐፍት ውይይትና ምርቃትን ጨምሮ ከንባብ ጋር ግንኙነት ያላቸው በርካታ ሁነቶች እንደሚኖሩ በመጠቆም፤ በአውደ ርዕይው ደራሲዎች፣ አሳታሚዎች፣ የከፍተኛ ትምህርት ተቋማትና መጽሐፍት አከፋፋዮች ተሳታፊ እንደሆኑ አስታውቀዋል።

# ምክር ቤቱ የአገራዊ ምክክሩን ሂደት የሚከታተል ቡድን ማቋቋሙን አስታወቀ

**ዳግማዊት ግርማ**

አዲስ አበባ፡- የሲቪል ማህበረሰብ ድርጅቶች ምክር ቤት የሀገራዊ ምክክሩን ሂደት የሚከታተል ቡድን አቋቋመ።

የሲቪል ማኅበረሰብ ድርጅቶች ምክር ቤት ሀገራዊ ምክክሩን አስመልክቶ ከሲቪል ማኅበራትና ከባለድርሻ አካላት ጋር ትናንትና ውይይት አድርጓል።

የምክር ቤቱ ዋና ዳይሬክተር አቶ ሄኖክ መለሰ በወቅቱ፤ የሀገራዊ ምክክሩን ሂደት የሚከታተል ቡድን ማቋቋም አስፈላጊ መሆኑን ተናግረዋል።

የሲቪል ማኅበረሰብ ድርጅቶች ምክር ቤት ሀገራዊ ምክክሩን በሚመለከቱ ጉዳዮች ላይ የሚሠሩ የተለያዩ የሲቪል ማኅበረሰብ ድርጅቶችንና ባለሙያዎችን በማካተት ሀገራዊ ምክክሩን ዋነኛ አጀንዳው አድርጎ የሚሠራ አንድ የሀገራዊ ምክክር ትኩረት ማዕከል ቡድን (National Dialogue Reference Group) እንዲቋቋም ማድረጉን ገልጸዋል።

በመጪው ኅዳር ወር ሊጀመር የታቀደው የሀገራዊ ምክክር ሂደቱ የተሳካ እንዲሆን የሲቪል ማኅበረሰብ ድርጅቶች የበኩላቸውን ድርሻ እንዲወጡ ምክር ቤት ሲያደርግ የቆየውን ጥረት አጠናክሮ እንደሚቀጥል አቶ ሄኖክ ጠቁመዋል።

የሲቪል ማኅበራት የምክክር ሂደቱ ተጀምሮ እስኪጠናቀቅ ድረስ በሚኖሩት የተለያዩ እርከኖች ላይ በተለያየ መልኩ ተሳትፎ እንደሚያደርግና በሂደቶቹ ላይ ክትትል በማድረግ አስፈላጊውን ግብዓት እንደሚያቀርብ ገልጸዋል፡፡

የሲቪል ማኅበረሰብ ተሳትፎ በተናጠልና በተበጣጠሰ መልኩ ከማድረግ ይልቅ እንደ ዘርፍ በተናበበ መልኩ መጓዝ አለባቸው። ይህም ሀገራዊ ምክክሩን ውጤታማ ከማድረግ አንጻርም ሆነ የዘርፉን ሀገራዊ አበርክቶ ከማሳደግ አኳያ የሚኖረው ፋይዳ ከፍ ያለ ይሆናል ሲሉ አቶ ሄኖክ ተናግረዋል፡፡

እንደ ዋና ዳይሬክተሩ ገለጻ፤ ምክር ቤቱ የብሔራዊ ምክክር ሂደቱ ምቹ፣ ሁሉን አቀፍ እና አካታች እንዲሆን የበኩሉን ድርሻ ለመወጣት በርካታ ሥራዎችን እየሠራ ይገኛል።

በተለይ የሲቪል ማኅበረሰብ ድርጅቶች በምክክር ሂደቱ ላይ የሚኖራቸውን ሚና ለማሳለጥ የሚረዳ የተሳትፎ-ማዕቀፍ ፖሊሲና በምክክር ሂደቱ የሲቪል ማኅበረሰብ ድርጅቶቹ ሊከተሏቸው የሚገቡ መርሆዎችን በማዘጋጀት፤ በዕውቀት ላይ የተመሠረተና የተቀናጀ ተሳትፎ በማድረግ የምክክር ሂደቱ እንዲሳካ የበኩላቸውን ሚና እንዲወጡ የሚያስችሉ ዝግጅቶችን በተጠናከረ ሁኔታ እያከናወነ ይገኛል ብለዋል።

የተጀመረው ሀገራዊ ምክክር የተሻለ ሀገራዊ መግባባትን ለመገንባትና በሂደትም የመተማመንና ተቀራርቦ የመሥራት ባህልን በማዳበር ይረዳል ያሉት ዋና ዳይሬክተሩ፤ እንደ ሀገር መሠረታዊ በሆኑ ጉዳዮች ላይ ያሉብንን የሃሳብ ልዩነቶችና አለመግባባቶች በመፍታት ረገድ ውጤታማ እንዲሆን የሲቪል ማኅበራት ሚና ወሳኝ መሆኑን ገልጸዋል።

ምክር ቤቱ ያዘጋጀው መድረክ የሲቪል ማኅበረሰብ ድርጅቶችን ተሳትፎ በማሳደግ በሀገራዊ ምክክር ሂደቱ ላይ አስፈላጊ የሆኑ ቴክኒካልና ስትራቴጂክ ጉዳዮች ላይ አስተዋጽዖ ማድረግ የሚቻልበት ሁኔታዎችን ለመፍጠር ያለመ ነው።

የኢትዮጵያ ሲቪል ማኅበረሰብ ድርጅቶች ምክር ቤት ከ3 ሺህ 700 በላይ የሲቪል ማኅበረሰብ ድርጅቶች በአባልነት ይዟል።

# ‹‹የጠላት ኃይሎች ዓላማ ኢትዮጵያን...

**ከ1ኛው ገፅ የዞረ**

ሀገራት የሚያሻግር መንገድ እንዲከፈትላቸው ይፈልጋሉ፣ ይሄንን ለማግኘትም የማይፈነቅሉት ጉድጓድ የለም። ኢትዮጵያ ሰላም እንዳታገኝ ይታትራሉ፣ የባዕዳንን ተልዕኮ ለማስፈጸምም ይሠራሉ።

ሁል ጊዜም ከጠላት ጋር ጦርነት በተጀመረ ጊዜ የውስጥ ጠላቶች በጥቅማ ጥቅም ተደልለው የውጭ ኃይሎችን ተልዕኮ በመቀበል እናት ሀገራቸውን ኢትዮጵያን ሲወጓት ነበርም ሲሉም ሜጀር ጄኔራል መርዳሳ አስታውሰዋል።

የሀገር ውስጥ የጥፋት ቡድኖቹ አልሸባብን ሲፈልጉ ያወግዙታል፤ አንዳንዴ ደግሞ ጥቅም በመቀበል በእጅ አዙር በመደገፍ በሀገር ላይ ጥፋት እንዲፈጽም እንደሚወተውቱም ነው የተናገሩት።

የጥፋትን ኃይሎችን ሴራ ለማክሸፍ የሕዝብ አንድነት እንደሚያስፈልግ፣ ለተመሳሳይ ዓላማ በጋራ መሰለፍ እንደሚገባ፣ በወታደራዊ አሰላለፍም መጠናከር እና የጠላትን እንቅስቃሴ ነቅቶ መከታተል እንደሚገባም ሜጀር ጄኔራል መርዳሳ ገልጸዋል።

የጠላት ኃይሎች ሀገራዊ ምክክሩ እንዳይሳካ መሥራት ዋና የትኩረት መስካቸው አድርገው እንደሚንቀሳቀሱ የጠቆሙት ሜጀር ጄኔራል መርዳሳ፤ ‹‹የውጭ ኃይሎች የጦር መሳሪያ ያቀርባሉ፣ ጥይት ያቀብላሉ፣ ገንዘብ ይሰጣሉ፤ የምንገዳደለው፣ የምንዋጋው እርስ በእርስ ነው፤ ጉዳቱም ለሀገር መሆኑን መገንዘብ ያስፈልጋል›› ሲሉም ነው የተናገሩት።

የውጭ ኃይሎች ዋና ዓላማቸው አገር መበታተን ነው። ወጣቶች በሐሰት ሰበካ ተታልለው ሕይወታቸውን እንዳይገብሩ ሊጠነቀቁ እንደሚገባ አሳስበዋል። ለአንዲት ኢትዮጵያ ከተሰለፉና ለኢትዮጵያ ሰላምና ደህንነት እየተዋደቁ ካሉ አገር ወዳድ ሠራዊት ጎን ሊሰለፉ እንደሚገባቸውም መክረዋል።

ኢትዮጵያ አንድነቷን ጠብቃ የምትቀጥል ከሆነ ታላቅ ትሆናለች፣ ችግሮች ቢኖሩ እንኳን በሰላማዊ መንገድ ለመፍታት ያስፈልጋል ያሉት ሜጀር ጄኔራል መርዳሳ፤ አንድነት ከጠፋ፣ ክፍተት ከተፈጠረ ጠላት ዓላማውን ለማስተግበር ዕድል ያገኛል። በመሆኑም የጠላትን አሠራር ለማክሸፍ ኢትዮጵያውያን በአንድነት ሊቆሙ እንደሚገባም ነው የተናገሩት።

የሀገር ልማትና የውስጥ ሰላም ለማስፈን በጋራ መንቀሳቀስ ያስፈልጋል። ሁሉም በልማት የበኩሉን አስተዋጽኦ እያደረገ ጎን ለጎን ደግሞ ለሀገር ሰላም የድርሻውን ማበርከት እንዳለበትም አመልክተዋል።

ሕዝባዊ አንድነት ከላላ፣ በቋንቋ ተከፋፍሎ መቋሰል ከቀጠለ ለጠላት ዕድል መስጠት ስለሚሆን መከፋፈልን በመተው አንድነትን ማጠናከር ይገባል። በዚህም ኢትዮጵያ ታሸንፋለች እንጂ አትሸነፍም ነው ያሉት።

# ክልሉ የዘንድሮ የአረንጓዴ አሻራ መርሐ...

**ከ1ኛው ገፅ የዞረ**

ገልጸዋል። ለተከላው ቅድመ ዝግጅትም ችግኝ ወደ ተከላ ቦታ በማጓጓዝ፣ በሙያ የተደገፈ የጉድጓድ ቁፋሮ ዝግጅት በማድረግና ኅብረተሰቡን በማዘጋጀት ረገድ በርካታ ሥራዎች መሠራታቸውን ጠቅሰዋል። ከዚህ ባሻገር የሀገር ውስጥ ዝርያ ያላቸው፣ ለምግብ የሚውሉና በፍራፍሬ ተክሎችም ላይ ትኩረት መደረጉን አንስተዋል። በዚህም ግብዓቶች በወቅቱ ተዘጋጅተው የችግኝ ጣቢያዎች ወደ ሥራ እንዲገቡ መደረጉን ተናግረዋል።

በአራተኛው ዙር አረንጓዴ አሻራ ልማት በክልሉ ወደ አራት ነጥብ ስምንት ቢሊዮን ችግኝ ተዘጋጅቶ እንደነበር የገለጹት ዳይሬክተሩ፤ የችግኝ ተከላው በመደበኛው በቂ እርጥበት ባለበት የአየር ንብረትና በአንድ ጀንበር በሚል ንቅናቄ እንደተከናወነ ጠቅሰው፤በአንድ ቀን ብቻ ወደ 400 ሚሊዮን ችግኞችን ለመትከል ታቅዶ፤ በከፍተኛ የኅብረተሰብ ንቅናቄ ተሳትፎ ወደ 471 ሚሊዮን የሚሆኑ ችግኞች እንደተተከሉም አስታውቀዋል። በቀረው ጊዜ ውስጥም ቀሪ የተከላ ሥራ እንደሚጠናቀቅ ጠቁመዋል።

ችግኝ ተከላው ከምንጊዜውም በተሻለ ሁኔታ ኅብረተሰቡን በስፋት በማሳተፍ፣ ግንዛቤን በመፍጠር ክፍተቶች እንዳይፈጠሩ በሙያ እንዲደገፍ ተደርጎ እንደተከናወነ ገልጸው፤ በአጠቃላይ ወደ አንድ ሚሊዮን 184ሺህ 755 ሄክታር መሬት ላይ የችግኝ ተከላ መከናወኑን ገልጸዋል። ከዚህ ውስጥ ለደን ሽፋን 40 በመቶ የተሰጠ ሲሆን፣ እንደ ፍራፍሬ፣ ቀርከሃ፣ የውበትና ሌሎች ችግኞችም መተከላቸውንና ለቀጣይ ዓመትም ከወዲሁ የችግኝ ጣቢያዎችን ወደ ሥራ የማስገባት እንቅስቃሴ እየተደረገ እንዳለም አመልክተዋል።

ችግኝ ተከላ መትከል ብቻ ሳይሆን ተንከባክቦ ማሳደግም ያስፈልጋል ያሉት ዳይሬክተሩ፤ከዚህ አኳያ ለወደ ፊት መሠራት ያለባቸው ተግባራት ተለይተው አቅጣጫ እንደተሰጠባቸው ተናግረዋል። በዚህም የተተከሉ ችግኞች በዝናብ እርጥበት እስከ ነሐሴ አጋማሽ ድረስ መጽደቃቸውን በመከታተል፣ የታለፉ ጉድጓዶችም ካሉ የመትከል ሥራዎች እንደሚከናወኑ ጠቅሰዋል። ለዚህ የሚሆኑ ችግኞችም ዝግጁ እንደሆኑ አስታውቀዋል።

አቶ ከተማ፤ የእንክብካቤ ሥራው ከተከላው ባልተናነሰ ሁኔታ ትኩረት እንደሚሰጠው ተናግረዋል። በዚህም በየአካባቢው ችግኝ የማረምና የመኮትኮት ሥራ እንደሚከናወን፤ ከእንስሳትና ከሰው ንክኪ እንዲጠበቅ የማድረግ፤ የእንክብካቤ እቅድ እንዲታቀድና በየደረጃው ያለው ምክር ቤት ውይይት አድርጎበት አቅጣጫ እንደሚሰጥ በመጥቀስ፤ ለተከላ ከፍተኛ ንቅናቄ ተደርጎ እንደተሠራው ዓመቱን ሙሉ ለእንክብካቤም ሁሉም ዜጋ ተሳትፎ እንዲያደርግ ይሠራል ብለዋል።

# “በበጀት ዓመቱ ከወጪ ንግድ፣ ከሬሚታንስና...

**ከ1ኛው ገፅ የዞረ**

ጠቅላይ ሚኒስትር ዶክተር ዐቢይ ማክሮ ኢኮኖሚ ኮሚቴ ስብሰባ ላይ እንደገለጹት፤ በዘንድሮው ዓመት የአገልግሎትና የሸቀጦች ኤክስፖርት ከ10 ነጥብ 2 ቢሊዮን ዶላር በላይ ተገኝቷል። ይህ የወጪ ንግድ ገቢ ሬሚታንስንና የውጭ ቀጥተኛ ኢንቨስትመንትን ሲጨምር ወደ 20 ቢሊዮን ዶላር ገደማ የሚጠጋ ነው።

ጠቅላይ ሚኒስትሩ በውጪ ንግዱ ዘርፍ የተገኘው ውጤት እምርታ የታየበት መሆኑን ጠቁመው፤ እጅግ አስቸጋሪ ሁኔታዎች ውስጥ ሆነን የመጣ ውጤት በመሆኑ ሁላችንም በተገኘው ውጤት ልንኮራ ይገባል ብለዋል።

በማክሮ ኢኮኖሚ የዕድገት አመላካቾች ከግሽበት በስተቀር በሁሉም ዘርፍ የተገኘው እምርታ በእጅጉ ይበል የሚያስብልና የሚያኩራራ እንዲሁም ይበልጥ እንድንተጋ የሚያነሳሳ ነው ያሉት ጠቅላይ ሚኒስትር ዶክተር ዐቢይ፤ ሆኖም ኢትዮጵያ ያላት የኤክስፖርት እምቅ አቅም አኳያ ከተገኘው በብዙ እጥፍ መሥራትና ማሳደግ የሚቻል መሆኑን ጠቁመዋል።

የወጪ ንግድን(ኤክስፖርትን) ሳያሳድጉ ሀገርን ማሳደግ እንደሚከብድ ጠቁመው፤ ምንም እንኳን የማክሮ ኢኮኖሚ የዕድገት አመላካቾች በርካታ ቢሆኑም የማክሮ ኢኮኖሚ ኮሚቴው በኤክስፖርት ምን አመጣሁ ብሎ በዋናነት የሚገመግመው የወጪ ንግድ ለሌሎች ሴክተሮች ዕድገት ወሳኝ በመሆኑ ነው ብለዋል።

መንገድ፣ ግብርና እና የመሳሰሉት ዘርፎች የሚደገፉትና የሚነቃቁት ሥራቸውን ከውነው ዕድገት የሚያመጡት በውጪ ንግድ በሚገኘው ገቢ መደገፍ ሲቻል እንደሆነም ተናግረዋል።

በሌላ በኩል አረንጓዴ አሻራ ላይ ትምህርት ሰጪ እና ሕዝቡን የሚያስመሰግን ሥራ መሠራቱን እንዲሁም የቱሪዝም ሀብቶች ላይ ተመሳሳይ ትኩረት አድርጎ መሥራት እንደሚገባ ጠቅላይ ሚኒስትሩ አንስተዋል።

ኢትዮጵያ በአራት ዓመታት ውስጥ 25 ቢሊዮን ችግኝ መትከል መቻሏን የተናገሩት ጠቅላይ ሚኒስትሩ፤ ለጠጥ አድርጎ ከታቀደ በአራት ዓመት ውስጥ ኢትዮጵያ ምን ማድረግ እንደምትችል ያስገነዘበ ትምህርት መቀሰሙን ጠቁመዋል።

እንደ ጠቅላይ ሚኒስትር ዶክተር ዐቢይ ገለፃ፤ የኢትዮጵያ ሕዝብ ያሳካው የአረጓዴ አሻራ(ግሪን ሌጋሲ) ውጤት በቀላሉ የሚታይ አይደለም። ሕዝቡ ለተከታታይ ዓመታት ምንም ክፍያ ሳያገኝ የሠራው ሥራ አስደማሚ ነው። ወደ ብልጽግና የሄዱ ሀገራት በሙሉ ታሪካቸው ሲታይ ስሙ ግሪን ሌጋሲ አይባል እንጂ የብልፅናቸው ጅማሬ ከችግኝ ተከላ የሚጀምር ነው።

በብልጽግና ጅማሬችን አሁን የምንከተለው አረንጓዴ አሻራ መርሐ ግብር ዛሬ ላለው ትውልድ ላይገባው እንደሚችል ያነሱት ጠቅላይ ሚኒስትሩ፤ እርግጠኛ ሆኜ የምነግራችሁ ከዓመታት በኋላ የኢትዮጵያ ብልጽግና ሲረጋገጥ ትውልድ ማየት የሚፈልገው አንዱ ነገር አረንጓዴ ሥፍራዎችን ነው። ይህ ደግሞ ሊሳካ የሚችለው ዛሬ ችግኞችን ስንተክል ነው ብለዋል።

በአረንጓዴ አሻራ ተግባራዊ በማድረግ (በግሪን ሌጋሲ) የታየው ውጤት የሚያበረታታ እና ተጠናክሮ መቀጠል ያለበት መሆኑንም ጠቅሰዋል። የኢትዮጵያ ሕዝብም በግሪን ሌጋሲ ላይ በሠራው ሥራ ሊመሰገንና ሊደነቅ የሚገባው መሆኑን አስገንዝበዋል።

ከቱሪዝም ዘርፉ አንፃርም ብዙ ሥራዎች እንደሚጠበቁ የተናገሩት ጠቅላይ ሚኒስትር ዶክተር ዐቢይ፤ በዘርፉ እንደ ኢትዮጵያ ሊሸጥ የሚችል መልከዓ ምድርና ታሪክ ያለው ሀገር ባይኖርም የአገልግሎት ኢንዱስትሪውን ማዘመን ስላልቻልን እየተጠቀምንበት አይደለም ብለዋል።

በቱሪዝም ዘርፍ ያሉትን መስህቦች በመጠቀም በዘርፉ ከፍተኛ እምርታ ሊመጣ እንደሚችል ጠቁመዋል። ለአብነት ኢትዮጵያ አንድ ተራራ ለአንድ ሪዞርት ፖሊሲን ብትከተል በበርካታ አካባቢ ያሉ መልከዓ ምድሮቿን በመጠቀም ሀገሪቱን የቱሪስት መስህብ ማድረግ እንደሚቻል አመልክተዋል።

# “ኢትዮጵያ የተለያዩ ሃይማኖቶችን...

**ከ1ኛው ገፅ የዞረ**

እንዲሆንና ወንድም በወንድሙ ላይ መጨከን እንዲወገድ መሥራት እንደለባቸው ገልጸዋል።

በሀገሪቱ በተለያዩ ጊዜያት በተከሰቱ ግጭቶች ምክንያት ተፈናቅለው በየመጠለያው የሚገኙ ዜጎች ወደ መደበኛ ሕይወታቸው እንዲመለሱ ለማድረግም የሃይማኖት ተቋማትን ጨምሮ መላው ኢትዮጵያውያን ሊረባረቡ እንደሚገባ አስገንዝበዋል።

በዛሬይቱ ኢትዮጵያ ከሰላም በላይ የምንፈልገው ጉዳይ እንደሌለ የጠቀሱት ፕሬዚዳንት ሣህለወርቅ፤ የምንፈልገው ሰላም እንዲረጋገጥ ሁላችንም ኃላፊነታችንን በአግባቡ መወጣት አለብን ብለዋል።

በእያንዳንዱ ሃይማኖት ተቋማት ሕዝብን የማገልገል መንፈስ መጠናከርና ፍትሕ መስፈን በሀገራችን የሚስተዋሉ ዘርፈ ብዙ ችግሮችን እንድንሻገር ያግዘናል ያሉት ፕሬዚዳንቷ፤ የሃይማኖት አባቶችም ተከታዮቻቸውን በማስተማርና በመገሰጽ ለሀገር ሰላም ሚናቸውን ሊወጡ ይገባል። ኢትዮጵያ ሁሉም ዜጋ እኩል በሰላም የሚኖርባት ሀገር እንድትሆንም ሁላችም በጋራ መነሳት እንደሚኖርብን አሳስበዋል።

ኢትዮጵያ እንደማንኛውም ታዳጊ ሀገር እድገትና ልማት ያስፈልጋታል ያሉት ፕሬዚዳንቷ፤ ይህን እድገት ለማምጣት የሃይማኖት ተቋማትን ጨምሮ የሁሉም ርብርብና አንድነት በእጅጉ እንደሚያስፈልግ ጠቁመዋል።

በጉባኤው ላይ የእንኳን ደህና መጣችሁ መልእክት ያስተላለፉት የኢትዮጵያ የሃይማኖት ተቋማት ጉባኤ ሰብሳቢ ብፁዕ አቡነ ኅርኀርዮስ በበኩላቸው፤ ጉባኤው አባል የሃይማኖት ተቋማትን በማስተባበር ሰላምን፣ ፍቅርንና መከባበርን በመገንባት ላይ መሆኑን ገልጸዋል።

በሀገራችን ባለፉት ዓመታት የተፈጠሩና አሁንም ድረስ የዘለቁ ግጭቶችና አለመግባባቶች እንዲፈቱ የበኩሉን ጥረት ሲያደርግ መቆየቱን አስታውሰው፤ ዛሬም ድረስ ችግሩ ሊቀረፍ ስላልቻለ ሁላችንም መሥራት ያለብንን የቤት ሥራ በአግባቡ መከወን ይጠበቅብናል ብለዋል።

በማወቅም ይሁን ባለማወቅ በማኅበራዊ ትስስር ገጾች ግጭትን የሚቀሰቅሱና የሚያባብሱ የጥላቻ መልዕክቶች የሚያስተላልፉ ወገኖች መኖራቸውን ጠቁመው፤ እነዚህ ተግባራት በቶሎ ሊታረሙ ይገባል። መንግሥትም መሰል ችግሮችን ለመከላከል ያወጣቸውን ሕጎች ሳይሸራረፉ ተግባራዊ እንዲያደርግ ጠይቀዋል።

በሃይማኖት ተቋማት መካከል የሚስተዋሉ ጤናማ ያልሆኑ የፉክክር መንፈሶች የሀገራችን ሰላምና አብሮነት የሚጎዱ በመሆናቸው ሊቆሙ እንደሚገባም ብፁዕነታቸው አሳስበዋል።

የሀገር ሰላም በምኞት ብቻ አይረጋገጥም ያሉት ብፁዕ አቡነ ኅርኀርዮስ፤ ሃይማኖቶች ሰላምና እርቅ መሠረቶች ስለሆኑ የሃይማኖት ተቋማት መሪዎች ከፈጣሪ የተሰጠንን ሰላምን የመስበክ ተልዕኮ በአግባቡ ልንወጣ ይገባናል ብለዋል።

የኢፌዴሪ የሰላም ሚኒስትር አቶ ብናልፍ አንዱዓለም በበኩላቸው፤ ሃይማኖት በግለሰብ ደረጃም ይሁን በማኅበረሰቡ ውስጥ ሰላም እንዲሰፍን የሚጫወተው ሚና እጅግ ከፍተኛ ነው። በተለይ እንደ ኢትዮጵያ አብዛኛው ሕዝብ አማኝ በሆነበት ሀገር ውስጥ ሰላምን ለማስፈን የሃይማኖት ተቋማት ሚና ከፍ ያለ መሆኑን ጠቁመዋል።

የሃይማኖት አባቶችና አማኞች የተጣሉትን በማስታረቅ፣ አጥፊዎችን በመገሰጽ፣ የተበደሉትን በመካስና የተገፉትን በማቀፍ ጤናማና ሰላማዊ የማኅበረሰብ ግንኙነት እንዲፈጠር ለማድረግ የሚያበረክቱት አስተዋጽኦ ወደር የለሽ መሆኑን አመልክተዋል።

የኢትዮጵያ የሃይማኖት ተቋማት በኢትዮጵያ ታሪክ ውስጥ በሀገር ግንባታ፣ ታሪክና ቅርስን ለትውልድ በማስተላለፍና የተፈጥሮ ሀብትን በመጠበቅ አበርክቷቸው ከፍ ያለ መሆኑን አስታውሰው፤ ሕዝብ ከተፈጥሮ መቅሰፍቶች እንዲጠበቅ ተግተው በመጸለይና በአጠቃላይ ሀገርን በመትከልና በማሻገር ጉልህ ሚና ተጫውተዋል ብለዋል።

ከቅርብ ጊዜያት ወዲህ በኢትዮጵያና በሌሎችም ሀገራት በሃይማኖት ስም የሚፈጠሩ ግጭቶች መበራከት አሳሳቢ ነው ያሉት አቶ ብናልፍ፤ ግጭቶች መነሻቸው ሃይማኖታዊ ሳይሆን ስልጣን አልያም ጥቅም በሚፈልጉ ጥቂት ግለሰቦች የሚፈጠር መሆኑን መረዳት ይገባል። በመሆኑም ለመላው የኢትዮጵያ ሕዝብና የሃይማኖት ተቋማት መሰል ችግሮች እንዲወገዱ በትብብር መሥራት እንደሚገባ ጥሪ አቅርበዋል።

# ርዕሰ አንቀፅ

## አበረታቹ የማክሮ ኢኮኖሚ ዕድገት በቀጣይ ዓመታትም ተጠናክሮ ሊቀጥል ይገባል!

በተጠናቀቀው የ2014 በጀት ዓመት የኢትዮጵያ ኢኮኖሚ ከ6 በመቶ በላይ እንደሚያድግ መረጃዎች ይጠቁማሉ። በተለይም ሀገሪቱ በበርካታ ውስብስብ ችግሮች ውስጥ ባለችበት በዚህ ወቅት ይህን መሰል ዕድገት ማስመዘግብ መቻሏ እንደ ሀገር ጠንካራ ስራ መሰራቱን የሚያመላክት ነው ። 45 በመቶ የሚሆነው የሀገሪቱ ክፍል በጦርነትና በጸጥታ ችግር ውስጥ ሆኖ በቆየበት ወቅት ከ6 በመቶ በላይ የኢኮኖሚ ዕድገት ማስመዝገብ መቻሉ ከለውጡ ወዲህ የተቀየሱ የኢኮኖሚ ፖሊሲዎችና ስትራቴጂዎች ውጤታማ መሆናቸውን የሚያመላክት ነው።

በተጠናቀቀው የበጀት አመት ኢትዮጵያ በታሪኳ አይታ የማታውቀውን ከወጭ ንግድ ከ4 ቢሊዮን ዶላር በላይ አግኝታለች።በአጠቃላይም ከአገልግሎት ዘርፉና ወደ ውጭ ከተላኩ ምርቶች ከ10 ቢሊዮን ዶላር በላይ ገቢ ተገኝቷል። በዚህ ላይ በውጭ ከሚኖሩ ኢትዮጳውያውያንና ትውልደ ኢትዮጵያውያን እንዲሁም ከቀጥታ ኢንቨስትመንት የተገኘው ገቢ ሲታከልበት ኢትዮጵያ በበጀት አመቱ ያገኘችው ገቢ ከ20 ቢሊዮን ዶላር በላይ ይዘላል።

ይህ የገቢ መጠን ቀደም ባሉት ጊዚያት ፈጽሞ የሚታሰብ አልነበረም። ሀገሪቱ ፍጹም ሰላም በነበረችባቸው ዓመታት እንኳን ከወጭ ንግድ ሲገኝ የነበረው አመታዊ ገቢ ከ3 ነጥብ 2 ቢሊዮን ዶላር ዘሎ አያውቅም። ከ2003 እስከ 2008 በነበሩት ዓመታትም የሀገሪቱ የወጪ ንገድ ገቢ በየአመቱ በ0 ነጥብ 3 በመቶ እያሽቆለቆለ ሄዶ ሀገሪቱ አጣብቂኝ ውስጥ ገብታ ቆይታለች።

ከ2009 ዓ.ም በኋላ ተግባራዊ መደረግ የጀመረው ሀገር በቀል የኢኮኖሚ ፖሊሲ ኢትዮጵያ ያሏትን ሃብቶች እንድታጤንና ለውጭ ገበያም በስፋት እንድታቀርብ ዕድል በመክፈቱ የወጪ ንግድ ከገባበት ቅርቃር ተላቆ በየዓመቱ በ16 በመቶ ዕድገት የሚያስመዘግብበት አዲስ ምዕራፍ ውስጥ ተገብቷል።

ቡናን የመሳሰሉ በሀገሪቱን የውጭ ንግድ ውስጥ ጉልህ ድርሻ ላላቸው ዘርፎች ትኩረት በመስጠትና በተለይም ረጅም የነበረውን የገበያ ሰንሰለት በማሳጠርና ምርቱን በኮንቴነር አሸጎ መላክ በመቻሉ ለገቢው ማደግ የበኩሉን አስተዋጽኦ አበርክቷል። ሌላው ሀገር በቀል ኢኮኖሚው ካነቃቃቸውና በተጨባጭም ለውጥ ከታየባቸው ዘርፎች አንዱ የማዕድን ዘርፍ ሲሆን በዓመት በአማካይ የ700 በመቶ ዕድገት በማስመዝገብ የወጪ ንግዱ ላይ የራሱን አዎንታዊ አስተዋጽኦ ማበርከት ችሏል።

በአጠቃላይ በ2014 በጀት አመት የተመዘገበው አበረታች የወጪ ንግድ አፈጻጸምና ቀጥታ የውጪ መዋዕለ ንዋይ ፍሰት አበረታች ነው። የወጪ ንግድ ማደግም የሌሎችን ዘርፎች ማደግ ስለሚያፋጥንና ሀገሪቱ ለተያያዘቸው ሃገር በቀል ኢኮኖሚ ውጤታማነትና ወደ ኢንዱስትሪ ለሚደረገው መዋቅራዊ ሽግግር መሰረት እየተጣለ መሆኑን የሚያመላክት ነው። ከወጪ ንግድ የሚገኘው ገቢ ባደገ ቁጥርም የገንዘብ እጥረት ማነቆ ለሆነባቸው ግብርናን ለመሳሰሉ ዘርፎች ዕድገትም መልካም የሆነ ዕድልን ይዞ ይመጣል።

ኢትዮጵያ በ2014 ከወጭ ንግድ፤ከቀጥታ ኢንቨስትመን፤ በውጭ ከሚኖሩ ኢትዮጵያውያን ከተላከ ብርና ከአገልግሎት ዘርፉ የተገኘው ከ20 ቢሊዮን ዶላር ገቢ ከፍተኛ የሚባል ቢሆንም ሀገሪቱ ካላት እምቅ አቅም አንጻር ግን ከዚህም በላይ በርካታ እጥፍ ገቢ ማግኘት እንደሚቻል የዘርፉ ምሁራን ይመክራሉ። ሀገሪቱ ከወጪ ንግድ ካገኘችው ገቢ ውስጥ ከ70 በመቶ በላይ የተገኘው ከግብርናው ዘርፍ ነው። ይህ አቅም በአምራች ኢንዱስትሪው እየተተካ ሲሄድ ከዚህ ብዙ እጥፍ ገቢ ለሀገሪቱ እንደሚያስገኝላት የታመነ ነው። ከአገልግሎት ዘርፉ የተገኘው ገቢም በአብዛኛው ከኢትዮጵያ አየር መንገድ ጋር የተያያዘ ነው። ሌሎች የአገልግሎት ዘርፎችን የበለጠ ማዘመን ከተቻለ ሀገሪቱን ካለባት የውጭ ምንዛሬ እጥረት በቀላሉ ማላቀቅ ይቻላል።

ሌላኛው ማነቆ ደግሞ እየተስተዋለ ያለው በሁለት ዲጂት እየተቆጠረ ያለው ከፍተኛ የዋጋ ግሽበት ነው። የዜጎችን ገቢ በማመናመን ለከፍተኛ ምሬት እየዳረገ ያለው የዋጋ ግሽበት ባለፉት ሁለት ወራት መጠነኛ ቅናሽ ቢያሳይም አሁንም የሀገሪቱ ፈተና ሆኖ ቀጥሏል። ይህንኑ ማነቆ ለመፍታትም መንግስት የዋጋ ግሽበቱን በአጭር ጊዜ ወደ ነጠላ አኃዝ በማውረድ በአዲሱ በጀት ዓመት ወደ 11 ነጥብ 9 በመቶ ለማድረስ ዕቅድ የያዘ ሲሆን ዕቅዱ በአግባቡ ወደ መሬት የሚወርድ ከሆነ ኢኮኖሚው ማመንጨት የጀመረው ገቢ ወደ ዜጎች ኪስ ገብቶ ተጨባጭ ለውጥ የሚታይበት ጊዜ ሩቅ አይሆንም።

በ2014 የተመዘገበው የማክሮ ኢኮኖሚ ዕድገትም በቀጣዩ አመት የበለጠ ጎልብቶ ለሀገሪቱ ሁለንተናዊ እድገት የበኩሉን አስተዋጽኦ እንዲያበረክት የሚመለከታቸው አካላት ሁሉ ከወዲሁ ተግተው ሊሰሩ ይገባል!


እኢፕድ

# አዲስ ዘመን

ግንቦት 30 ቀን 1933 ዓ.ም ተቋቋመ

**የኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት ዋና ስራ አስኪያጅ**

ስልክ ቁጥር - 011-126-42-22

**ዋና አዘጋጅ**

አንተነህ ኃ/ብርሃን ወ/መድህን

**አድራሻ**

ንፋስ ስልክ ላፍቶ ክ/ከ

ወረዳ 06

የቤት ቁጥር 319

ኢሜይል - anteneh.hailebirhan@press.et

ስልክ ቁጥር - 011-1-26-42-40

**የአዲስ ዘመን ማኔጂንግ ኤዲተር**

ወንድወሰን ሽመልስ ታደሰ

ስልክ፡- 011 126 4240

Email:- wendweson.shimelis@press.et
wendwesonshimelis@gmail.com

**የአዲስ ዘመን ምክትል ዋና አዘጋጆች**

- ወርቁ ማሩ
- ኃይሉ ሣህለድንግል
- አልማዝ አያሌው
- እስማኤል አረቦ

**የገበያ ልማትና ፕሮሞሽን ዘርፍ**

ኢሜይል - etpresspromotion@gmail.com

ስልክ - 011-126-43-41

ፋክስ - 011-811-13-15

**የማስታወቂያ መቀበያ ክፍል**

ስልክ ቁጥር - 011-156-98-73

ፋክስ - 011-126-58-12

**የማስታወቂያ ሽያጭ ማስተባበሪያ**

ስልክ - 011-1-26-43-39

**ማከፋፈያ**

ስልክ ቁጥር - 011-157-02-70


**ነፃ ሃሳብ**

**ይህ አምድ በተለያዩ ፖለቲካዊ ኢኮኖሚያዊና ማህበራዊ ጉዳዮች ዙሪያ ዜጎች ነፃ ሀሳባቸውን የሚሰጡበት ነው፡፡ በዓምዱ ላይ የሚወጡ ጽሁፎች የዝግጅት ክፍሉን አቋም አያመለክቱም፡፡**

# ጨዋታው አይፍረስ - ዳቦውም አይቆረስ፤

**ከትዝታ ማስታወሻ**

ያኔ በልጅነት አንድ አይነት ባህሪ አለን ብለን ያመንን የሰፈር ህጻናት በራሳችን ተነሳሽነት ላወጣናቸው ህጎችም ሆነ ከታላላቆቻችን የወረስነውን የጨዋታ ደንብ ለመከተል ተስማምተን ጨዋታው ይጀመራል። በዛ አቅማችን ከመሃላችን ህግና ደንቡን ተከትሎ ጨዋታውን ያልተጫወተ አካል ካለ ውሳኔያችን የሚሆነው ጨዋታው ፈረሰ ዳቦ ተቆረሰ በማለት ጨዋታውን ሳንጠግብ ወደየቤታችን መግባት ነበር። ምናልባት ረባሹ ከመሃል አንድ ልጅ ብቻ ሊሆን ይችላል።

ያኔ የልጅነት ነገር ነውና ከመሃል አንድም ልጅ በመነጋገር ችግሩን ፈቶ ወደ ጨዋታችን እንድንመለስ የሚያደርግ አልነበረም። ታዲያ ይሄን ያለፈ ልጅነቴን ያስታወሰኝ የአሁኑ የሀገሬ ሁኔታ ነው። ምክንያቱም ጦርነት አልነው፤ ራስን የመከላከል ዘመቻም ሆነ፣ ባህላዊ ጨዋታ ብለን ብንሰይመው፤ በአጀማመሩም ሆነ በሂደቱ ምንም አስተዋጽኦ ያልነበራቸው አካላት ከመጠን በላይ የተጎዱበት በመሆኑ ነው።

ስለልጅነት ጸብና እርቅ ሳስብ ሁልጊዜ የማልረሳው የእኔና እኩያዬ ጸብ ነው። በመሃላችን ወር ያልሞላ የእድሜ ልዩነት ከመኖሩ በላይ አንድ አጥር የምንጋራ በመሆናችን በአካልም በመንፈስም ቅርብ ነን። ግን ምን ዋጋ አለው ለፍቅር ብቻ ሳይሆን ለጸብም ቅርብ ነን። መጣላት ካሻን ምክንያት አናጣም፤ እራሳችን ጋር ሰበብ ካለቀብን ካንቺ አባት ይልቅ የኔ አባት ጀግና ነው በሚል የለየለት ድብድብ ውስጥ እንገባለን። በዛው ልክ በፍቅራችን ጊዜም በአንድ ነጠላ ካላስቀደስን የምንል ነን።

ታዲያ ይሄ በረባውም ባልረባውም የሚያጣላ ፍቅር አይሉት ጥላቻ የመረራት የጋደኛዬ እናት አንድ ቀን ለሽምግልና በተቀመጠችበት አንድ ነገር አለችን። አትታረቁ፤ እኔ የሰለቸኝ እናንተን ማስታረቅ ነው። አስታርቄ ሳልጨርስ ለሁለተኛ የጥል ስሞታ እየመጣችሁ ስለተቸገርኩ አትታረቁ እንዲሁ እንደተጣላችሁ ሳትደራረሱ በሰላም ኑሩ ብላ ሸኘችን። እውነት እንዳለችውም ለተወሰነ ጊዜ በጥል ውስጥ በሠላም ሰነበትን፤ ተጣልቶ አይቀርምና አላስታራቂ በቀጥታ ስንታረቅ በቀጣይ ሽምጋይ እንደሌለ አስቀድመን ስላወቅን እስካሁን በወዳጅነታችን አለን።

የሀገራችንም ሁኔታም ይሕ ይመስለኛል። ሀገር፣ በወንድማማቾች መሃል ደም መፋሰስ ሲሆን ሃይ ባይ ገላጋይ ዳኛ ትሻለች። ሆኖም በእኛ ሀገር ሁኔታ እንዲያስታርቋት ተስፋ ያሳደርንባቸው የሀይማኖት አባቶች ሳይቀሩ እርስ በእርስ እየተሻኮቱ በተቃራኒው ፖለቲከኞች ሊያስማሙ እላይ ታች ሲሉ ማየት እየተለመደ መጣ። ይባስ ብሎ ቤተ እምነቶች የፖለቲካውን ጎራ ተከትለው ቀድመው ራሳቸውን ራስ ገዝ ሲያደርጉ ዝም ብሎ መስማትና ማየት እጣችን ሆነ። ይሄን አይነት አካሄድና ሌላውም ጉዳይ ተደማምሮም በክርስትናውም ሆነ በእስልምናው የእምነት ተቋማት በኩል ከውስጥ ጉዳያቸው በዘለለ አገራዊ ችግሩን ለመፍታት የሚደረገው ጥረት እምብዛም ሆኖ አልታየም።

እናም ተው ልጆቼ የሚል የሀገር ሽማግሌም ሆነ የሃይማኖት አባት በጠፋበት ጊዜ በፌዴራሉ መንግስት ተደጋጋሚና ያለመሰልቸት ጥረት ሁለቱም ወገኖች ቆርጠው ለሰላም ውይይት ዝግጁ መሆናቸው ለዜጎች ተስፋን ያጫረ ሆኗል። የኔ ስጋት ግን ግርግር ለሌባ ይመቻል እንዲሉ፤ ሀገር ሰላም ባለመሆኗ የእነሱ ኪስ የሞላ ራስ ወዳድ ግለሰቦች ቁጥር ቀላል ባለመሆኑ ይሄን ኪሳቸውን ላለማድረቅ ሲሉ ሂደቱን እንዳያደናቅፉት የሚል ነው። በቅርቡ ወደ ትግራይ ክልል በህገ ወጥ መልኩ ሊገባ ሲል የተያዘው ከስምንት ነጥብ ስምንት ሚልየን ብር በላይ በጦርነት ወቅት የማትረፍ ሂደት አንዱ ማሳያ ነው።

ይህ ብቻ አይደለም የተፈጠረው ችግር በሰዎች መቸገር ውስጥ ጥቅማቸውን ለሚያሰሉ ደላሎችም ከፍ ያለ እንጀራን ይዞ የደረሰላቸው የመስላል። ምክንያቱም ዘመዶቻቸው በትግራይ ክልል የሚገኙ ዜጎች ካላቸው ቀንሰው ለዘመዶቼ ለማድረስ ቢፈልጉ ሳይወዱ ህገወጥ ገንዘብ አዘዋዋሪዎችን በር መርገጥ ግዴታ ሆኗል። በዚህ የተነሳም በርካቶች ተቸግረው ከሌላቸው ለወገኔ ልድረስ ሲሉ እስከ 40 በመቶ ኮሚሽን የሚቀበሉ የእኛው ወገኖች ተፈጥረዋል።

ታዲያ ሰላም ቢሰፍን ባንክ ቢከፈት ይሄ ሁሉ ብር ወገናቸውን እያስለቀሱ መሰብሰብ የለመዱ ሰዎች በቀላሉ የሥራ መስካቸው ሲዘጋ ደስ የሚሰኙም አይመስለኝም። በማወቅም ባለማወቅም አንዱን ወገን ደግፈው ሌላውን ነቅፈው ሲተቹ የነበሩ ሰዎችም የበምን ይመጣብኛል ፍራቻ ሰላም መሆንን ሊፈሩ ይችላሉ። ይሄ ሁሉ ለችግሩ ገፈት ቀማሽ የሀገር ልጆች ስቃይን እንጂ እፎይታን የሚሰጥ አይደለም፤ የተነጣጠሉ እናትና ልጆችን ለማገናኘት ለሚደረግ የሰላም ጥረት ተጨማሪ እንቅፋት እንጂ መፍትሄ አላስገኘም፤ አያስገኝምም። በእነዚህ ቡድኖች የሰላም ገፊነት ምክንያት በዓለም አደባባይ በድል የነገሱ ኢትዮጵያዊ የትግራይ ልጆች እናቴ አሸነፍኩልሽ ብሎ የደስታቸው ተካፋይ ለመሆን ሲናፍቁ ማየት ያማል። በድል ላይ ሌላ ድል በሽልማት ላይ ሌላ ሽልማት ተይዞ፤ ለተቸገረ ቤተሰብ ማካፈል አለመቻል የመኖር ትርጉሙ እስኪዛባ ድረስ ግራ ያጋባል።

አብዛኛው ህዝባችን ዘንድሮን ሳላርስ ለከርሞ ምን ልበላ ብሎ ቢሰቃይም፤ የተወሰነው ለሰብአዊ ርዳታ ተብሎ በነጻ የገባን እርዳታ ከመሸጥ ጀምሮ ብዙ አትርፏል። ታዲያ ይህ ኃይል እንዴት ከጦርነት ይልቅ ስለ ሰላም አስቦ ሊሰራ ይችላል? በየቦታው ለተቸገሩ እርዳታ እናደርሳለን በሚል የት እንደገባ የማይታወቁ በርካታ ብሮችና የአይነት ድጋፎች ተሰብስበዋል። ሆኖም ዛሬም የብዙዎች ሕይወት ተጎሳቁሏል። በርካቶች የጀመሩት ህክምና ተቋርጧል፤ የነገ ተስፋዎቻቸው የሆኑ ልጆቻቸውን አጥተዋል። በአንጻሩ በብዙሃኑ መጎሳቆል ውስጥ የተወሰኑ ግለሰቦች ሕይወት ተደላድሏል።

በመሆኑም በዚህ ጦርነት አትራፊ የሆኑ ቡድኖችና ግለሰቦች የሰላም ንግግር ሂደቱን እንዳያደናቅፉት ስጋቴ ነው። ስለዚህ ተወያይ ወገኖች ህዝብን ያስቀደመ ውይይት እንድታደርጉ አደራ እላለሁ። ለዚህም መፍትሄው በመነጋገርና በመተማመን ወደ ጋራ መፍትሄ መሄድ እንጂ ገና ሳይጀመር ይሄ ጉዳይ ሳይፈታ አንደራደርም በማለት በቅድመ ሁኔታ ሊሆን አይገባም። እናንተ ፖለቲከኞች የምትመሩት ሕዝብ ከጦርነት ምንም አላተረፈም፤ ወደፊትም አያተርፍም። ይህንን እውነታ መቀበል ካቃታችሁና የሰላም ውይይቱ በእኔ በልጥ እኔ በልጥ ስሜት ከተደረገ፤ የሰላም ውይይት መሆኑ ቀርቶ ጨዋታው ፈረሰ ዳቦ ተቆረሰ የሚባልበት ቀን ሩቅ አይሆንም። ያኔ ማንም አሸናፊ ሳይኖር በርካታ ተሸናፊዎች ይፈጠራሉ። ስለዚህ ጨዋታው አይፍረስ ዳቦውም አይቆረስ፤ ችግሮቻችንንም በንግግር መፍታት እንለምድ።

ፖለቲካ እና ልዩ ልዩ

# ነፃ ሃሳብ

# የሕወሓት የሰላም ውይይት «ፎብያ»

**ሙሉቀን ታደገ**

በቡድኖች ወይም በግለሰቦች መካከል የሚደረጉ ግጭቶች ወይም አለመግባባቶች ሁለት ነገሮችን ይዘው ሊመጡ እንደሚችሉ በመስኩ ጥናት ያደረጉ ምሁራን ይናገራሉ። አንደኛው አወንታዊ (ጥሩ ዕድል ) ሲሆን፤ ሌላኛው ደግሞ አሉታዊ (መጥፎ እና አጥፊ አጋጣሚዎችን) ነው:: ግጭትም በዚህ መልኩ የሚገለጹ መንታ ገጾችን የተላበሰ ሲሆን፤ ሊታወቅ የሚገባው አንኳር ጉዳይ ግን ግጭቱ ወይም አለመግባባቱ በአጭሩ ካልተቀጨ እጅግ ለማሰብ የሚከብዱ አውዳሚ ጦርነቶችን የሚፈጥር መሆኑ ነው:: ይሄንንም በዚሁ በአገራችን ተመልክተናል:: ነገር ግን በግጭቶች ሳቢያ የሚከሰቱ የትኛውንም ዓይነት አውዳሚ ጦርነቶች መደምደሚያቸው ቁጭ ብሎ መነጋገር፣ መወያየት በመጨረሻም ከስምምነት መድረስ ነው::

በርካታ የፖለቲካ ጠበብት በተለያዩ ጥናቶቻቸው ላይ እንዳመላከቱት፣ በሁለት ኃይሎች መካከል የሚፈጠርን አለመግባባት ወይም ግጭት ለማስቆም የሚደረጉ የውይይትና ድርድር ዓይነቶች በርካታ ናቸው:: እነኙህን የውይይትና ድርድር ዓይነቶች መቼ፣ በምን ሁኔታዎች ላይ እንጠቀማቸዋለን የሚለው እና የሚያስከትሏቸው ውጤቶች በተወያይና ተደራዳሪዎቹ ወቅታዊ አቋም እና ጥንካሬ የሚወሰን ነው:: ከተወያዮቹ ወይም ከተደራዳሪዎቹ አንዱ ጠንካራ ከሆነ፤ ጠንካራ የሆነው ተደራዳሪ ከግጭቱ ወይም በጦርነቱ ከተሸነፈው ወገን የተሻለ ጥቅም እንዲያገኝ በድርድሩ ላይ ጫና ስለሚያሳደር፤ በሚደረገው ውይይትና ድርድር ሂደት ብዙውን ጊዜ የተሻለ ጥቅም እንደሚያገኝ ይታመናል:: በአንጻሩ በግጭቱ የተሸነፈው አካል ህልውናው ከነጭራሹ እንዳይጠፋ በማሰብ በርካታ ጥቅሞችን እያጣ መሆኑን እያወቀም ለውይይትና ድርድር ይቀመጣል:: በውይይትና ድርድሩም ሳይወድ በግድ ይስማማል።

ለዚህም በናፖሊዮን ቦና ፓርት ዘመን የተሸነፈችው ፈረንሳይ በ1815 እ.ኤ.አ በተካሄደው በቬናው ጉባኤ ያጣቻቸው ግዛቶች እና ጥቅማ ጥቅሞች የሚታወቁ ናቸው። በዚህ ጉባኤ የተደረገው ድርድር ፈረንሳይ ከጦርነቱ በፊት በኃይል ይዛቻው የነበሩ የበርካታ አገራትን ግዛቶች እንድትለቅ በማድረጉ የአውሮፓ ካርታ እንደገና እንዲዋቀር እስከማድረግ የደረሰ የውሳኔ ስምምነት የተደረሰበት ነበር።

በጦርነት የአሸነፈ አካል በጦርነት የተሸነፈን አካል በድርድር ወቅት ከሚያገኛቸው ጥቅሞች የተሻሉ ስለመሆናቸው ሌላው ማሳያ ደግሞ በአንደኛው እና በሁለተኛው የዓለም ጦርነት የተሸነፉት ጀርመን እና አጋሮቿ በድርድር ሰበብ የተወሰነባቸውን ውሳኔ ብቻ ማየቱ በቂ ነው። ጀርመን እና አጋሮቿ በድርድር ሰበብ በጣም በርካታ ግዛቶችን ከማጣታቸውም በላይ እንዲከፍሉ የተወሰነባቸው የጦርነት ካሳ እጅጉን ከፍተኛ ነበር። ለዚህ ያበቃቸው ደግሞ በጦርነት ተሸነፍው ለድርድር በመብቃታቸው ነበር:: ጀርመን እና አጋሮቿ በርካታ ብሔራዊ ጥቅሞቻቸውን ቢያጡም በአሸነፊዎች ወገን ከነጭራሹ ከመጥፋታቸው በፊት የተጣለባቸውን ውሳኔ መቀበል የግድ ስለነበር ተቀብለውታል።

አንድ አንድ ጊዜም ሁለት በጉልበት ተመጣጣኝ ኃይሎች ከጦርነት በኋላ የሚያደርጉት ድርድር Collaborating ወይም ሁለቱም ኃይሎች ጥቅማቸውን የሚያስከብሩበት እና በተመሳሳይ ሁለቱም የሚያሸንፉበት ድርድር ይሆናል:: ይህ ማለት ግን ሁልጊዜም በጦርነት ያሸነፈ ወገን በድርድር የተሻለ ዋጋ ይኖረዋል ማለት ግን አይደለም። የዓለም ታሪክም የሚያሳየው ይህን እውነታ ነው::

ሰላም ለአንድ አገር እድገት የማይተካ ሚና እንዳለው ማስረዳት ሙቅ እንደማላመጥ ይቆጠራል:: በአንድ አገር ሰላም ለማምጣት መሪና ተመሪው ኃይል በርካታ ማይሎችን መጓዝ ይጠበቅባቸዋል:: በርካታ ማይሎችን መጓዙ ብቻውን በቂ ስላልሆነ የታሰበውን ሰላም በአንድ አገር ለማምጣት በበርካታ አድካሚ ማይሎች ጉዞ ውስጥ የጉዟችንን እያንዳንዱን እርምጃ በጥበብ መራመድ እንዳለብን የሚያሳይ ጥበበኛ መሪ እና በትዕግስት መሪውን የሚከተል ሕዝብም ያስፈልጋል:: ጥበበኛ መሪ ሰላምን ለማምጣት ከሚያደርጋቸው ጉዞዎች መካከል ውይይት ወይም ድርድር አንዱ ነው:: ምክንያቱም ሁሉንም ችግሮች በጉልበት መፍታት የሚጠበቀውን ውጤት ሊያመጣ አይችልም። እናም አንድ አገር የትኛውንም ያህል ጉልበት ቢኖራት ብሔራዊ ጥቅሟን ለማሟላት ሁልጊዜ ጉልበትን እንደ አማራጭ አትወስድም:: መውሰድም የለባትም::

በነገራችን ላይ በዓለም ላይ የሚገኙ አገራት ሁነኛ የአገራቸውን ፖሊሲ እና ስትራቴጂ የቀረጹት ከግጭት ማግስት ካደረጓቸው ስምምነቶች ወይም ድርድሮችን እንደመነሻ ተጠቅመው መሆኑን የፖለቲካ እና የታሪክ ምሁራን ያስረዳሉ። (major public policies are the outcome of a complex round of negotiation between interests, choices between values and competition between resources) ... there are no single 'best' options for any player in this game, for the 'best' outcome depends on what others do and what deals are possible.")። ይህ የሆነው ደግሞ አገራቱ ከውጭም ሆነ ከውስጥ ኃይሎች ጋር ያላቸውን ግጭት መነሻ አድርገው በሚደርሱት በሚከውኑት ውይይትና ድርድር እንዲሁም በሚደርሱት ስምምነት መሠረት ነው::

ኢትዮጵያም ዛሬ በውስጥ የገጠማትን ችግር በውይይት ተነጋግሮ በሰላም ለመፍታት እየሠራች ትገኛለች:: ይሁን እንጂ ሰላምን እንደጦር ወይም አውዳሚ ቦምብ አጥብቆ የሚፈራው ሕወሓት፤ የኢትዮጵያ መንግሥት ብዙ ሺህ ማይሎችን ተጉዞ ለሰላም እጁን ቢዘረጋም የተፈጠረውን ችግር በውይይትና ምክክር ለመፍታት የሚያሳየው

> ውይይትና ድርድር ሲካሄድ ሲቀመጡ የሚገባቸው በርካታ ቅድመ ሁኔታዎች ሲኖሩ ይችላሉ:: ይሁን እንጂ ሕወሓት ከጅምሩም ወደ ውይይት እመጣለሁ ያለው ለሰላም አልወያይም አለ ተብሎ ዓለም አቀፍ ጫናዎች እንዳይደርሱበት በማሰብ ነው:: ለዚህም ነው ተደጋጋሚ በመንግሥት በኩል የተደረጉ የሰላም ጥረቶችና ጥሪዎች በቡድኑ በኩል በቅድመ ሁኔታና እንቢታ ምክንያት ሳይሳኩ የቆዩት:: አሁንም ቢሆን ሕወሓት ለውይይት ዝግጁ ነኝ ይበል እንጂ ለውይይት ከሚያደርጋቸው ዝግጅቶች ይልቅ አደናቃፊ ቅድመ ሁኔታዎችን በመደርደር ተጠምዶ ይታያል:: ምክንያቱም ምሁራን እንደሚስማሙበት ውይይት ወይም ድርድር የሚያደርጉ አካላት ከውይይት በፊት ሊያደርጓቸው የሚገቡ አራት ደረጃዎች አሉ:: እነዚህም ግንዛቤ (awareness)፣ ራስን ማዘጋጀት (self-preparation)፣ ግጭት ቅነሳ (confiict reduction) and ስምምነት (negotiation) የሚባሉት ናቸው

ቁርጠኝነት እጅጉን የላላ ነው። በኢትዮጵያ መንግሥት ልክ ለሰላም ብዙ ማይሎችን መሄድ ባይችል እንኳን ለሰላም ብዙ ማይሎችን ተጉዞ ችግሮችን በውይይት ለመፍታት የሚፈለግን አካል ድካም ከምንም ባለመቁጠር በዚህ ልክ በድርድር መንገዱ ላይ የቅድመ ሁኔታ ጋሬጣዎችን በመደርድር አገሪቱ ሰላም እንዳትሆን አበክሮ መሥራት ምን የሚሉት «ግብፀኝነት» እና ግበተኝነት ነው?

በእርግጥ ውይይትና ድርድር ሲካሄድ ሊቀመጡ የሚገባቸው በርካታ ቅድመ ሁኔታዎች ሊኖሩ ይችላሉ:: ይሁን እንጂ ሕወሓት ከጅምሩም ወደ ውይይት እመጣለሁ ያለው ለሰላም አልወያይም አለ ተብሎ ዓለም አቀፍ ጫናዎች እንዳይደርሱበት በማሰብ ነው:: ለዚህም ነው ተደጋጋሚ በመንግሥት በኩል የተደረጉ የሰላም ጥረቶችና ጥሪዎች በቡድኑ በኩል በቅድመ ሁኔታና እንቢታ ምክንያት ሳይሳኩ የቆዩት:: አሁንም ቢሆን ሕወሓት ለውይይት ዝግጁ ነኝ ይበል እንጂ ለውይይት ከሚያደርጋቸው ዝግጅቶች ይልቅ አደናቃፊ ቅድመ ሁኔታዎችን በመደርደር ተጠምዶ ይታያል:: ምክንያቱም ምሁራን እንደሚስማሙበት ውይይት ወይም ድርድር የሚያደርጉ አካላት ከውይይት በፊት ሊያደርጓቸው የሚገቡ አራት ደረጃዎች አሉ:: እነዚህም ግንዛቤ (awareness)፣ ራስን ማዘጋጀት (self-preparation)፣ ግጭት ቅነሳ (conflict reduction) and ስምምነት (negotiation) የሚባሉት ናቸው። ሕወሓትም ውይይት ለማድረግ ያለውን ቁርጠኝነት ለመገምገም ይቻል ዘንድ እነኙህን አራት ቀድመ ሁኔታዎች ከእርሱ ባህሪ አኳያ አንድ ባንድ ማየቱ ተገቢ ነው::

የውይይት/ድርድር የመጀመሪያው ደረጃ ግንዛቤ (awareness) የሚባለው ነው:: ከዚህ አኳያ ሕወሓት ስለ ውይይት/ድርድር ያለው ግንዛቤ ከልጅነቱ ጀምሮ ውይይትንና ቁጭ ብሎ ስለ ሰላም ማውራትን እንደ ፍርሃት የሚቆጠር ነው:: ይህ እንደተጠበቀ ሆኖ ግን ሕወሓት አንድ አንድ ጊዜ ውይይት/ድርድርን ለማጥፋት ዝግጅት እንደ ጊዜ መግዣ ሲጠቀምበት ነው የሚታወቀው:: ከዚህ ውጪ ከውይይትና ድርድር ፖሊሲዎችን እና ስትራቴጂዎችን መንደፍ የሚችል አቅም ሆነ ሞራል የሌላቸው የግብተኞች ስብስብ ነው::

ለዚህ እንደማሳያ አንድ ምሳሌ ላስታውሳችሁ፡- ሕወሓት የጨረቃ ምርጫ ከማድረጉ እና በመከላከያ ላይ ጥቃት ከመፈጸሙ በፊት በአገራችን «ዝናብ የሚያፍራቸው» አንቱ የተባሉ የአገር ሽማግሌዎችን መንግሥት መቀሌ ድረስ ልኮ ቢያስለምነው ለሰላም መለመንን እንደ ፍርሃት የሚቆጥረው ወያኔ እንኳንስ የሰላም ጥሪውን ሊቀበል ይቅርና ከኢትዮጵያ ባህል በፈነገጠ አኳኋን ለሽምግልና የተላኩ ሰዎችን ጦርነት በመጠማታቸው ወታደሮቹን በማስፈትሸ እና ክብራቸውን ዝቅ በማድረግ ሽማግሌዎችን አዋረደ::

ሌላው እና ሁለተኛው የሰላም ውይይት ደረጃ ራስን ማዘጋጀት (self-preparation) የሚባለው ነው:: ከዚህ አንጻር መጀመሪያውኑ ውይይትና ድርድርን እንደፍርሃት የሚቆጠር ድርጅት እንዴት ሆኖ ራሱን ለሰላም ውይይት ሊያዘጋጅ ይችላል? ሕወሓት ራሱን ለሰላም ውይይቱ እንዳላዘጋጀ ከምንመለከትባቸው መነጽሮች አንዱ ከውይይቱ በፊት የኢትዮጵያ መንግሥት ሊያሟላቸው የሚገባቸው ነገሮች ብሎ ያስቀመጣቸው ቅድመ ሁኔታዎች ናቸው:: እነኙህ ቅድመ ሁኔታዎች በውይይት የሚፈቱ ሆነው ሳለ፤ ሕወሓት ሆነ ብሎ የሰላም ውይይቱን ለማጨናገፍ በማሰብ ቅድመ ሁኔታዎችን በማስቀመጥ እነኙህ ቅድመ ሁኔታዎች ካልተሟሉ ውይይትን አታስቡት፤ በቅርቡ ጦርነት እከፍታለሁ እያለ የሚታወቅበትን የጦርነት ነጋሪት እየጎሰመ ነው:: የሽብር ቡድኑ ለድርድር ዝግጁ አለመሆኑን ዓለም አቀፉ ማኅበረሰብም በተግባር እያየ ነው::

ለምሳሌ፣ ነዳጅ ወደ ክልሉ እየገባ ቢሆንም፤ ምንም ነዳጅ እየገባ እንዳልሆነ በማስመሰል እና የዓለም አቀፉን ማኅበረሰብ ለማታለል በማሰብ ነዳጅ አልገባልንም፤ ስለዚህ ቁጭ ብለን ስለሰላም ለመነጋገር እንቸገራለን ሲል ይደመጣል:: ይሄንና መሰል ቅድመ ሁኔታዎች ካልተሟሉ አይደለም ቁጭ ብዬ ስለሰላም ልወያይ በቅርብ ጊዜ ውጊያ እከፍታለሁ እያለ ነጋሪት ይጎስማል::

በሦስተኝነት የሚጠቀሰው ቅድመ ውይይት/ድርድር ዝግጅት ደግሞ ግጭት ሊያባብሱ ከሚችሉ ነገሮች ራስን መገደብ (conflict reduction) የተሰኘው ነው። ከዚህ አንጻር ሕወሓት የሚያደርገውን ለተመለከተ ስለ ሰላም ቁጭ ብሎ መወያየትን አንድም ቀን አስቦ የማያውቅ መሆኑን በግልጽ አሳይቷል:: በአፈ ቀላጤዎቹ እና የጥፋት ቡድኑ መሪዎች በየቀኑ ከሚሰጣቸው መግለጫዎች ባለፈ በተለያዩ የአገሪቱ ክፍሎች ራሱን አስመስሎ በፈለፈላቸው የጥፋት እሳት ተሸካሚ ፈረሶች አማካኝነት የሚያደርጋቸው ጥፋቶች ኢትዮጵያውያንን ምን ያህል እንዳቆሰሉ የሚታወቅ ነው::

ከዚህ ባለፈም ግጭት ሊያባብሱ ከሚችሉ ነገሮች ራስን ከመገደብ አኳያ ስለ ሰላም ለመነጋገር ለአፍታም አስቦበት እንደማያውቅ ሁነኛ ማሳያው ደግሞ የትግራይ ክልል አዋሳኝ በሆኑት የአማራ እና የአፋር ክልሎች ከሚያደርጋቸው ትንኮሳዎች በተጨማሪ በቤኒሻንጉል፣ በወለጋ እና ሌሎች አካባቢዎች በወኪሎቹ አማካኝነት በዜጎች ላይ የሚያደርሰው አሳዛኝ የሆነ ጭፍጨፋ ነው:: በዚህም የሽብር ቡድኑ ሦስተኛውን የውይይት/ድርድር ቅደመ ሁኔታ ቀረጣጥፎ መብላቱን፤ ስለሰላም ለመነጋገርም ዝግጅት የሌለው ስለመሆኑ አሳይቶናል::

የመጨረሻው እና አራተኛው ደረጃ ደግሞ (negotiation) የሚባለው ነው። አራተኛው ደረጃ ላይ ለመድረስ መጀመሪያ ያሉትን ሦስት ደረጃዎች አምኖ መቀበል ይጠይቃል። የሽብር ቡድኑ ግን የሰላም ውይይትን እንደ አውዳሚ ቦምብ ፈርቶ የሚይዘውን የሚጨብጠውን አጥቶ እየተርመጠመጠ ይገኛል። ይሄንን ከሚያረጋግጡልን ተጨማሪ ማሳያዎች መካከል ደግሞ ውይይቱን የሚመሩት አካላት እኔ ያልኳቸው ብቻ ካልሆኑ ለውይይት አልቀርብም እያለ በየአጋጣሚው የሚያስተጋባው ጩኸት ነው::

እንደሚታወቀው በርካታ ዓይነት የግጭት ማቆሚያ ስልቶች አሉ:: አንደኛው negotiation የሚባለው ሲሆን፤ በዚህም የሦስተኛ ወገን ጣልቃገብነት ሳይኖር ሁለቱ የተጣሉ ወገኖች ብቻ እርስ በራሳቸው በመነጋገር ችግሮቻቸውን የሚፈቱበት ስልት ነው:: በዚህ ዘዴ የኢትዮጵያ መንግሥት እና የሽብር ቡድኑ ስምምነት ያደርጋሉ ተብሎ አይታሰብም:: ምክንያቱም ከላይ ለመጥቀስ እንደሞከርኩት ከጦርነቱ በፊት በአገራችን ዝናብ የሚያፍራቸውን የአገር ሽማግሌዎች እንዴት አድርጎ እንዳዋረደ ተመለክተናል:: በመሆኑም ይህ ግጭትን የማስወገጃ ዘዴ ጊዜው አልፎበታል::

ሌላኛው ግጭትን የማስወገጃ ዘዴ ደግሞ mediation የሚባለው ሲሆን፤ በዚህ ዘዴ ሦስተኛ ወገን በጉዳዩ ጣልቃ እንዲገባ ይደረጋል። ሦስተኛው ወገን ግን ሁለቱ ተደራዳሪዎች እንዲታረቁ ሁኔታዎችን ከማመቻቸት በስተቀር ይህ መሆን አለበት ብሎ ፍርድ ወይም ውሳኔ መስጠት አይችልም::

ብዙ ጊዜ ሦስተኛው ወገን የሚመረጠው በሁለቱ በተጣሉ ወገኖች ነው። ይሁን እንጂ ጉዳዩ ያሳሰበው አካል ላደራድር ብሎ መጠየቅ አይችልም ማለት ግን አይደለም። በአሁኑ ወቅትም የኢትዮጵያ መንግሥትን እና የሽብር ቡድኑ ለማደራደር ራሱን ዝግጁ የአደረገው እና ለድርድሩ በርካታ ማይሎችን የተጓዘው የአፍሪካ ህብረት በሁለቱ ወገኖች የተመረጠ ሳይሆን በኢትዮጵያ የተፈጠረው ችግር ስላሳሰበው ችግሩን ለመቅረፍ በመቆርቆር ነው:: ይህ ደግሞ ኢትዮጵያ ከያዘችው የአፍሪካ ችግር በአፍሪካ ማዕቀፍ ውስጥ መፈታት አለበት፤ ይሄን ማድረግ ይቻላል ከሚለው መርህ ጋር የሚስማማ ነው::

የአፍሪካ ህብረትም ችግሩ እልባት የሚያገኝበትን የመፍትሄ ሃሳብ ለማፈላለግ ብዙ ማይሎችን ከተጓዘ በኋላ ስለ ሰላም ቁጭ ብሎ ለመነጋገር የሚፈራው የሽብር ቡድኑ፤ የሰላም ውይይቱ እንዳይሳካ ለማድረግ የውይይት ሂደቱ በአፍሪካ ህብረት መደረግ የለበትም ሲል የእናቴ መቀነት አደናቀፈኝ እያለ ነው። የዚህ ጥረት ውጤት ደግሞ ምን እንደሚሆን ወደፊት የምናየው ይሆናል::

ምንም እንኳን አሁን ላይ በኢትዮጵያ ላለው ተጨባጭ ሁኔታ ሊያገለግል ባይችልም፤ ሦስተኛው የግጭት መፍቻ ዘዴ የሚባለውን ልጥቀስ:: ሦስተኛው የግጭት መፍቻ ዘዴ የሚባለው ደግሞ እንደ ሽምግልና የሚቆጠረውና Arbitration የሚባለው ሲሆን፤ በዚህም ሦስተኛው አካል ውሳኔ የሚያስተላለፍበት እና ሁለቱ ተደራዳሪ ወገኖች በሦስተኛው ወገን በሚያስተላልፈው ውሳኔ የግድ መስማማት ይጠበቅባቸዋል:: ለምሳሌ፣ የኢትዮ- ኤርትራ የአልጀርስ ስምምነት ለዚህ አንዱ ማሳያ ነው። እ.ኤ.አ በ1951/52 ኤርትራ በፌዴራላዊ አወቃቀር የኢትዮጵያ አካል እንድትሆን የተወሰነው ውሳኔ Arbitration በሚባለው የግጭት መፍቻ ዘዴ የተወሰነ ውሳኔ ነው:: እኔም ለዛሬው እዚህ ላይ ላብቃ! ወደፊት ሌሎች የግጭት መፍቻ ዘዴዎችን እና ፕሮሲጀሮችን ጨምሬ በማምጣት በመንግሥት እና በሕወሓት መካከል ሊደረግ ስለታቀደው የሰላም ውይይት የማስመለከታችሁ ይሆናል። እስከዚያው ቸር እንሰንብት፤ ሰላም!!

# ሥነቃል - ቀዳሚው አገር በቀል የፍልስፍናችን መሠረት

ግርማ መንግሥቴ

የሰው ልጅ ሁለት ዓይነት ሀብቶች አሉት። አንዱ መንፈሳዊ ሀብቱ ሲሆን፤ ሁለተኛው ደግሞ ቁሳዊ ቅሪቱ ነው። ይህንን ወደ ቱሪዝም ቋንቋ እንተርጉመው ብንል የምናገኘው በ«ሀብቶች» ስፍራ «ቅርሶች» ተተክቶ፤ ቅርሶቹም «የሚዳሰሱ» እና «የማይዳሰሱ» ሆነው እናገኛቸዋለን። ከማይዳሰሱት አንዱ ደግሞ ይህ የዛሬ ርእሰ ጉዳያችን ያደረግነው አገር በቀል እውቀት ሰራሹ ሥነቃል ነው።

አንድ ምንጭ (ፊኒጋ (1970)ን እና ፈቃደ (1991)ን) ጠቅሶ ለንባብ የበቃ ጽሑፍ እንደሚያሳየው ሥነቃል የአንድ ሕዝብ ቁሳዊና መንፈሳዊ እሴት መግለጫ፣ የኑሮውና የስሜቱ ነፀብራቅ ነው፡፡

በዱንዴስ (Dundes፡ 1965:5) የተጠቀሰውን ዊሊያም ጆን ቶምስ በመጥቀስ ፎክሎር፤ የነገራትን አሠራርና አኳኋን፣ ልማዶችን፣ በአላትንና ሥርዓተ አከብሮን፣ ዘፈኖች፣ ምሳሌያዊ ንግግሮች፣ እምነትና አምልኮ የሚያጠና የሙያ መስክ መሆኑም ስለሥነቃል ሲነሳ ተቀባይነትን ካገኙት ብያኔዎች አንዱና ሳይጠቀስ የማይታለፈው ነው፡፡

በአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ በኢትዮጵያ ቋንቋዎችና ባህል አካዳሚ የአማርኛ ቋንቋ መምህር የሆኑት አቶ መስፍን መሰለን ጥናት እየጠቀሱ የሚያረጋግጡ ሰዎች እንደሚሉት ሥነቃል ከትውልድ ወደ ትውልድ የሚተላለፍ የራሱ መከወኛ አጋጣሚ ያለው ሲከወን ደግሞ ግጥሙን የሚደረድር ወይም ተረቱን የሚተርክ ወይም እንቆቁልሹን የሚጠይቅ፤ ተረቱ ሲወራ የሚያዳምጥ፤ ግጥሙ ሲደረደር የሚቀበል፤ በባህላዊ ልብሶችና በባህላዊ መሣሪያ ሊታጀብ የሚችል፤ ከትውልድ ትውልድ የሚተላለፍ የአንድ ኅብረተሰብ ሀብት ነው።

ቀደም ሲል የጠቀስናቸው አጥኚዎች እንደሚሉት «ሥነቃል የአንድ ማህበረሰብ ባህል መግለጫ ከሆኑት መሠረታዊ ጉዳዮች መካከል በዋነኛነት ይጠቀሳል።» እንዲሁም፤ «ሥነ-ቃል የሰው ልጅ ለረዥም ጊዜ ቆይታው ያጠራቀመውንና ዛሬ ያለውን ማህበራዊ፣ ፖለቲካዊ እና ኢኮኖሚያዊ ገጠመኞቹን የሚያንፀባርቅበትና ለመጪው ትውልድ በቃላዊ መልኩ የሚገልፅበት የሥነጽሑፍ ዘርፍ» ነው። «ሥነቃል ለረጅም ዘመናት በሰዎች አዕምሮ ውስጥ ያለውን ሀሳብ በማስታወስ ለሌሎች ሰዎች በመንገር፣ በመተረት ወይም በመዜም የሚተላለፍ ጥበብ ሲሆን ጥበቡም የማኅበረሰቡን ፍልስፍና፣ ባህል፣ ኑሮ፣ ርዕዮተዓለም፣ ወግ፣ ልማድ፣ ታሪክ፣ የሕይወት ገጠመኝ ወዘተ. ማስተላለፊያ፣ ማስታወቂያና መግለጫ ጥበብ ነው።»

ሥነቃል ለሰው ልጅ የእርስ በርስ መስተጋብር ወቅት በተወሰኑ ማህበራዊ ጉዳዮች ላይ የሚቀርብ የሕዝብ ፈጠራ ውጤት ሲሆን፣ ቃላዊ ተላልፎን መሠረት በማድረግ በትውስታ ከትውልድ ወደ ትውልድ የሚሸጋገር የፎክሎር ዐቢይ ዘርፍ ነው። በመሆኑም ነው ሥነ-ቃል ለፍልስፍና ቀዳሚ ምንጬ፤ ወይም መሠረቱ መሆኑ ላይ እየተነጋገርን ያለነው።

ሥነ-ቃል የአንድ ማህበረሰብ መገለጫ መሆኑ ይሁንታን ካገኘ ሰንብቷል። በዘመናዊው የጥናት መስክም በፎክሎር (ቀጥሎ ያለውን አንቀፅ ይመልከቱ) ስር መታቀፉና ቃላዊ ቅርስና የሕዝብ ሀብት መሆኑ ተደርሶበታል። ከሰው ልጅ የዕለት ተዕለት ሕይወትና ተግባር ጋር ጥብቅ ግንኙነት እንዳለው፤ መገለጫዎቹም ተረት፣ ተረትና ምሳሌ፣ እንቆቅልሽ፣ እንካ ሰላንቲያ ... መሆናቸው ተለይቷል። የኢትዮጵያውያን እሴት እንደሆነና ግብረ ገብን የሚያስተምር፣ ታሪክን፣ ልማድን ... (ancestral tradition) ከትውልድ ወደ ትውልድ የሚያስተላልፍ መሆኑም በተመሳሳይ። እንዲሁም፣ «ሥነቃል ልክ እንደ ሥነጽሑፍ ሁሉ የተነገረበትን ማህበረሰብ ማህበራዊ፣ ኢኮኖሚያዊና ፖለቲካዊ ጉዳዮች በጥበባዊና በጠለቀ መንገድ ያቀርባል።» የሚለው የጋራ ስምምነትን አግኝቷል። ፍልስፍናዊ፣ ሥነልቦናዊ ... የሚሉትንም በዚሁ መንገድ ማየት ይቻላል። በመሆኑም፣ በከፍተኛ ደረጃ ተጠብቆ ለትውልድ መተላለፍ ይገባዋል።

ፎክሎር ብቻውን አየር ላይ የተንጠለጠለ ሳይሆን ዘርፎች አሉት። አጥኚዎቹ (ለምሳሌ ፈቃደ አዘዘ፣

> **ሥነቃሎቻችን ተደፈሩ ማለት ፍልስፍናችን ተናደ ማለት ይሆናል። ሥነቃሎቻችን ተነኩ ማለት ማንነታችን ተነካ፤ አገር በቀል እውቀታችን ተበረዘ፣ ተከለሰ ... ማለት ይሆናል**

1991) እንዳገኙት፣ ሥነቃል፣ ቁሳዊ ባህል፣ ሀገረሰባዊ ልማድ እና ሀገረሰባዊ ትውን ጥበባት ናቸው።

ከፋይዳው አኳያ ካየነው ደግሞ ሥነቃል ያስተምራል (ለምሳሌ ተረት)፤ ያመራምራል (እንቆቅልሽ)፤ ያነቃቃል (የሥራ ግጥም)፤ ያስፏጫል ወይም ይነሽጣል (ፉከራ፣ ሽለላ ...)፤ ሀሳብን ባጭሩ ለመግለፅ ያገለግላል (ምሳሌያዊ አነጋገር፣ ዘይቤያዊ አገላለፅ ...)፤ ታሪክን የማሳወቅ ሚና ይጫወታል (አፈ-ታሪክ)፤ ስለ ነገሮች አመጣጥና አፈጣጠር ያትታል/ያብራራል (ሚት) ... ወዘተርፈ። በመሆኑም የአንድን ሕዝብ አጠቃላይ ፍልስፍና ይዟል ማለት ነው። በመሆኑም ከፍልስፍና እውቅና ማግኘት በፊት ሥነቃል ነበር ማለት ነው። በመሆኑን፣ ሊጠበቅና ከትውልድ ወደ ትውልድ በአግባቡ ሊተላለፍ ይገባል እንጂ «በከተሞች ከደበዘዙት ባህሎች ሥነ-ቃል አንዱ ነው» በሚለው የጥናት ግኝት ቆሽታችን ሲቃጠል መኖር የለበትም።

ወደ ዋናው ርእሰ ጉዳያችን ከመሄዳችን በፊት በፎክሎር ጥናትም ሆነ ንባብና ትንታኔ ወቅት በመግቢያነት ሳይጠቀስ የማይታለፈውን፤

ፎክሎር በሚለው ቃል ለመጀመሪያ ጊዜ የተጠቀመው ዊሊያም ጆን ቶምስ (Wiliam John Thoms፣ 1803-1885) የተባለ እንግሊዛዊ የጥንታዊ ቅርስ ተመራማሪ (antiquarian) ሲሆን ነሐሴ 22 ቀን 1846 (እ.አ.አ.) አቴንየም (The Atheneum) ለተባለ ትምህርታዊ መጽሔት በጻፈው ደብዳቤ ላይ ነው፡፡ ከዚያ በፊት ግን እንግሊዝ አገር ውስጥ የዳበሩ የጥንታዊ (የአሮጌ) ጥናቶች (antiquarian scholarship) ማለትም የጥንታዊ ሕንፃ፣ የጥንታዊ ተረት፣ የጥንታዊ ባህል፣ የጥንታዊ ዘፈን፣ የጥንታዊ መዝገብ ወዘተ ጥናቶች ሲሆኑ የሚጠሩባቸው ስሞች ሕዝባዊ ቅሪት (popular antiquities)፣ ሕዝባዊ ሥነጽሑፍ (popular literature) ወዘተ ነበር፡፡

ቃላዊ ሥነጽሑፍ የሆነው ሥነ-ቃል (በሥሩ የሚካተተው ቃል ግጥምን ጨምሮ) ሀሳብን/መልዕክትን በአጭሩና በማይረሳ መልኩ ለመግለጽ አመች መሆኑ ተጠንቶ ማረጋገጫዎችን ካገኘ ቆይቷል። ሁሉም እንደ አገሩ ቋንቋና ባህል በተለየና በራሱ በሆነ መንገድ ቢጠቅምበትም ሥነ-ቃል በኢትዮጵያውያን (እንደ አጠቃላይም በአፍሪካውያን (ለምሳሌ የመላከነህን Map of African Literature፤ እንዲሁም ፈቃደ፣ 1991፣ 22 እዝስከ 26 ይመለከቷል።)) ዘንድ ለየት ያለ ቦታና ፋይዳ አለው።

እንደምናውቀውም ሆነ በተደጋጋሚ የተለያዩ ጥናቶች እንደሚያረጋግጡት እኛ ኢትዮጵያውያን ሥነ-ግጥምን በተለያየ መልኩ እንጠቀምበታለን፤ ... ለደስታ፣ ለኀዘን፣ ለጦርነት፣ ለፍቅር፣ ለጥላቻ፣ ለእምነት መግለጫ፣ ለፈጣሪያችን ምስጋና (ወቀሳንም ጨምሮ) ማቅረቢያ፤ በሕዝብ ላይ የተንሰራፋ የፖለቲካ ዝቅጠትንና የከፋ አገዛዝን፤ እንዲሁም ሙስናን ለመግለጽና በመሳሰሉት አጋጣሚዎች ሥነ-ቃልን እንጠቀማለን። በጉዳዩ ላይ አብዝተው የሠሩት፣ የአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲዎቹ ዘሪሁን አስፋው፤ ዶ/ር ፍቃደ አዘዘ (ሥነቃልን «ኪነተ-ቃል» (1989) ይለዋል)፣ ዶ/ር መላክነህ መንግሥቱ፤ ትውልደ ካናዳዊውና በምርጫ ኢትዮጵያዊው፣ በኢትዮጵያ ፍልስፍና ላይ ተወዳዳሪ በሌለው ደረጃ በርካታ ሥራዎችን የሠሩት፣ የፍልስፍና ፕሮፌሰር ክላውድ ሰምነር (1919–2012)፤ ሩዝ (Ruth Finnegan) እና የመሳሰሉት አጥብቀው የሚነግሩን ይህንኑ ነው። (www.folklore.et የተባለው ድረ-ገጽም በዚሁ ላይ ያተኮረ እንደ መሆኑ መጠን እዚህ ሊጠቀስ ግድ ይላል።)

(እዚህ ላይ «ፎክሎራዊ ጉዳዮችን በመሰብሰብ (አንዳንዶች በማጥናት ይሉታል) በዓለማችን በግንባር ቀደምነት የሚጠቀሱት የግሪም ወንድማማቾች /The Grimm Brothers/ የሚባሉ ሁለት ጀርመናውያን ናቸው፡፡ ሙሉ ስማቸውም ያኮብ ሉድቪክ ካርል ግሪም (Jacob Ludwing Karl Grimm 1785-1863 እ.አ.አ.) እና ቪልሄልም ካርል ግሪም (Wilhelm Karl Grimm 1786-1859 እ.አ.አ.) በመባል ይታወቃል::» የሚለውን በቅንፍ አስቀምጠነው ብናልፍ ከውለታ አንፃር ያስኬደናል ብለን እናስባለን። «ምርጥ የግሪም ተረቶች» በሚል ርእስ ወደ አማርኛ የተመለሰው የእነዚሁ ወንድማማቾች ሥራ መሆኑንም ማስታወሱ አይጎዳምና አድርገነዋል።)

በቋሚና ዘላቂ የኅብረተሰብ ሀብትነቱ የሚታወቀው ሥነቃል «በአንድ ኅብረተሰብ ውስጥ ያለውን ማንኛውንም ክንዋኔ የሚገልጽ ነው። የሚገልጸውም የኅብረተሰቡን አስተሳሰብ፣ አመለካከት፣ እርስ በርሱ ያለውን ግንኙነት» ነው። «ሥነ-ቃል ለአንድ ማኅበረሰብ ዛሬም ሀብት ሆኖ ያገለግላል»። ይሁን እንጂ፣ በከተሞች እየደበዘዙ በመምጣት ላይ ካሉት የሕዝብ ሀብቶችና ማህበረ ባህላዊ እሴቶች መካከል አንዱ መሆኑ በብዙዎች እየተነገረ ይገኛል።

ሥነቃል በከተማ ተቀይጦም ቢሆንም በኅብረተሰቡ ዘንድ አገልግሎቱን እየሰጠ እንደሚገኝ፤ ከከተማው በበለጠ ግን በገጠሪቱ ክፍል መሠረቱን አልለቀቀም የሚለውን የመምህር መስፍንን ጥናት በማስረጃነት የሚያቀርቡ ሰዎች አሁን አሁን ጉዳዩ እየባሰበትና ፈሩን እየለቀቀ መምጣቱን ነው አዝወትረው የሚናገሩት። «ፈሩን አልለቀቀም ...» የሚሉት አቶ መስፍንም ቢሆኑ አደጋ ላይ አለመሆኑን አይናገሩም። በመሆኑም፣ ጉዳዩ ያሳስባል፣ ያጠያይቃል፣ ያመራምራልም።

በአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ፣ በኢትዮጵያ ቋንቋዎችና ሥነጽሑፍ «የአማርኛ ቋንቋ ማስተማር ሥነ ዘዴ» ላይ ሁለተኛ ዲግሪያቸውን የሠሩትና ለ32 አመታት በመምህርነት ያገለገሉት አቶ ሚሊዮን ዘውዴ ከጀርመን ሬዲዮ ጣቢያ ጋር አድርገውት በነበረ ቆይታ እንደተናገሩት የሥነቃል ሀብታችን አደጋ አጥልቶበታል። [...] ምንም እንኳን ሥነ-ቃል የተለዋዋጭነት ባህርይ ቢኖረውም ሥነቃላችን የመጥፋትና የመረሳት ነገር እየታየበት ነው ያለው። በመሆኑም «ማንነት ማጣት ስለሆነ [ጉዳዩ] ትኩረት ሊሰጠው፤ መፍትሄ[ም] ሊበጅለት ይገባል። ትውልዱ ባህሉን [ወደ] ማወቅ መምጣት አለበት።»

እርግጥ ነው ዛሬ በከተሞች በርካታ ቱባ ቱባ ሕዝባዊ ባህሎች፣ እንዳ'ጠቃላይም የሕዝብ የአኗኗር ፍልስፍናዎች ባልተጠበቀ ፍጥነት እየተቀየሩ ይመስላል። ከእነዚህም መካከል አንዱ ተማራማሪዎቹ ከላይ እንደገለፁት ሥነቃል ሲሆን፤ ይህም በመጽሔት ሁሉ ሳይቀር እየታገዘ እንደሚከናወን እየታየ ይገኛል። (እስኪ አሁን «አባይ ማደሪያ የለው ችክ ይዞ ይዞራል» የሚለውን ምን ይሉታል? መፍጠሩ እንኳን ቢያቅት ነባሩን ይዞ ማቆየቱ ምን ያቅታል?)

«ሰንበሌጥ» ከ'ነተሸከመው ፍልስፍናና ትርጓሜው ወዲያ ተጥሎና ተነጥሎ «የ'ነ ቶሎ ቶሎ ቤት፣ ግድግዳው ብሎኬት» ሆኖ የጸሐፊነት ስማቸውን ካ'ናት ያሰፈሩ ጸሐፊዎች ከስማቸው ቀጥሎ አስፍረውት ማንበብ ለማንም አዲስ አይደለም። ኤሌክትሮኒክሱ ሚዲያም ተቀብሎ ሂድ ሲለው መስማትም እንደዛው።

የሰው ልጅ በቡድን መኖር ከጀመረበት ጊዜ ጀምሮ የነበረ መሆኑ የሚነገርለት ሥነቃል (ቃላዊ ትውፊት)፤ «ከዕለታት አንድ ቀን ...» በሚል መሠረት ላይ በመቆም ረጅም ዕድሜን ማስቆጠሩ፣ የፈጣን አእምሮ ፈጠራ ውጤትና ሲበዛም አመራማሪ መሆኑ የተረጋገጠለት ሥነቃል፤ በሚያገለግለው ማህበረሰብ ታሪክ ላይ የተመሠረተ (የሚመሠረት) መሆኑ የሚታወቅለት ሥነቃል፤ የአንድ ማህበረሰብ ፍልስፍናው መገለጫ እንደሆነ የታመነው ሥነቃል፤ ከዛሬው ዘመናዊ ተብዬ ዘመናይ የፍትህ ሥርዓት ሥራ ላይ ከመዋሉ አስቀድሞ የፍትህና ርትእ ምንጭ ሆኖ ሲያገለግል የኖረው ሥነቃል (ስለሺ ለማን «በላ ልበልሃ ...» ያስታውሷል)፤ የአንድን ማህበረሰብ ወግ፣ ልማድ፣ እንዲሁም ታሪክ ማስተላለፊያና ልዩ ልዩ ክስተቶችን እና የሕይወት መልኮችን መግለጫ ጥበብ (ፍልስፍና) የሆነው ስነቃል፤ «በመነገር፣ በመተረት ወይም በመዜም በተወሰኑ ማህበራዊ አጋጣሚዎች ላይ የሚከወን ቃላዊ ፈጠራ» ስለመሆኑ የሚወሳለት ሥነቃል ... እንዴት ሆኖ ለእንደዚህ ዓይነቱ የከፋ አደጋ ሊጋለጥ ይገባል የሚል ጥያቄ በቀጥታ፣ በዚህ መልክም ባይሆን በየራሱ መንገድ ሲቀርብ ቆይቷል።

ከዚህ በመለስ በማይባሉ የዘርፉ ጥናቶች ማህበረሰቦች በረጅም ዘመን ታሪካቸው ያጠራቀሙትና የሚያጠራቅሙት ቅርስ ከመሆኑ፤ ለህልውናቸው ሲሉ በሚያደርጓቸውና ከተፈጥሮ ጋር ካላቸው መስተጋብርና ትግል የሚፈጠር የአያሌ ገጠመኞች ጥርቅምና የገጠመኞችም ማንፀባረቂያ መሆኑ፤ ቃላዊ ጥበብ በተለይ ፊደል ቀርፀው በጽሑፍ በማይገለገሉ ማህበረሰቦች ዘንድ ማንነትና ምንነትን፣ እምነትን የኑሮ ዘይቤንና ፍልስፍናን ባጠቃላይ የዓለም አመለካከትን ቀርፆ ለተተኪው ትውልድ በማስተላለፍ ረገድ የሚጫወተው ሚና ከፍተኛ እንደሆነ ... ወዘተርፈ የታወቀው ሥነቃል እንዴት እንዴት የባህል አፍራሾች፣ ማንነት ናጆች፣ ታሪክ አፋላሾች ... ሰለባ ይሁን? የሚለው የወግ ጠባቂዎችና ተቆርቋሪዎች ድምፅ መሰማት ከጀመረ ዘመኑ ዛሬ እንዳልሆነ ድርሳናትን የፈተሸ ሁሉ በሚገባ ያውቀዋል።

### ማጠቃለያ

ኢትዮጵያ ከ80 በላይ ቋንቋዎች ያሏት ትልቅ አገር መሆኗ ይታወቃል። ይህ ማለት ደግሞ ኢትዮጵያ የቱባ ባህል ባለቤት ነች ማለት ነው። በሁሉም አገሪቱ ውስጥ በሚገኙ ቋንቋዎች አማካኝነት የካበተ የሥነቃል ሀብት ያላት አገር ነች ማለት ነው። ይህ ከሆነ የአገሪቱም ሆነ ሕዝቧ ልዩ ልዩ ፍልስፍናዎች (የአኗኗር፣ አስተሳሰብ፣ አሠራር ...) ሁሉ የሚገለፁትም ሆነ የሚቀዱት ከዚሁ ነው ማለት ነው (እስቲ «በሕግ አምላክ» የሚለውን ብቻ እንኳን እንመርምረው፤ ሁለት የገዘፉ ቃላት በአንድ አብረው ለአንድ ጽንሰ ሀሳብ አድረው እናገኛቸዋለን። ከዚህ አኳያ ሥነቃሎቻችን ተደፈሩ ማለት ፍልስፍናችን ተናደ ማለት ይሆናል። ሥነቃሎቻችን ተነኩ ማለት ማንነታችን ተነካ፤ አገር በቀል እውቀታችን ተበረዘ፣ ተከለሰ ... ማለት ይሆናል። ሥነቃሎቻችን ማላገጫ ሆኑ ማለት በማንነታችን ተላገጠ ማለት ይሆናል። ሥነቃሎቻችን በነጭ ተሰረዙ ማለት ማንነታችን በነጭ ተሰረዘ ማለት እንጂ ሌላ ሊሆን አይችልም። ሥነቃሎቻችን ተደነቆሉ ማለት አጠቃላይ ሥነጽሑፋችን አይኑ ጠፋ ማለት ነው። ወዘተርፈ ....። ሌሎች አገራት በየአመቱ፣ በተቋም ደረጃ በትላልቅ ቅፆች እየሰበሰቡና እየሰነዱ ማቆየታቸው ለጌጥ ሳይሆን ማንነታቸው በነጭ እንዳይሰረዝ በማሰብ ነው። በመሆኑም፣ እኛም የእኛዎቹን ልናለማቸው፣ ልንጠብቃቸው፤ ጠብቀንም ከ'ነወግ ማእረጋቸው ለትውልድ ልናስተላልፋቸው ይገባል። ግዴታ ያለበት ኃላፊነትም ነው። (ለዚህ ደግሞ ከመቼውም በላይ ዛሬ ምቹ ሁኔታ አለ፤ በሁሉም ክልል የባህልና ቱሪዝም ቢሮዎች አሉ።) በኢትዮጵያ ታሪክና ፍልስፍና ላይ እድሜያቸውን የፈጁት ፕሮፌሰሮች (ክላውድ ሰምነር፣ ሪቻርድ ፓንክረስት ... እና የመሳሰሉት) የሚሉት ይህንኑ ነው።

ማህበራዊ

# ወጣቶች

# ጤናማ የሥራ እድል ስነ-ምህዳር ለመፍጠር

**አስናቀ ፀጋዬ**

ለወጣቱ የስራ እድል ለመፍጠር ከዚህ ቀደም በመንግስት በኩል በርካታ ጥረቶች ሲደረጉ ቆይተዋል:: ከነዚህ ጥረቶች ውስጥ አንዱ ወጣቶች በጥቃቅንና አነስተኛ ተደራጅተው እንዲሰሩ ማድረግ ነበር:: አብዛኛው ብድር ሳይመለስ ቀረ እንጂ ለወጣቶች የተመደበው የ10 ቢሊዮን ብር ተዘዋዋሪ ፈንድም ለወጣቶች የስራ እድል ለመፍጠር ነበር:: ሆኖም ካለው የስራ ፈላጊ ወጣት ቁጥር አንፃር አዋጭና ውጤታማ የስራ መፍጠሪያ ስርአቶች ጉድለት በመኖሩ በሚፈለገው ልክ ለወጣቱ የስራ እድል መፍጠር ሳይቻል ቀርቷል::

‹‹ከዚህ ቀደም በመንግስት በኩል ለወጣቱ የስራ እድል ለመፍጠር ሲደረጉ የነበሩ ያለፉ ሙከራዎች ጥሩ ቢሆኑም ከፍተኛ የስራ ፍላጎት፣ የወጣት ቁጥርና የህዝብ እድገት በመኖሩና የዛኑ ያህል ደግሞ ሀገሪቱ ውስጥ ያለው ገበያ ይህን መሸከም የሚችል ባለመሆኑ የሚፈለገውን ውጤት ማምጣት አልተቻለም:: በመሆኑም ለወጣቱ ጤናማ የስራ እድል ለመፍጠር ሞያዊ ምክረ ሃሳቤ ይህ ነው›› ይላሉ የብሩህ ማይንድስ ኮንሰልት መስራችና ዳይሬክተር አቶ ሰለሞን ደሳለኝ::

እርሳቸው እንደሚሉት ድርጅታቸው ‹‹ብሩህ ማይንድስ›› አማካሪ ድርጅት ሲሆን ስራውን እ.ኤ.አ በ2014 በይፋ ጀምሯል:: የጥናትና ምርምር ስራዎችንም ሲያከናውን ቆይቶ እ.ኤ.አ ከ2020 ወዲህ በማህበራዊ፣ ቢዝነስና ኢኮኖሚያዊ ጉዳዮች ላይ ያተኮሩ አስራ ሁለት ያህል ስልጠናዎችን እየሰጠ ይገኛል:: በአሁኑ ግዜ ደግሞ በሚታወቅበት የንግድ ስራ ማጎልበት አገልግሎት ይሰጣል::

እንደ ዳይሬክተሩ ገለፃ በኢትዮጵያ በርካታ የስራ ፍላጎት አለ:: ይህም አሁን በስራ ላይ ካለው ሰው በተጨማሪ በየዓመቱ 2 ሚሊዮን ወጣቶች ከከፍተኛ የትምህርትና የቴክኒክና ሞያ ስልጠና ተቋማት ተመርቀው ወደ ስራ ገበያ ይመጣሉ:: በተጨባጭ መሬት ላይ ያለው እውነታ ሲታይ ግን የኢንዱስትሪውና የግብርናው ዘርፍ ባለማደጉ፣ ያለው የንግድና የግብይት ስርአትም በሚገባ መስመር የያዘ ባለመሆኑ ከፍተኛ የስራ አጥነት ችግር አለ::

ይህም ስራ ፈላጊ በብዛት አለ እንጂ ስራ መፍጠር የሚያስችል ምህዳር የለም ማለት ነው:: ይህን ችግር በማየት መንግስት በአሁኑ ግዜ የስራና ክህሎት ሚንስቴር፤ ከዚህ ቀደም ደግሞ የስራ ፈጠራ ኮሚሽንን አቋቁሟል:: ጥቃቅንና አነስተኛ በሚል ኢንተርፕራይዞችን ለማደራጀትና ስራ ለመፍጠር ያለሙ ጥረቶች ሲደረጉም ቆይተዋል:: በመንግስት በኩል ሲደረጉ የነበሩ ያለፉ ሙከራዎች ጥሩ ቢሆኑም ታዲያ ከፍተኛ የስራ ፍላጎት፣ የወጣት ቁጥርና የህዝብ እድገት በመኖሩና በዛው ልክ ደግሞ ሀገሪቱ ውስጥ ያለው ገበያ ይህን መሸከም የሚችል ባለመሆኑ የሚፈለገውን ውጤት ማምጣት አልተቻለም::

ብዙ ስራ መፍጠር የሚያስችል አቅም እያለ ለወጣቱ ስራ መፍጠር አልተቻለም:: ወጣቱ ጋር እውቀት፣ ክህሎት፣ ጉልበትና ግዜ አለ:: ይሁንና የመስሪያ ቦታና መነሻ ካፒታል ትልቅ ማነቆ ሆኗል:: ሆኖም ይህን ችግር ፈጠራ የታከለባቸው የአሰራር ስሪቶችን በመከተል፣ በመደራጀትና በመቀናጀት ብሎም በጋራ በመስራት መቅረፍ ይቻላል::

ጥቅም ላይ ሳይውሉ የቀሩና የመከኑ በርካታ እድሎች አሉ:: የተዘዋዋሪ ፈንድን ጨምሮ በመንግስት በኩል የተደረጉ የገንዘብ ድጋፎችም ነበሩ:: በወጣቶችም ዘንድ እነዚህን እድሎች ወስዶ ከመጠቀም ይልቅ እንደ ልገሳና እርዳታ ወስዶ ተጠቅሞ ዞር የማለትና ብድርን ያለመመለስ ችግሮች ይታዩ ነበር:: በዚህም በርካታ ብድሮች ተበላሽተዋል:: ይህም በቀጣይ ለሚፈጠረው የስራ እድል እንቅፋት ሆኗል::

መንግስትም ሆነ ሌሎች አካላት ወጣቶችን ማመን ይፈልጋሉ:: መተማመን ከሌለ ማበደርም መስራትም



**አቶ ሰለሞን ደሳለኝ**

ያስቸግራል::ዕድሉን ያገኙ ወጣቶች የተሰጣቸውን ሼድ ለሌላ ወጣቶች ከአምስት አመት በኋላ ካልለቀቁ የስራ እድል መፍጠር አይቻልም:: በሌላ በኩል ደግሞ በትክክል የቀረቡ ወጣቶች የስራ እድል ፈጠራ ጥያቄዎች ሲያነሱ በአግባቡ ምላሽ የሚያገኙበት ስርአት አልተዘረጋም::

በዛው ልክ በጣም በርካታ የስራ እድል መልሰው የሚፈጥሩ፣ ከውጪ የሚገቡ ምርቶችን የሚተኩ፣ የፍጆታ እቃዎችን ችግር የሚቀርፉ፣ የኑሮ ውድነትን የሚያቃልሉ የፈጠራ ሃሳቦች ያሏቸው ወጣቶች ሲመጡ አደራጅቶ፣ አሰልጥኖ፣ አብቅቶ፣ የብድር አመላለስንም ባህልን ፈጥሮ፣ በቁጠባ በኩል ያለውንም ባህል አሳድጎ የሚሰጥ ስርአት አልተበጀም:: በዚህም ምክንያት በርካታ ሀብት ባክኗል::

ዳይሬክተሩ እንደሚያብራሩት የሚመለከታቸው ባለድርሻ አካላት ተቀናጅተው ቢሰሩ፣ ከመስሪያ ቦታና መነሻ ካፒታል ከማቅረብ አንፃር ምቹ ሁኔታ ቢፈጠር፣ የአካሄድም፤ የአስተሳሰብም፤ የአሰራርም፤ የህግ ማሻሻያዎች ቢደረጉ የሚገኙትን ትሩፋት በማሰብ መንግስትም ፍቃደኛ በመሆኑና በልማት ባንክ በኩልም የተደረጉ ጥረቶች አበረታች በመሆናቸው፣ ወጣቶችም ከበፊቱ ይልቅ አሁን ጥሩ መነሳሳት ያላቸው በመሆኑ ጤናማ የስራ እድል መፍጠር ይቻላል:: ነገር ግን ደግሞ ወጣቶቹ የቅርብ እገዛና ክትትል ያስፈልጋቸዋል::

ከዚህ አኳያም ብሩህ ማይንድስ ከኢትዮጵያ ኢንተርፕራይዝ ልማት ጋር በጋራ ለመስራት ያነሳሳው ደጋፊ አካላትና ወጣቱ በመሀል ያለውን ክፍተት መቅረፍ እችላለሁ ብሎ በማሰቡ ነው:: ምንም እንኳን ድርጅቱ ለትርፍ የተቋቋመ ቢሆንም እንደግሉ ዘርፍ ማህበራዊ ሃላፊነትም ያለበት በመሆኑ በመንግስትም ሆነ መንግስታዊ ባልሆኑ ተቋማት የሚሰሩ የስራ እድል ፈጠራ ስራዎች ላይ የራሱን አስተዋፅኦና አሻራ ማኖር አለብኝ ብሎ ያምናል::

በተለይ ስራ ፈጠራ ሃሳብ ማመንጨትን ስለሚጠይቅ የግሉ ዘርፍ ለስራ ፈጠራ ቅርብ ነው ተብሎ ይታመናል:: ካለው አካሄድና አሰራርም ተወዳዳሪነት ላይ ተመስርቶ የሚሰራ ስለሆነ ስራን ለመፈፀም ሳይሆን ስራን ለነገ አበርክቶ የተሻለ ውጤት ለማምጣት የግሉ ዘርፍ ይሰራል:: በመሆኑም ሁሌም ውድድር ስላለ ሁሌም ነቃ ያለ አስተሳሰብ፣ አሰራርና ለየት ያለ የቴክኖሎጂ አጠቃቀም ያለበት በመሆኑ የግሉን ዘርፍ ተሞክሮ ማምጣትና ማገዝ ያስፈልጋል::

አብዛኛው ስራውን የሚፈጥሩት ወጣቶችና የኢንተርፕራይዞች ሆኖ የመንግስት ሚና ከመስሪያ ቦታና መነሻ ካፒታል አንፃርና ህጎችን ፍቃድ ከማውጣት ጀምሮ ያሉ ቢሮክራሲዎችን በማቅለል በገበያ ውስጥ ይበልጥ ተወዳዳሪ እንዲሆኑ፣ የመንግስት ትልቅ ግዢዎችም ከኢንርፕራይዞች እንዲከናወኑ በማድረግና በማገዝ ማሳደግ ይቻላል::

ብሩህ ማይንደስም የወጣቶቹ ችግር ምን እንደሆነ በጥናት በመለየት መፍትሄዎችን ይጠቁማል:: ለአብነትም ቴክኖሎጂ ላይ የሚደራጁ ወጣቶች መብራትና ውሃ አይፈልጉም:: ከዚህ ይልቅ የዲጂታል መሰረተልማት ይፈልጋሉ:: ባላቸው መሰረተልማት ውስጥ ገብተው ፈጠራ በታከለበት መንገድ ብዙ አገልግሎት መስጠት ይችላሉ:: ከዚህ አኳያ በህክምና፣ በግብርና፣ በሆቴልና ቱሪዝም ዘርፎች ወጣቶች ሃሳብ ካላቸው ያንን ስራ ለመስራት የሚያስችል መሰረተ ልማት ያስፈልጋቸዋል::

ዳይሬክተሩ እንደሚሉት ኢንተርፕራይዞችን የሚመሩ የመንግስት አካላት ለሁሉም ኢንተርፕራይዞች ወጥ የሆነ ድጋፍ ነው የሚያዘጋጁት:: ከዚህ አንፃር ብሩህማይንድስን የመሰሉ አማካሪ ድርጅቶች መምጣት ለእያንዳንዱ ኢንተርፕራይዞች የትኛው መፍትሄ እንደሚሰራ፣ ምን አይነት ክፍተት እንዳለባቸው፣ የገበያ ትስስር እንዲኖራቸው ለመጠቆም ይረዳል:: ይህም በስልጠና፣ መረጃ በመስጠት አልያም ቴክኖሎጂ በማበልፀግ ሊሆን ይችላል::

የኢትዮጵያ ኢንተርፕራይዞች ልማት ወጣቶችን መልምሎ፣መዝግቦና አደራጅቶ ድጋፍ ያደርጋል:: ብሩህማይንድስ ደግሞ ሞያዊ እገዛ ለማድረግ ከዚህ ተቋም ጋር የጋራ ስምምነት አድርጓል:: በመንግስት ድጋፍ የተሳካላቸው ኢንተርፕራይዝ ቢኖሩም ምንያህሉ ናቸው የሚለው ግን አጠያያቂ ነው:: እየተደረገላቸው ያለው መንግስታዊ ድጋፍ እንዳለ ሆኖ ታዲያ በርካቶች እንዲሳካላቸው እየተደረገላቸው ያለውን የድጋፍ አካሄድ፣ የቴክኖሎጂ መሰረተ ልማት ላይ ያለውን አጠቃቀምና ተቀናጅቶ መስራት ላይ ያለውን ድክመት ማስተካከል ያስፈልጋል::

በኢንተርፕራይዞችና ድጋፍ አድራጊ ተቋማት በኩል ድክመት እንዳለ ይታወቃል:: በሁሉም ኢንተርፕራይዞች ውስጥ ወጥ የሆነ ድጋፍ የማድረግ ችግር አለ:: ከዚህ አንፃር የፋይናንስ፣ ቴክኖሎጂ የሚፈልግ የቴክኖሎጂ፣ የማርኬቲንግ ድጋፍ ማድረግ ይገባል:: ኢንተርፕራይዞቹ ሲደራጁም ምን አቅም አላቸው፣ ምን ይጎላቸዋል የሚለውን ማየት ያስፈልጋል::

ብሩህ ማይንድስ ከኢትዮጵያ ኢንተርፕራይዝ ልማት ውጪ ከሌሎች መንግስታዊ ካልሆኑ ተቋማትና ከግል ድርጅቶች ጋር ይሰራል:: ለአብነትም መንግስታዊ ካልሆኑት ውስጥ ከሶስት ሀገር በቀል ድርጅቶችና ከሁለት አለም አቀፍ ድርጅቶች ጋር የስድስት ወር የንግድ ስራ ማጎልበት አገልግሎት ድጋፍ በመስጠት በተለያዩ መስኮች 60 ኢንተርፕራይዞችን ወደ ስራ ማስገባት ተችሏል:: ባለፉት ስድስት ወራቶች ውስጥም ካፒታላቸው እያደገ ነው፤ አባላቶቹም አልተለያዩም::

በቅርቡ ደግሞ ከአንድ የግል ድርጅት ጋር በመተባበር የሚሰሩ ስራዎች 25 ኢንተርፕራይዞች ከትርፍ፣ከደምበኛ አያያዝና ድርጅታዊ ቅርፃቸውን ጠብቆ ከመሄድ አንፃር ውጤታማ መሆን ችለዋል፤ ከፍተኛ ለውጥ እየታየም መጥቷል:: የአምራች ኢንተርፕራይዝ ዘርፍ እንደሀገር ሲታሰብ በርካታ ገንዘብ የሚፈስበት እንደመሆኑ ብዙ ለውጥ ይመጣበታል:: ለወጣቱ በርካታ የስራ እድል ይፈጠርበታል ተብሎ ይታሰባል::

ዳይሬክተሩ እንደሚገልፁት ብሩህ ማይንድስ ‹‹ ልዩ ምልከታ›› በሚል ርዕስ በስራ እድል ፈጠራ ላይ የሚያተኩር የፖሊሲ የውይይት መድረክ በየወሩ ያካሂዳል:: ከፖሊሲ ውይይቱ ባሻገር የስራ እድል ፈጥረው ለሌላው አርያ የሆኑ ወጣቶች ልምዳቸውን በዚህ መድረክ ያካፍላሉ:: ይህ መድረክ አራት መሰረታዊ ዓላማ ያለው ሲሆን የመጀመሪያው የባለድረሻ አካላት የስራ እድል ፈጠራ ምህዳሩ እንዲሰፋ በጋራ እንዲቀናጁ ማደርግ ነው:: ይህም አጋርነታቸውንና ቅንጅታዊ አሰራራቸውን ማሻሻል ነው::

ሁለተኛው ዓላማ ደግሞ የፋይናንስ ተደራሽነትን በተለይ ደግሞ የስራ ማስኬጃ መነሻ ካፒታል ተደራሽነትን መጨመር ነው::ይህም በአንድ ወገን በመንግስት ወይም መንግስታዊ ባልሆነ ተቋም አልያም በግሉ ዘርፍ ብቻ የገንዘብ ብድርና ድጋፍ ለዚህ ሁሉ ጀማሪ ስራ ፈጣሪ ማድረስ ስለማይቻል ስራው ቢቀናጅና ወደ አንድ ማእከል ቢሰበሰብ የፋይናነስ ተደራሽነቱን ማስፋት ይቻላል::

ሶስተኛው ዓለማ ደግሞ የስራ ጀማሪዎች ትልቁ ፈተና የሆነውን ቢሮክራሲ /ውጣውረድ/ መቀነስ ነው:: በጣም ውስብስብ የሆነው ነገር እንዲቀል ባለድርሻ አካላት እየተመካከሩ ህጋዊነቱን የጠበቀ ነገር ግን ቀላልና ቀልጣፋ የሆነ የንግድ ስራ ቢጀመር ስራ ፈጣሪዎች ሃሳቡ በመነጨላቸው ሰአት መብታቸው ተከብሮ ፍቃድ አውጥተው ወዲያው ወደስራ ይገባሉ:: ይህም በርካታ የስራ እድል ይፈጥራል::

አራተኛውና የመጨረሻው ‹‹የልዩ ምልከታ›› ዓላማ የፖሊሲ ማሻሻያዎችን ማምጣት ነው:: በሀገሪቱ 28 ከመቶ ያህሉ ስራ አጥ ወጣት ነው:: ለስራ ፈጠራ የሚመደበው በጀት ደግሞ አነስተኛ ነው:: በዚህ ዘርፍ የሚመደቡት ባለሞያዎች ምን ያህል ብቁ ናቸው የሚለውም አጠያያቂ ነው:: መንግስት ለሌሎች ዘርፎች የሚሰጠውን ያህል ትኩረት ለስራ እድል ፈጠራ በትክክል ትኩረቱ ከበጀት፣ ከውሳኔ፣ ከክትትል አንፃር ይሰጣል ወይ የሚለውም አነጋጋሪ ጉዳይ ነው:: ከዚህ አኳያ የተሻሉ ፖሊሲዎችና አሰራሮች ቢመጡ ተቋማትም የራሳቸውን አስተዋጽኦ ያበረክታሉ::

ለአብነት ከፖለሲ አኳያ ከገንዘብ ተቋማት ውስጥ ባንኮችን ማየት ቢቻል ማስያዣ ስለሚያስፈልግ ለአነስተኛና መካከለኛ ኢንተርፕራይዞች ብድር አይሰጡም:: ነገር ግን ኢንተርፕራይዞቹ ያለማስያዣ ብድር የሚያገኙበትና መንገስትም ግማሽ ዋስ የሚሆንበት ሁኔታ ቢፈጠር፣ ከባንኮችና ማይክሮ ፋይናነስ ተቋማት በህግ ደረጃ ተቀባይነት ያለው የብድር ስርአት ቢመቻች ወጣቶቹ በአጭር ግዜ ውስጥ አምራች ሆነው በስራቸው ለሌሎች በርካታ ወጣቶች የስራ እድል መፍጠር ይችላሉ::

# የምድር በረከት

# የድንጋይ ከሰልን በሀገር ውስጥ ምርት የመተካት እቅድና ያለው ነባራዊ ሁኔታ

**ስምስም መንግሥቱ**

ስለ ማዕድን ዘርፍ አጠቃላይ እንቅስቃሴ የማዕድን ሚኒስትር ኢንጂነር ታከለ ኡማ፣ሚኒስቴር መስሪያ ቤቱ መረጃን በሚያሰራጭበት ድረገጹ ላይና በአንድ ወቅት ከፋና ብሮድካስት ኮርፖሬሽን ጋር ባደረጉት ቆይታ ከማዕድን ዘርፎች መካከል የድንጋይ ከሰል፣ብረትና ወርቅ የገበያ ሰንሰለትን በማስተካከል ምርትና ግብይቱ እንዲሳለጥ እርምጃዎች እንደሚወሰዱ አስታውቀው ነበር።

ሚኒስትሩ እንዳሉት፤ ኢትዮጵያ ለድንጋይ ከሰልና ብረት ግዥ በአመት ከአንድ ቢሊየን ብር በላይ ታወጣለች። ለማዳበሪያ ግዥም እንዲሁ ከፍተኛ የውጭ ምንዛሪ ይወጣል። እነዚህ ከፍተኛ የውጭ ምንዛሪ ወጭ ተደርጎባቸው ከውጭ ሀገር በግዥ ወደ ሀገር ውስጥ የሚገቡ ግብአቶች ጥሬ ዕቃ በሀገር ውስጥ የሚገኙ ናቸው። ይሁን እንጂ የሀገርን ሀብት በሀገር ማዋል ባለመቻሉ ግብአቶቹ ሁሉ ከውጭ እንዲመጡ ሆኗል።

ከማዕድን ዘርፍ ሀብቶች መካከል አንዱ የሆነውን የድንጋይ ከሰል ከውጭ ማስገባት በ2015ዓም ሙሉ ለሙሉ በማስቀረት በሀገር ውስጥ የድንጋይ ከሰል ምርት ለመተካት ማዕድን ሚኒስቴር አቅዶ ጠንክሮ እየሰራ መሆኑን አስታውቋል። ግብአቱን የሚጠቀሙት የሲሚንቶ አምራች ኢንዱስትሪዎች በአመት አንድ ነጥብ አምስት ሚሊየን ቶን የተጣራ የድንጋይ ከሰል ያስፈልጋቸዋል። ይህን ለማሳካትም 12 ኩባንያዎች ተመርጠው በሁሉም የሀገሪቱ አካባቢዎች ሁለትና ሶስት ቦታዎች ላይ የምርት ፍለጋ እንዲያካሂዱ ፈቃድ ተሰጥቷቸዋል።

ኩባንያዎቹም በማሽን ግዥ ላይ እንደሆኑና መንግሥትም አስፈላጊውን እገዛ አድርጎላቸው ወደ ሥራው እንደሚገቡ ሚኒስትሩ ማስረዳታቸው ይታወሳል። ሚኒስቴር መስሪያ ቤቱ ባለሀብቶች ጥሬ ሀብቱ በሚገኝበት ሥፍራ ፋብሪካ አቋቁመው ጥሬ ሀብቱን አልምተው ለአምራች ኢንዱስትሪው ማቅረብ እንዲችሉም ሁኔታዎችን ማመቻቸቱንም ከዚህ ቀደም ዘግበናል።

ሚኒስትሩ ኢንጂነር ታከለ እድገትን መመኘት ብቻውን በቂ እንዳልሆነና በእቅድ የያዙትንም ለመፈፀም መትጋት እንደሚጠብቅባቸው በወቅቱ ተናግረዋል። ሚኒስቴር መስሪያ ቤቱም የተሰጠውን ኃላፊነት ለመፈፀም ቅንጅትን ዋነኛ ማዕከል አድርጎ እየተንቀሳቀሰ መሆኑንና በቅንጅት የማዕድን ወጪ ንግድን እንደሚያሳድጉ ተናግረዋል። ከውጭ የሚገቡ ምርቶችንም በሀገር ውስጥ በማምረት ለመተካት ሚኒስቴሩ በትክክለኛው መንገድ ላይ መሆኑንም አመልክተው ነበር።

የድንጋይ ከሰል ለሲሚንቶ አምራች ኢንዱስትሪዎች ለኃይል ግብአትነት የሚውል በመሆኑ በአምራቾቹ በእጅጉ ይፈለጋል። የምርት አቅርቦቱ በሀገር ውስጥ ቢኖርም የአቅርቦት ማነስና የጥራት ጉድለት እንዳለበት በአምራቾቹ በስፋት የሚነሳ ጉዳይ በመሆኑ ከውጭ በግዥ የሚገባው በስፋት ጥቅም ላይ ሲውል መቆየቱን ነው መረጃዎች የሚጠቁሙት።

አሁን ባለው ሁኔታ ከውጭ በግዥ የሚገባው የድንጋይ ከሰል ዋጋ በመናሩና እንደ ሀገር ባጋጠመው የውጭ ምንዛሪ እጥረት የተነሳም የአቅም ውስንነት መፈጠሩ በተደጋጋሚ ይነሳል። ይህ የአንድ ወቅት መነጋገሪያ የነበረውን የሲሚንቶ አምራቾች የድንጋይ ከሰል ጥሬ ዕቃ አቅርቦት ችግር ለመፍታት መንግሥት በቁርጠኝነት ሲያደርግ የነበረው እንቅስቃሴ ውጤት ላይ ደርሶ እንደተባለው ይነሳ ለነበረው ለአቅርቦት ችግር መፍትሄ እየሆነ ይሆን?

በጉዳዩ ላይ የሲሚንቶ አምራቾች ማህበር ፕሬዚደንት አቶ ኃይሌ አሰግዴን እንዲሁም የድንጋይ ከሰል ጥሬ ዕቃ ሀብት ክምችት ከሚገኝባቸው የኢትዮጵያ ክፍል አንዱ በሆነው በደቡብ ብሄር፣ብሄረሰቦችና ህዝቦች ክልል በጉራጌ ዞን አበሽጌ ወረዳ ጊቤ ቀበሌ ውስጥ የድንጋይ ከሰል ማምረትና ማቀነባበር ስራ በማዕድን ሚኒስቴር ፍቃድ የተሰጠው ሰን ማይኒንግ ትሬዲንግ ኃላፊነቱ የተወሰነ የግል ኩባንያ የሚገኝበትን የሥራ ሁኔታ በተመለከተ በደቡብ ብሄር፣ብሄረሰቦችና ህዝቦች የጉራጌ ዞን ውሃ፣ማዕድን እና ኢነርጂ መምሪያ ኃላፊ አቶ ፍሰሐ ዳምጠውን ሀሳብ።

በቅድሚያም አቶ ኃይሌ አሰግዴ እንዳስረዱት ሲሚንቶ ለማምረት የኃይል ግብአት ወሳኝ ነው።በሥራው ሂደት ውስጥ ለማቃጠል ጥቅም ላይ የሚውለው ኃይል ፈሳሽ ጋዝ እና የድንጋይ ከሰል ነው።በዋጋ የድንጋይ ከሰል ግብአት ቅናሽ በመሆኑ አምራች ኢንደስትሪዎቹ በቅናሽ ዋጋ የሚቀርበውን ግብአት ይጠቀማሉ።አምራች ኢንደስትሪዎቹ ቅናሽ ዋጋ ያለው ግብአት ሲጠቀሙ፤ሸማቹም በዋጋ ተጠቃሚ ይሆናል።

የግበአት ዋጋ ውድ ሲሆን፣ሸማቹ ላይ ነው የሚያርፈው።ይህ ደግሞ ኢኮኖሚያዊ ጫና ያሳድራል።እንዲህ ያለውን ችግር ለመፍታት መንግሥት የተለያዩ ጥረቶች አድርጓል።የመፍትሄ ጥረቶቹ ግን የሚፈለገውን ውጤት አስገኝቷል ለማለት አቶ ኃይሌ አልደፈሩም።

እርሳቸው እንዳሉት አምራች ኢንደስትሪዎቹ እስከ ቅርብ ጊዜ ድረስ ከውጭ በግዥ ወደ ሀገር በሚገባ የድንጋይ ከሰል በመጠቀም ነው ሲሚንቶ ሲያመርቱ የቆዩት።ከውጭ በግዥ በሚገባው እና በሀገር ውስጥ ከሚመረተው የድንጋይ ከሰል ግብአት መካከል ያለውን ልዩነትም እንዳስረዱት፤ከውጭ የሚገባው የድንጋይ ከሰል የሚቀርብበት የጥራት መጠን ወይንም ለማቃጠል ያለው የኃይል መጠን የሚዋዥቅ(ፍላክችዌትአያደርግም) አይደለም። ቢያጋጥም እንኳን በከፍተት የሚጠቀስ አይደለም።

የሀገር ውስጥ የድንጋይ ከሰል ግን የመዋዠቅ ባህሪ ያለውና የማቃጠል ኃይሉም አነስተኛ ነው። በዋጋ ግን ከውጭ በግዥ ከሚገባው የድንጋይ ከሰል አነስተኛ ነው። ዋጋው ቢቀንስም አገልግሎቱ አነስተኛ ከሆነ ከጥቅሙ ጉዳቱ ያመዝናል። የማቃጠል ኃይሉ አነስተኛ የሆነው በተፈጥሮ ነው።

ስለዚህ‹‹በኔፊኬሽን ፐላንት) ያስፈልጋል። ወይንም ጥሬ ዕቃውን ፈጭቶ፣አጥቦና አድርቆ የሚያቀርብ ድርጅት መኖር አለበት። መንግሥትም በዚህ መልኩ የሚቀርብበትን ሁኔታ ለማመቻቸት ነበር ጥረት ሲያደርግ የነበረው። አቶ ሀይሌ በዚህ መልኩ እስካሁን የአምራች ኢንደስትሪውን ፍላጎት የሚያሟሉ ድርጅቶች ስለመኖራቸው እና መንግሥት በ2015ዓም ሙሉ ለሙሉ በሀገር ውስጥ አቅርቦቱን ምቹ ለማድረግ ይችላል የሚል ጥርጣሬ አላቸው።

በኢትዮጵያ ውስጥ ከሚገኙ የሲሚንቶ አምራች ኢንደስትሪዎች መካከል ትላልቅ የሚባሉት ደርባ፣ሙገር፣ዳንጎቴ፣መሶቦ ኢንደስትሪዎች ሲሆኑ፣በአሁኑ ጊዜ መሶቦ ሲሚንቶ ፋብሪካ በሥራ ላይ ባይሆንም እያንዳንዳቸው በቀን አምስትሺ ቶን ሲሚንቶ የማምረት አቅም ስላላቸው በቀን ወደ ሰባት መቶ ቶን (ሰባትሺ ኩንታል)፣በወር ደግሞ 20ሺ ቶን የድንጋይ ከሰል ግብአት ይፈልጋሉ። ናሽናል ሲሚንቶ ፋብሪካም እስከ 13ሺ ቶን ይጠቀማል።

በመሆኑም በሀገር ውስጥ ጥሬ ዕቃውን ፈጭተው፣አጥበውና አድርቀው ለኢንደስትሪዎቹ የማቅረብ አቅም ያላቸው ድርጅቶች መፍጠር ይጠበቃል። የሀገር ውስጥ ምርትን መጠቀም ጥቅም እንዳለው ሁሉ ሊያስከትል የሚችለውንም ክፍተት ለይቶ ማወቅ ያስፈልጋል። ግብአቱ በጥራትና በመጠን ካልቀረበ የምርት መቀነስና የዋጋ ንረት ያስከትላል።

እንደ አቶ ኃይሌ ገለጻ፣በአሁኑ ጊዜ የድንጋይ ከሰል ከውጭ በግዥ እየገባ አይደለም። አምራቹ ቀድሞ የያዘውን ክምችትና ፈሳሽ ጋዝ በመጠቀም ነው በማምረት ላይ የሚገኘው። ጋዝ በሊትር ወደ 49 ብር ነው የሚሸጠው፤ ይሄ ደግሞ አምራቾችን አዋጭ አያደርጋቸውም። እንደየአምራቹ የማምረት ሁኔታ ቢለያይም በቀን እስከ 120ሺ ሊትር ጋዝ የሚያስፈልገው አምራች ድርጅት አለ። አሁን ባለው የጋዝ በሊትር የመሸጫ ዋጋ ለማምርት አያዋጣም። አቅርቦቱም ቢሆን የተቆራረጠ ነው። የምርት ዋጋን ያስወድዳል። ይህንን ተግዳሮት መቅረፍ የሚቻለው ቤኔፊኬሽን ፕላንት ላይ ጠንክሮ መሥራት ነው።የጥሬ ዕቃ ሀብቱ የሚገኝባቸው አንዳንድ የሀገሪቱ አካባቢዎችም



**ማእድን ሚኒስቴር የድንጋይ ከሰል ለማምረት ፈቃድ ለሰጣቸው ኩባንያዎች አስፈላጊውን ድጋፍ እና ክትትል ማድረግ ይጠበቅበታል**

የፀጥታ ስጋት ያለባቸው መሆኑም የራሱ ተጽዕኖ እንዳለው ጠቁመዋል።

የሀገር ውስጥ የድንጋይከሰል የማቃጠል ኃይሉ አነስተኛ የመሆን ጉዳይ ብዙዎች የሚያነሱት ቢሆንም አቅርቦቱ ካለ አምራቾቹ በራሳቸው የኃይል ማስተካከል በማድረግ የሚጠቀሙበት ዕድል ስለመኖሩ አቶ ኃይሌ ላቀረብኩላቸው ጥያቄ በምላሻቸው ማስተካከያው የውጭውን ከሀገር ውስጥ ጋር በማቀላቀል ወይንም ደግሞ የሀገር ውስጡን ከናፍጣ ጋር በማደባለቅ የተሻለ ውጤት እንዲያመጣ በማድረግ ጥቅም ላይ ይውላል።ናፍጣ ዋጋው ውድ እየሆነ ስለሚሄድ ከናፍጣ ጋር አደባልቆ መጠቀሙ አዋጭ አይሆንም።ይሄ ጊዜያዊ ዘለቄታዊ መፍትሄ አይሆንም።

አሁን ባለው የውጭ ምንዘሪ አቅርቦት ችግር፣ከውጭ የሚገባውም የድንጋይ ከሰል ዋጋ መናርና መንግሥትም የግብአት አቅርቦቱ ሙሉ ለሙሉ በሀገር ውስጥ እንዲሆን በአቋም እያደረገ ስላለው እንቅቅስቃሴ ያላቸውን ሀሳብና እንደመፍትሄም የሚጠቁሙት ካለ አቶ ኃይሌ ላቀረብኩላቸው ጥያቄ ‹‹ዋናው መፍትሄ በሀገር ውስጥ የተጀመረውን የቤኔፊኬሽን ፕላንት ፕሮጀክት መጨረስ ነው። ይህ ከሆነ ሳይቆራረጥ ግብአቱን ማግኘት ይቻላል››ሲሉ ምላሽ ሰጥተዋል።

ማዕድን ሚኒስቴር የድንጋይ ከሰል አልምተውና አቀነባብረው ለአምራች ኢንደስትሪዎች የማቅረብ አቅም ላላቸው ባለሀብቶች የድንጋይ ከሰል ሀብቱ በሚገኝባቸው የሀገሪቱ ክፍሎች ውስጥ እንዲሰሩ ፍቃድ ከሰጣቸው መካከል ሰን ማይኒንግ ትሬዲንግ ኃላፊነቱ የተወሰነ የግል ኩባንያ አንዱ ነው፤ ኩባንያው በደቡብ ብሄር፣ብሄረሰቦችና ህዝቦች ክልል በጉራጌ ዞን አበሽጌ ወረዳ ጊቤ ቀበሌ ውስጥ እንዲሰራ ነው ፍቃድ የተሰጠው።

ኩባንያው የሚገነባው ፋብሪካ ተጠናቅቆ ማምረት ሲጀምር በወር ስምንት መቶ ሺ ቶን የድንጋይ ከሰል የማምረት አቅም እንደሚፈጥርና የታለመውን የውጭ ምንዛሪ ወጭ በማዳን ሚና እንደሚኖረው እንዲሁም ለአካባቢው ወጣቶች የሥራ ዕድል በመፍጠርም የሥራ አጥነትን ክፍተት በመሙላት ድርሻ እንደሚኖረውም ሚኒስቴር መስሪያቤቱ በወቅቱ በድረገጹ ማስነበቡ ይታወሳል።

በደቡብ ብሄር፣ብሄረሰቦችና ህዝቦች ክልል የጉራጌ ዞን ውሃ፣መአድን እና ኢነርጂ መምሪያ ኃላፊ አቶ ፍሰሐ ዳምጠውም በጉዳዩ ላይ እንዳብራሩት፤እንደሀገር የኢኮኖሚ አንቀሳቃሽ ተብሎ ከተያዘው ዘርፍ አንዱ የማእድን ልማት እንደሆነ በመገንዘብ ዞኑም የተቀመጠውን የልማት አቅጣጫ በማሳካት ረገድ የበኩሉን ድርሻ ለመወጣት በአካባቢው የሚገኝ የማእድን ህብትን ከመለየት ጀምሮ ጥቅም ላይ የሚውልበትን መንገድ በማመቻቸት ተንቀሳቅሷል።

ዞኑ ከዲላ፣ሐዋሳና አርባምንጭ ዩኒቨርሲቲዎች ጋር በመተባበር ዞኑ ስላለው የማዕድን ሀብት ጥናት በማካሄድ ሀብቱን ለይቷል። በጥናት ግኝቱም በስምጥ ሸለቆ ኬላ ተብሎ በሚጠራው አካባቢ በሚገኙ ሶዶ፣ደቡብ ሶዶ፣በከፊል መስቃን እንዲሁም በጊቤ ተፋሰስ አብሽጌና እነሞር ወረዳዎች የድንጋይ ከሰልን ጨምሮ ለኢንዱስትሪ ግብአት የሚውሉ የማዕድን ሀብቶች መኖራቸውን አረጋግጧል።

ኩባንያው ግንባታ የሚያከናውንበትን ቦታ አመቻችቷል። የመሠረት ድንጋይም ተጥሏል። ለቅድመ ግንባታ የሚያስፈልጉ እንደ አፈር ምርመራና የተለያዩ ተግባራት ተከናውነው ዝግጁ ሆኖ በአጭር ጊዜ ውስጥ የድንጋይ ማጠቢያ ማሽን ተከላ ተከናውኖ ወደ ምርት ይገባል የሚል እቅድ እንደነበርም አቶ ፍሰሐ ከስድስት ወር በፊትም በጉዳዩ ላይ ሰጥተውናል።

አቶ ፍሰሐ እንዳሉት፤ ተስፋ የተጣለበት የድንጋይ ከሰል አልምቶ አቀነባበር ለአምራቾች የማቅረቡ ሥራ የውሃ ሽታ ሆኖ ቀርቷል። የዞኑ መምሪያ ኩባንያው ወደ ሥራ ያልገባበትን ምክንያት ለማጣራት ባደረገው ጥረት ኩባንያው ወደሥራ ላለመግባቱ የሚያነሳው የድንጋይ ከሰል ማጠቢያ ማሽኑን ከውጭ ለማምጣት የውጭ ምንዛሪ እጥረት ያጋጠመው መሆኑን ነው።

አቶ ፍስሐ ኩባንያው ከማዕድን ሚኒስቴር ፈቃድ ሲወስድ የውጭ ምንዛሪ አቅርቦት ችግሩ እንደሚፈታለት ሳያረጋግጥ ወደ ሥራው አይገባም የሚል እምነት አላቸው። የዞኑ መምሪያ ክልሉም ሆነ ማዕድን ሚኒስቴር እንዲያውቁት በቃልም በደብዳቤም በማሳወቅ መፍትሄ እንዲያገኝ እያደረገ መሆኑን ይገልጻሉ። በግላቸውም የማዕድን ሚኒስትሩን በአካል አግኝተዋቸው በጉዳዩ ላይ መነጋገራቸውንና ሚኒስትሩም በማወያየትና ደብዳቤ በመጻፍም እርምጃ እንደሚወሰድ በቃል እንደገለጹላቸው ነው የተናገሩት። ‹‹መሬት ለኢኮኖሚያዊ ልማት ዕድገት ታሳቦ ለኢንቨስትምንት እንዲውል ህዝብ የሚጠቀምበት መሬት ሲሰጥ ለታለመለት አላማ ካልዋለ ተጠያቂነት ያመጣል። ይህንን መሠረት በማድረግ ነው ለሚመለከተው አካል በየደረጃው ለማሳወቅ የተገደድነው››ብለዋል።

አቶ ፍሰሐ፣በደቡብ ክልል ብሄር፣ብሄረሰቦችና ህዝቦች ክልል የጉራጌ ዞን ውሃ፣ማዕድንና ኢነርጂ መምሪያ አወ/ ው/ 51/ 14/ ቀን 8 /11 /2014ዓም ለደቡብ ብሄር፣ብሄረሰቦችና ህዝቦች ክልል በደብዳቤ ያሳወቀበትን፣በደቡብ ብሄር፣ቤሄረሰቦችና ህዝቦች ክልላዊ መንግሥት ማዕድንና ኢነርጂ ኤጀንሲ ደግሞ በሀ/350/መ/152/በቀን 14/11/2014ዓም ለፌዴራል ማዕድን ሚኒስቴር በደብዳቤ ያሳወቀበትንም ሁኔታ ገልጸዋል።

በጉዳዩ ላይ የማእድን ሚኒስቴር የኮሚኒኬሽን ዳይሬክተር ሞባይል ስልክ ላይ ብንደወልም ስልኩ ሊነሳ ባለመቻሉ ምላሽ ማግኘት አልቻልንም።

መዝናኛ

# የብዕር ጠብታ

## ትንቅንቅ

በትረ ሙሴ (መልከ ኢትዮጵ)

ሕይወት ትንቅንቅ ናት:: ከራስ ጋር፣ ከፈጣሪ ጋር፣ ከተፈጥሮ ጋር ከነዚህ ሁሉ ጋር:: ከሁሉም ግን ከራስ ጋር የሚደረግ ትንቅንቅ ይከፋል:: ከራስ ጋር ትንቅንቅ መልስን ደብቆ፣ እውነትን ሸሽጎ ነው:: በማይገኝ መልስና በማይደረስ እውነት ውስጥ ቆሞ ላለመውደቅ ትግል እንደምን ይቻላል? ሰው ራሱን ታግሎ እስካላሸነፈ ድረስ ሁሌም ትንቅንቅ ውስጥ ነው:: እናም ከራሱ ጋር እንዲህ ያስባል:: በተለይ መኖር አፈር ከድሜ ሲያስግጠው፣ በተለይ እብድ እናቱ ፊት ቆሞ የማይነቃ ሴትነቷን ሲያስብ::

አስራ አራት አመቱ ነው..አስራ አራት የመከራ ቀንበሮች ጠይም ፊቱ ላይ ተስለዋል:: ተስሞ ያልበቃው ጉንጭ፣ ቦርቀው ያልጠገቡ እግሮች ዛሬም ድረስ ልጅነት ያምራቸዋል..ዛሬም ድረስ መሄድ ይናፍቃሉ:: እንዳያልፈው ልጅነቱ ላይ የተጋደመ የሕይወት ሰንኮፍ አለ:: ተናንቆ ያልተሻገረው.. ተፍገምግሞ ያላለፈው:: ከዚህ ርቆ መኖር ይፈልጋል::

ስድስት ሰዓት አለፍ ሲል ከእናቱ ሸሽቶ መንገድ ጀመረ:: የምግብ ፌስታሉን እንደያዘ አንድ ሆቴል በር ላይ ቆመ:: በሀሳቡ ሁለት ሴቶች ይመላለሳሉ:: አንድ ዓይነት ተፈጥሮ፣ አንድ ዓይነት ሴትነት ተሸክመው ግን የተለያየ ልብ ያላቸው ሴቶች:: አንዷ ደስታው ናት..እንዲህ እንደ አሁኑ በሕይወት ትንቅንቅ በአደፈ ልብስና አካሉ ጋር የምግብ ፌስታሉን ይዞ በር ላይ ሲቆም መቼም በማይረሳው፣ በሕይወቱ ሙሉ በሚከተለው ትህትና ፌስታሉን በምግብ ሞልታ ትሸኘዋለች:: ሩቅ ከደረሰ በኋላ እሷን ለማየት ዞሮ ያውቃል:: ሲዞር እዛው በር ላይ ምግብ የያዘችበትን ሳህን እንደያዘች ትሁት በሆነ ፊት ወደ እሱ እያየች ያገኛታል:: እናቱ ጋ እስኪደርስ ድረስ ሀሳቡ እሷ ናት:: እና ደግሞ አንድ ሴት አለች..ከዚች ሴት የራቀች፣ ማጣት ላገረጣት ነፍሱ መከራ የሆነች:: እንዲህ እንደ አሁኑ የምግብ ፌስታሉን ይዞ በር ላይ ሲቆም ድንገት ትመጣና ‹ሂድ ከዚህ..! ትለዋለች:: ከበር ሸሽቶ ሩቅ እስኪደርስ ድረስ እንዳይመለስ በአይኗ ትጠብቀዋለች:: ወፍራም ናት..በእሷ ምክንያት ወፍራም ሴቶች ሁሉ ክፉዎች ይመስሉታል:: እሷ ካባረረችው በኋላ ባዶ እጁን ወደ እናቱ ይሄዳል:: እናቱ መጽናኛው ናት:: እናቱ እንደዛች ወፍራም ሴት ሕይወትና ሁኔታዎች ሲያሰቃዩት ማረፊያው ናት:: የምታደርገው ሳይገባው፣ የምትለው ሳይሰማው ተነስታ እስኪታባርረው ድረስ ሄዶ አጠገቧ ቁጭ ይላል::

ዛሬም ሁለት ሴቶች በሀሳቡ እየተመላለሱ ሆቴሉ በር ላይ ቆመ:: ከሆቴሉ ውስጥ ብዙ ሳቆች ይሰሙታል:: ጥጋብና ድሎት ጸንሶ የወለዳቸው ሳቆች:: ደስታ ምን እንደሆነ አያውቅም..ደስታ ማለት ምን ማለት እንደሆነ አልገባውም:: ከሆቴሉ ውስጥ የሚሰማው ሳቅ ግን የነፍሱ ማረፊያ ሆነ:: ሳቅ አማረው..መከራውን ሁሉ ረስቶ እንደነዚያ ነፍሶች መሳቅ..መፍነክነክ አማረው:: በሕይወቱ ተመኝቶ ያጣው ይሄን ነበር:: አስቆት የሚያውቅ የለም:: የምታስቀው አንድ ነፍስ ነች..እዚህ ሆቴል በር ላይ ቆሞ፣ ነጭ በጥቁር የመስተንግዶ ልብስ ለብሳ ፌስታሉን በምግብ የምትሞላለት ነፍስ:: የምታስቀው እሷ ናት:: ኅዘን በሚተናነቀው በማይስቅ ፊት፣ አቆፋዳውን በምግብ ትሞላለታለች:: ያኔ ይስቃል..ያኔ እየሳቀ ወደ እናቱ ይገሰግሳል:: በዚያች አስተናጋጅ ነፍስ ብዙ ጊዜ ስቋል:: ግን ሰሞኑን አላያትም...ያለፉትን ሦስት ቀናት እየደነበረ ያለው በወፍራሟ ሴት ነው:: ዛሬም ሳቅ አማረው..ደጓን ሴት ሽቶ በር በር ያይ ጀመር::

ዓይኖቹ የሚወጣውንና የሚገባውን እየቀላወጡ ብዙ ቆየ:: ከዛ ሁሉ ሳቂታ ፊት መሀል ለእሱ የሚሆን አንድ ሰው መጥፋቱ አስከፋው:: የሚያየው የለም.. የሚመጣው ሁሉ እየገፋው ያልፋል:: መሞት ጀመረ..በነፍሱ ላይ የለኮሳት የተስፋ ጭላንጭል መክሰም ጀመረች:: ሆቴሉ በር ላይ እንደቆመ ጀምበር ሸሸችው:: ከሆቴሉ የሚሰማው ሳቅ ግን አሁንም ይሰማዋል:: ተንቆራጠጠ..በዚህ መሀል ወደ እሱ የሚረግጥ ኮቴ ሰማ:: ይሄን ኮቴ ያውቀዋል..እዛ የሆቴል በር ላይ በተመላለሰባቸው ጊዜያቶች ውስጥ ከዚህ ኮቴ ጋር ተቆራኝቷል:: የወፍራሟ ሴት ኮቴ ነው..እንዲህ ትመጣና ነው ታግሎ ባልጣለው ራሱ ውስጥ የምትሸነቀረው:: እንዲህ ትመጣና ነው ሳቅ የናፈቃት ነፍሱን የምታጸልምበት:: እንዲህ ትመጣና ነው ከጠበቀው ከብዙ ተስፋው የምታቆራርጠው::

ሆቴሉ በር ላይ አያት:: ቁመቷን ከፍ ያደረገ ባለታኮ ጫማ ተጫምታለች:: ጉልበቷ ላይ የቀረ ደረቷን የሚያሳይ ሰማያዊ ቀሚስ ለብሳለች:: ጸጉሯ በአጭሩ ተቆርጦ ለራስ ቅሏ በሚመች ሁኔታ ወዲያና ወዲህ ተለጥልጧል:: ጫማዋ እንዳይጥላት ቀስ እያለች በመራመድ ወዳለሁበት ተጠጋች:: ልትናገረኝ አፏን ስታሞጠሙጥ ከአንድ ወዳጇ ጋር ተገናኘችና ለኔ ባሞጠሞጠችው ከንፈሯ የእሱን ጉንጮች ሳመቻቸው:: ለጥቂት ጊዜ ተሳሳቁ:: ትቷት ወደ ሆቴሉ ሲገባ እሷም ወደ እኔ ተመለሰች:: ሳቋን አክስማ ‹ስማ አንተ! አለችኝ::

የሆቴሉን አንድ ጥግ ይዤ አየኋት::

‹አትሰማም እንዴ! ሁለተኛ እንዳትመጣ አላልኩህም?

ዝም አልኩኝ..ምን እንደምልና ምን እንደሚባል አላውቅም:: ሰዎች ሲናገሩኝ የኖርኩ ሰው ነኝ:: ከእናቴ ጋር እያባረሩንና እየገፉን የኖርኩ ነኝ:: ሰዎች በእኔና በእናቴ ላይ እንደፈለጉ ናቸው..ይቺንም ሴት ምን እንደምላት አላውቅም:: አይደለም ይቺን ቀርቶ ያቺን የነፍሴን ሳቅ አስተናጋጅ እንኳን በዛ ሁሉ ደግነቷ ውስጥ ምንም ብያት አላውቅም:: በእጄ ያንከረፈፍኩትን ፌስታል በመዳፌ እያሚሸሸኩ ዝም ብዬ አየኋት::

‹ምን ይመስላል! አመዳም› አለችኝ::

ዝም አልኩኝ..በዓይኖቼ እየሰረኩ አያታለሁ:: የተጸየፉኝ ዓይኖቿ ይታዩኛል:: የገፉኝ..የሸሸኝ ልቧም::

‹ሁለተኛ ድርሽ እንዳትል..ሂድ አሁን ከዚህ› ስትል ፊቷን በጥላቻ ሞልታ፣ በእጇ መሄጃዬን እየጠቆመች ተናገረችኝ::

ከዛ በኋላ እዛ ሆቴል አልተመለስኩም..ሁለት ሴቶች በነፍሴ ላይ አፍርቼ ከዛ ስፍራ ተገለልኩ:: ከዚህ እዛ እስክደርስ፣ ይሄን ዘመን አልፌው ሌላ እስክሆን ድረስ እኚህ ሁለት ነፍሶች አይረሱኝም:: በሄድኩበት ሁሉ ይከተሉኛል:: ‹ሰው የሚሞተው ሰው ያጣ ቀን ነው:: ሕይወት የሚታክተው ቀና ልብ ሲርቀው ነው› እንዲህ እያሰብኩ ራሴን አገኘሁት:: ይሄ ሃሳብ እንዴት ወደ ልቤ እንደመጣ አላውቅም::

ባዶ እጄን ወደ እናቴ ሄድኩ:: ወደ እናቴ ስሄድ ከፊት ለፊቴ ስሙን የማላውቀው ካቴድራል ይታየኛል:: ርምጃዬን አንቀርፍፌ ተጠጋሁት:: ሕይወት ያስተማረችኝ ዝምታ አይደል? አሁንም ምን እንደምል አላውቅም:: እግዜር ፊት ቆሜ ዝም አልኩኝ::

በርቀት ጀርባው ላይ የተቀደደ ነጠላ ለብሳ ያቺን መልካም አስተናጋጅ አየኋት..እግዜር ለካ ዝምታ ይሰማል..

# ዓለም አቀፍ

## ኬንያ በሕገ ወጥ የዱር እንስሳት ‘አዘዋዋሪነት’ የጠረጠረችውን ግለሰብ በቁጥጥር ስር አዋለች

የኬንያ ፖሊስ በድንበር ተሻጋሪ ሕገ ወጥ የዱር እንስሳና አደንዛዥ ዕፅ ዝውውር ላይ ከተሰማራ ቡድን ጋር ግንኙነት አለው ተብሎ ተጠርጥሮ በአሜሪካ ፍርድ ቤት ክስ የተመሠረተበትን ግለሰብ በቁጥጥር ስር አዋለ። አብዲ ሁሴን አህመድ ወይም በቅጽል ስሙ አቡ ካዲ፤ በማዕከላዊ ኬንያ ሜሩ ተብሎ በሚጠራ አካባቢ ነበር ማክሰኞ ዕለት በቁጥጥር ስር መዋሉን ፖሊስ የገለጸው።



አሜሪካ ግለሰቡን ለማግኘት የሚረዳ መረጃ ላለው ሰው የአንድ ሚሊዮን ዶላር የወሮታ ክፍያ አዘጋጅታ ነበር። ተከሳሹ አህመድ እ.ኤ.አ. በ2019 በኒውዮርክ ፍርድ ቤት የአውራሪስ ቀንድ እና የዝሆን ጥርስን በሕገ ወጥ መልኩ ለማዘዋወር በማሴር ወንጀል ክስ ተመስርቶበት ነበር። ከዚህ በተጨማሪም ቢያንስ አንድ ኪሎ ሄሮይን ለማዘዋወር በማቀድ ወንጀልም ሌላ ክስም ቀርቦበታል። ከእርሱ በተጨማሪ ሌሎች ሦስት ሰዎች ክስ ተመስርቶባቸው ነበር።

ለሰባት ዓመታት ያህልም ከኬንያ፣ ከኡጋንዳ፣ ከዲሞክራቲክ ሪፐብሊክ ኮንጎ፣ ከጊኒ፣ ከሞዛምቢክ፣ ከሴኔጋል እና ከታንዛኒያ ሰባት ሚሊዮን ዶላር የሚገመት 190 ኪሎ ቀንድ እና 10 ቶን የዝሆን ጥርስ በድብቅ ለማዘዋወር ማሴራቸው ተዘግቧል። ለዚህም ሲባል ከ35 በላይ አውራሪሶች እና ከ100 በላይ ዝሆኖችን በሕገ ወጥ አደን ኢላማ ማድረግን ይጠይቃል።

ቀንዱ እና የዝሆን ጥርሱ ለአሜሪካ እና ደቡብ ምሥራቅ እስያ ላሉ ገዥዎች ለመሸጥ ያሰበ እንደነበርም ተዘግቧል። ከሦስት ወራት በፊትም የአሜሪካ እና የኬንያ ባለሥልጣናት ተከሳሹን አህመድ በቁጥጥር ስር ለማዋል የሚያስችል መረጃ ለማግኘት ያሰበ ጥሪ ለኬንያውያን አቅርበው ነበር።

አሜሪካ አህመድን እና በሌላ በሕገ ወጥ የሰዎች ዝውውር የተጠረጠረ በድሩ አብዱል አዚዝ ሳሌህ የተሰኘ ግለሰብን ጨምሮ እያንዳንዳቸውን ለመያዝ የሚረዳ መረጃ ላለው ሰው አንድ ሚሊዮን ዶላር ሽልማት እንደምትሰጥ ቃል ገብታ እንደነበር ይታወሳል።

ሕገ ወጥ የሰዎች ዝውውር የተጠረጠረው ሳሌህ ከሳምንት በኋላ በቁጥጥር ስር ውሎ ነበር። ይህ የአውራሪስ ቀንድ ለማግኘት የሚደረጉት አደኖች የእንስሳቱን ቁጥር ለመመናመን ምክንያት እንደሆነ ይታመናል። ቀንዱ የቻይና ባሕላዊ መድኃኒትን ለማዘጋጀት ይጠቅማል ተብሎ መታሰቡ አደኑን ለመከላከል የሚደረጉ የመንግሥት ሙከራዎችን አስቸጋሪ ሆነው እንዲቀጥሉ አድርጓል።

እንዲሁም የዝሆን ጥርስ የመደብ እና የሀብት መገለጫ ሆኖ እስካሁን ድረስ መወሰዱ አደኑ ተጠናክሮ ለመቀጠሉ ምክንያት ነው። ባለፈው ዓመት የተደረገ አንድ ጥናት እንደሚያሳየው በሞዛምቢክ የዝሆን ጥርስን ለማግኘት በሚደረጉ ተግባራት ምክንያት ጥርስ አልባ ዝሆኖች እንዲበራከቱ ምክንያት ሆኗል መባሉን ቢቢሲ ዘግቧል።




## በአሜሪካ ታይቶ የማይታወቅ የዋጋ ጭማሪ በመከሰቱ ዜጎች ወደ ነፃ ምግባ ማዕከላት ለመሄድ ተገደዋል

በአሜሪካ የመሠረታዊ ፍጆታ ዕቃዎች ዋጋ ታይቶ በማይታወቅ ሁኔታ መጨመሩን ተከትሎ ዜጎች ወደ ነፃ ምግባ ማዕከላት እንዲሄዱ መገደዳቸው ተገልጿል፡፡ አሁን ላይ በአሜሪካ በመሠረታዊ የፍጆታ ዕቃዎች ላይ ከፍተኛ የዋጋ ጭማሪ በመከሰቱ በርካታ ዜጎች በአስቸጋሪ የኑሮ ጫና ውስጥ እንደሚገኙ ፎክስ ኒውስ ዘግቧል፡፡

በተፈጠረው ከፍተኛ የዋጋ ግሽበት ምክንያትም በርካታ ቤተሰቦች መሠረታዊ የፍጆታ ዕቃዎችን በመደበኛ ሱቆች መሸመት አለመቻላቸው ተመላክቷል፡፡ ይህን ተከትሎም ዜጎች መንግሥት መሠረታዊ የፍጆታ ዕቃዎችን በነፃ የሚያከፋፍልባቸውን የምገባ ማዕከላት አጨናንቀዋል ነው የተባለው፡፡

በዚህ ሳቢያም አሁን ላይ በአሜሪካ የሚገኙ 40 በመቶ የሚሆኑት የምገባ ማዕከላት የዜጎች ፍላጎት በመጨመሩ ከፍተኛ የአቅርቦት ችግር ያጋጠማቸው መሆኑ በዘገባው ተመላክቷል፡፡ የዋጋ ጭማሪው በተለይ ዝቅተኛ ገቢ ላላቸው የኅብረተሰብ ክፍሎች ተስፋ አስቆራጭ መሆኑ የተጠቆመ ሲሆን፣ ሁኔታው በኮቪድ-19 ወረርሽኝ ጊዜ ከነበረው በእጅጉ እንደሚከፋ ተጠቅሷል፡፡

በርካታ አሜሪካውያንም የዕለት ጉርሳቸውን ከወርሃዊ ገቢያቸው ጋር ለማጣጣም በመደበኛ ሱቆች አስፈላጊ የሚባሉትን የፍጆታ ዕቃዎች ብቻ መርጠው ለመግዛት እየተገደዱ መሆኑ ተነግሯል፡፡ ለተጨማሪ እርዳታም ዜጎች መሠረታዊ የፍጆታ ዕቃዎች በነፃ ወደ ሚከፋፈሉባቸው የመንግሥት የምገባ ማዕከላት ማቅናት ግዴታ እየሆነባቸው ነው ተብሏል፡፡

The Ethiopian Herald
አዲስ ዘመን
BARIISAA
ወጋሕታ
BAKKALCHO
የኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት
ዌብሳይት:- www.press.et
ፌስቡክ:- Ehiopian Press Agency

አዲስ ዘመን
ሐሙስ
ስፖርት



ይህ ቦታ
ለማስታወቂያ ክፍት ነው!

# ወጣቱ ኢትዮጵያዊ አትሌት በካሊ ሁለተኛውን የብር ሜዳሊያ አስመዘገበ

**ብርሃን ፈይሳ**

የደቡብ አሜሪካ የስፖርት ማዕከል በሚል ትታወቃለች። ምክንያቱ ደግሞ የትኛውንም ስፖርታዊ ክንውን የማስተናገድ አቅም ያላት አህጉር በመሆኗ ነው። የኮሎምቢያዋ መዲና ካሊም ባለፉት ጥቂት ቀናት ይህን አስመስክራለች። ካሊ 38ሺ ሰዎችን የመያዝ አቅም ባለው ስታዲየሟ የዓለም ከ20 ዓመት በታች አትሌቲክስ ቻምፒዮናን በማስተናገድ ላይ ትገኛለች። ምናልባትም በሕይወት ዘመን አንዴ ሊገኝ በሚችለው የዚህ ውድድር ተሳትፎን ለማድረግም በሺዎች የሚቆጠሩ ወጣቶች በከተማዋ ታድመዋል። እአአ በ2015 የዓለም ከ18 ዓመት በታች ውድድርን ያስተናገደችው ካሊ ለስድስት ቀናት የሚዘልቅ ድግሷን ለማጠናቀቅም አንድ ቀን ብቻ ቀርቷታል።

ወጣትና ተተኪ አትሌቶችን የሚያፎካክረው የዓለም ከ20 ዓመት በታች አትሌቲክስ ቻምፒዮና ቀጣይ የአትሌቲክሱ ዓለም ከዋክብትን ከዓላማቸው የሚያገናኝ ድልድይ ነው። በመሆኑም ወጣት አትሌቶች ህልማቸውን እውን ለማድረግ እንደ መንደርደሪያ ይጠቀሙታል። በውድድሩ ላይ እየተካፈሉ የሚገኙ አገራትም ባለፉት ቀናት በርካታ ሜዳሊያዎችን በማስቆጠር ሽሚያ ውስጥ አልፈዋል። ከእነዚህ አገራት መካከል አንዷ ኢትዮጵያ ናት። ኢትዮጵያ ከውድድሩ መጀመሪያ ቀን አንስቶ ሜዳሊያዎችን ማስመዝገብ የቻለች ሲሆን ባለፈው ረቡዕም የሜዳሊያ ስብስቧን ከፍ ያደረገችበት ውጤት በወንዶች 1ሺ500 ሜትር




በ1ሺ500 ሜትር የብር ሜዳሊያ ለአገሩ ያስገኘው ወጣቱ አትሌት ኤርሚያስ ግርማ፤

አሳክታለች። በርቀቱ ከብር ሜዳሊያ በተጨማሪ የዲፕሎማም ደረጃም አግኝታለች።

በ1ሺ500 ሜትር የፍጻሜ ውድድር በካሊ በጣለው ከባድ ዝናብ ምክንያት አስቀድሞ ሊካሄድ ከተያዘለት መርሃ ግብር በሁለት ሰዓት ዘግይቶ ነበር የተካሄደው። ጠንካራ ፉክክር ባስተናገደው በዚህ ውድድር በኬንያውያን እና ኢትዮጵያውያን አትሌቶች መካከል አስደናቂ ፉክክር ታይቷል። በመጨረሻም ፈተና የሆኑበትን ሁለት ኢትዮጵያውያን አትሌቶችን በመርታት ኬንያዊው ሬይኖልድ ኪፕኮሪር ቼሩዮት አሸናፊ ሊሆን ችሏል። አትሌቱ ውድድሩን የፈጸመበት ሰዓትም ቀድሞ ከነበረው የግል ፈጣን ሰዓቱ በ4 ሰከንዶች የተሻለ ሆኖ ተመዝግቦለታል። ጥቂት ሰከንዶችን ዘግይቶ የገባው የ17 ዓመቱ አትሌት ኤርሚያስ ግርማ በበኩሉ ኬንያዊውን ተከትሎ የብር ሜዳሊያን ለማጥለቅ የፈጀበት ሰዓት 3:37.24 ሆኗል።

በውድድሩ የመጨረሻ ሜትሮች አስደናቂ ፉክክር ያሳየው የኢትዮጵያ ወጣቶች ስፖርት አካዳሚ ፍሬና የሲዳማ ቡና አትሌትክስ ክለብ አትሌት ኤርሚያስ፣ የአሯሯጥ ስልቱን ተከትሎ ከመነሻው በበርካታ የስፖርት ቤተሰቡ ከፍተኛ ግምት የተሰጠው ነው። ነገ በሚካሄደው የ800 ሜትር ውድድርም ይህ አትሌት ሌላ ስኬት እንደሚያስመዘግብም ይጠበቃል። ኬንያዊው ዳንኤል ኪማዮ ሦስተኛ ሆኖ ባጠናቀቀበት ውድድር ሌላኛው ኢትዮጵያዊ አትሌት አድሀና ካሳየ በ3:38.10 በሆነ ሰዓት አራተኛ ሆኖ በመግባት የዲፕሎማ ተሸላሚ መሆን ችሏል።

ትናንት በውድድሩ አራተኛው ዕለት የተለያዩ የማጣሪያ እና የፍጻሜ ውድድሮች ተደርገዋል። ከእነዚህ መካከል ኢትዮጵያውያን አትሌቶች የሚካፈሉባቸው የ800 ሜትር ወንዶች እና የሴቶች 1ሺ 500 ሜትር ማጣሪያዎች ተካሂደዋል። በጉጉት ሲጠበቅ የነበረው የ3ሺ ሜትር የሴቶች መሰናክል ውድድር ሌሊቱን ተደርጓል። በአሪጎኑ የዓለም ቻምፒዮና ተሳታፊ የነበረችውና በሳምንት ልዩነት በዚህ የወጣቶች ቻምፒዮና በድጋሚ ተካፋይ በመሆን ላይ የምትገኘው አትሌት ሲምቦ አለማየሁ ለአሸናፊነት ተጠባቂ ከሆኑት መካከል ቀዳሚዋ ናት። በዚህ ርቀት ኬንያዊቷ አትሌት ፌይዝ ቼሮቲችም ጠንካራ ተፎካካሪ እንደምትሆን ትጠበቃለች። የ17 ዓመት ታዳጊ የሆነችው ሲምቦ ባለፈው የፈረንጆቹ ወር በፓሪስ በተካሄደው ዳይመንድ ሊግ ሁለተኛ የወጣችበት 9:09.19 የሆነ ሰዓት የግሏምርጥ ሲሆን፤ በዚህ ዕድሜም ፈጣን የሚባል ሰዓት ነው።

በዛሬው የአምስተኛ ቀን የውድድር ውሎም ከሚካሄዱት ውድድሮች መካከል የወንዶች 800 ሜትር ግማሽ ፍጻሜ እንዲሁም 3ሺ ሜትር ፍጻሜ ኢትዮጵያውያን አትሌቶች ይጠበቃሉ። ነገ በሚጠቃለለው በዚህ ውድድር ላይ ኢትዮጵያውያን አትሌቶች የሚሮጡበት አራት ውድድሮች ፍጻሜያቸውን ያገኛሉ።

ባለፈው ዓመት በኬንያ አስተናጋጅነት በተደረገው በዚህ ውድድር ላይ ኢትዮጵያ 12 ሜዳሊያዎችን በመሰብሰብ ሁለተኛ ብትሆንም በወርቅ ሜዳሊያዎች ተበልጣ በደረጃ ሰንጠረዡ አራተኛ ደረጃ ላይ መገኘቷ የሚታወስ ነው። በአጠቃላይ የውድድሩ ተሳትፎ ደግሞ 117 ሜዳሊያዎችን በማግኘት ከአሜሪካ፣ ኬንያ እና ሩሲያ ቀጥላ በአራተኛ ደረጃ ላይ ትገኛለች።

## ከኢ.ፌ.ዴ.ሪ የሕገ መንግሥት ጉዳዮች አጣሪ ጉባኤ
### ጋር በመተባበር የሚታተም

# የሕፃናት ሕገ መንግሥታዊ መብት ከአሳዳጊዎቻቸው የሃይማኖት ነፃነት አንፃር

**በያደታ ግዛው**

ውድ አንባብያን ባለፉት እትሞቻችን የሕገ መንግሥት ጉዳዮች አጣሪ ጉባዔ በተለያዩ ጊዜያት አጣርቶ የውሳኔ ሃሳብ አሳልፎባቸው በፌዴሬሽን ምክር ቤት የመጨረሻ ውሳኔ ያገኙ እና ለኅብረተሰቡ እና ለሕግ ባለሙያዎች በአስተማሪነታቸው የታመነባቸው ጉዳዮች ስናቀርብላችሁ ቆይተናል። በዛሬው እትማችንም ከአሳዳጊዎቻቸው የእምነት ነፃነት አንፃር የሕፃናት ሕገ መንግሥታዊ መብት ምን ይመስላል የሚለውን እናቀርብላችኋለን።

በኢ.ፌ.ዴ.ሪ ሕገ መንግሥት አንቀፅ 36 የሕፃናት ሕገ መንግሥታዊ መብቶች ተደንግገዋል። በሌላ በኩል ደግሞ በሕገ መንግሥቱ አንቀፅ 34 (4) መሠረት የግል እና የቤተሰብ ሕግን በተመለከተ በተከራካሪዎች ፍቃድ በሃይማኖት እና በባህል ሕጎች መሠረት የመዳኘት መብት ተከብሯል። እነዚህ ሁለቱን ሕገ መንግሥታዊ መብቶች በሚመለከት ለአጣሪ ጉባኤው የቀረበ እና የውሳኔ ሃሳብ የተላለፈበትን አንድ ጉዳይ እነሆ።

ለአጣሪ ጉባኤው የቀረበው ጉዳይ የተጀመረው በፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ሸሪዓ ፍርድ ቤት ሲሆን አቤቱታ ያቀረቡት ተጠሪ (የሕፃኗ አባት) ናቸው። የተጠሪ አቤቱታ በአመልካች (የሕፃኗ እናት) ላይ ባቀረቡት ሞግዚትነትን ይሰረዝልኝ አቤቱታ መነሻነት ነው። የአቤቱታው ይዘት በአጭሩ አመልካችና ተጠሪ መካከል የነበረው ጋብቻ በፍቺ የፈረሰው ግራ ቀኙ በሸሪዓ ፍርድ ቤት ለመዳኘት ፍቃድ ሰጥተው በነበረበት ጊዜ ነው። በዚህ መልኩ የግራ ቀኙ ጋብቻ ሲፈርስ በመካከላቸው የተወለደችው ሕፃን ልጅ እናቷ ጋር ወይም አመልካች ጋር እንድታድግ እና የሕፃኗ አባት ደግሞ በየወሩ ብር ሁለት ሺ 500 ቀለብ እንዲቆርጥ ተወስኖ ነበር። የሞግዚትነት ውሳኔ በፍ/ቤት በሚሰጥበት ወቅት አመልካች (የሕፃኗ እናት) የእስልምና እምነት ተከታይ ነበሩ።

ነገር ግን አመልካች (የሕፃኗ እናት) የሕፃኗ አሳዳጊነት ውሳኔ በፍርድ ቤት ከተሰጠ በኋላ የእስልምና እምነታቸውን ቀይረዋል። በዚሁ ምክንያት ተጠሪ (የሕፃኗ አባት) አሁን የሚያቀርቡት አቤቱታ ለአመልካች (ለሕፃኗ እናት) በፍርድ ቤት ተሰጥቷት የነበረው የሞግዚትነት ውሳኔ እንዲሰረዝ የሚል ነው። ለዚህም ምክንያቱ የሕፃኗ እናት የእስልምና እምነቷን ቀይራ ልጇንም የክርስትና እምነት ተከታይ እንድትሆን እያደረገች ነው በሚል ነው።

ክርክሩን የተመለከተው ፍርድ ቤቱም በሸሪዓው ሕግ የልጆች አሳዳጊ የሆነ ወገን ሊያሟላቸው ከሚገቡ መስፈርቶች ውስጥ አንዱ ልጅ አሳዳጊ የሆነው ወገን በእምነቱ የፀና መሆን እንዳለበት ነው። ነገር ግን የሕፃኗ እናት በተደጋጋሚ እምነታቸውን እንደሚቀያይሩና በአንድ እምነት የማይፀኑ መሆኑ በማስረጃ ተረጋግጧል። ስለሆነም የሕፃኗ እናት ከሸሪዓ ሕጉ አኳያ ሕፃኗን ለማሳደግ መስፈርቱን የማያሟሉ ስለሆነ በፍርድ ቤት ተሰጥቶአቸው የነበረው የአሳዳጊነት ውሳኔ ተሰርዞ ሕፃኗ ከአባቷ ጋር እንድታድግ እና እናት ልጇን በየ 8 ቀኑ አንድትጎበኝ ሲል ወስኗል። ውሳኔውም እስከ ፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት ድረስ ፀንቷል።

አመልካች ለሕገ መንግሥት ጉዳዮች አጣሪ ጉባዔ ባቀረቡት አቤቱታ በሕገ መንግሥቱ የተፈቀደውን ሃይማቴን የመቀየር መብቴን በሚፃረር መልኩ በፍርድ ቤቶች የልጄ አሳዳጊ እንዳልሆን የተሰጠው ውሳኔ ሕገ መንግሥታዊ መብቴን የሚጥስ ነው። ከፍቺ ውሳኔ በኋላም ሃይማኖቴን የቀየርኩ በመሆኑ በሸሪዓ ፍርድ ቤት ለመዳኘት ፍላጎት እንደሌለኝ ለችሎቱ በመግለፅ መቃወሚያዬን አቅርቤ ነበር። ከዚሁ ጋር በተያያዘ ቀደም ሲል የፌዴሬሽን ምክር ቤት በወይዘሮ ከድጃ በሽር እና በወይዘሮ ራንያ አህመድ በሰጠው የሕገ መንግሥት ትርጉም ውሳኔ ያለተከራካሪዎች ፍቃድ በሃይማኖት ፍርድ ቤት መዳኘት ኢ-ሕገ መንግሥታዊ ነው ብሏል።

ጉባዔውም አመልካች ያቀረቡትን አቤቱታ ከሕገ መንግሥቱ አንቀፅ 34/5/፣ 35/1/ እና /2/፣ 27 /1/ እና /3/፣ 36 /2/ አንፃር በመመርመር ሁለት መሠረታዊ የሕገ መንግሥት ነጥቦችን መሠረት አድርጎ የውሳኔ ሃሳብ አቅርቧል።

1ኛው አመልካች ከተጠሪ ጋር በፍች ከተለያዩ በኋላ ሃይማኖታቸውን በመቀየራቸው በሸሪዓ ፍርድ ቤት ለመዳኘት ፍቃደኛ አይደለሁም እያሉ የተሰጠው ውሳኔ ሕገ መንግሥታዊነት ሲሆን 2ኛው የልጅ ሞግዚትነት ስልጣንን ለመወሰን በፍርድ ቤቶች በቀደምትነት ሊታይ የሚገባው ነጥብ ምን መሆን አለበት የሚለው ነው።

የመጀመሪያውን ነጥብ በተመለከተ በኢ.ፌ.ዴ.ሪ ሕገ መንግሥት አንቀጽ 34(5) መሠረት የግልና የቤተሰብ ሕግ በተከራካሪዎች ፈቃድ በሃይማኖታዊ ወይም በባህላዊ ሕጎች መሠረት መዳኘትን አይከለክልም። በዚህ ድንጋጌ መሠረት የሃይማኖት ወይም የባህል ተቋማት የዳኝነት ስልጣን በተከራካሪ ወገኖች ፈቃድ ላይ የተመሠረተ ነው። የተከራካሪ ወገኖች ፈቃድ ከሌለ የዳኝነት ስልጣን አይኖረውም።

ሕገ መንግሥቱን ተከትሎ የፌዴራል የሸሪዓ ፍርድ ቤቶችን ለማጠናከር በወጣው አዋጅ ቁጥር 188/92 አንቀጽ 4(2) በተመሳሳይ ሁኔታ በሕገ መንግሥቱ አንቀጽ 34(5) በተገለጸው መሠረት ፍርድ ቤቶች የዳኝነት ስልጣን የሚኖራቸው ተከራካሪ ወገኖች በእስልምና ኃይማኖት ሥርዓት ለመዳኘት ግልጽ በሆነ መንገድ ፍቃዳቸው ከሰጡ ነው።

የኃይማኖት ፍርድ ቤቶች የዳኝነት ሥልጣንን ከመተግበራቸው በፊት ባለጉዳዮች በፍርድ ቤቱ እና በሕጉ ለመዳኘት ፈቃደኛ መሆናቸውን ማረጋገጥ እንዳለባቸው በግልጽ ሰፍሯል። ከዚህ አንፃር የፌዴሬሽን ምክር ቤት በወይዘሮ ከድጃ በሽር ጉዳይ ተመሳሳይ ውሳኔ ሰጥቷል። በዚሁ መሠረት አመልካች (የሕፃኗ እናት) ለቀረበባቸው ክስ መልስ ሲሰጡ ወደ ክርስትና እምነት የተመለሱ መሆኑን በመጥቀስ በሸሪዓ ፍርድ ቤት ለመዳኘት ፈቃደኛ አለመሆናቸውን ገልፀዋል። ፍርድ ቤቱም ይህንኑ መቃወሚያ መሰረት በማድረግ ሕገ መንግሥቱ በሚፈቅደው መሠረት መወሰን ሲገባቸው ከሕገ መንግሥቱ ድንጋጌ ውጪ በአመልካች ጉዳይ ላይ በሃይማኖት ፍርድ ቤት ውሳኔ መስጠታቸው ኢ-ሕገ መንግሥታዊ ነው።

ሁለተኛውን ነጥብ በሚመለከት በኢ.ፌ.ዴ.ሪ ሕገ መንግሥት አንቀጽ 36(2) እንደተደነገገው ሕፃናትን የሚመለከቱ እርምጃዎች በሚወሰዱበት ጊዜ በመንግሠታዊ ወይም በግል የበጎ አድራጎት ተቋሞች፣ በፍርድ ቤቶች፣ በአስተዳደር ባለስልጣኖች ወይም በሕግ አውጪ አካላት የሕፃናት ደህንነት በቀደምትነት መታሰብ አለበት በማለት ይደነግጋል። አመልካችና ተጠሪ መካከል ያለው ክርክር ከሕፃን ሞግዚትነት ጋር የተያያዘ ሲሆን የአሁን ተጠሪ አመልካች የልጅቷን ሞግዚትነት ከአመልካች ለመውሰድ የአመልካችን እምነት መቀየር እንደመከራከሪያ አድርገው አቅርበዋል።

ጉዳዩን የተመለከተው የሸሪዓ መጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት ሆነ የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በሕገ መንግሥቱ አንቀጽ 36(2) መሠረት ከዕድሜዋ አንጻር ለሕፃኗ ትምህርት፣ ጤና፣ እድገት ማን ዘንድ ብታድግ የተሻለ ነው የሚለው በማህበራዊ ሠራተኛ ባለሞያ ተደግፎና ተጣርቶ መወሰን ሲገባው አልተጣራም።

ጉዳዩ በአግባቡ ባለመጣራቱም በሕገ መንግሥቱ አንቀጽ 36 ንዑስ አንቀጽ 1 (ሐ) እና ንዑስ አንቀጽ 2 መሠረት ሕፃናትን የሚመለከቱ እርምጃዎች በሚወሰዱበት ጊዜ በመንግሥታዊ ወይም በግል የበጎ አድራጎት ተቋሞች፣ ፍርድ ቤቶች፣ የአስተዳደር ባለስልጣኖች ወይም በሕግ አውጪ አካላት የሕፃናት መብትን (the best interest of the child) በቀደምትነት ማሰብ አለባቸው የሚለውን መርህ የተከተለ አይደለም። በመሆኑም ፍርድ ቤቶቹ የአመልካችን ሕፃኗን የማሳደግ ስልጣን በመሰረዝ ተጠሪ እንዲያሳድግ በማለት የሰጡት ውሳኔ የሕገ መንግሥቱ አንቀጽ 36 ንዑስ አንቀጽ 1(ሐ) እና ንዑስ አንቀጽ 2ን የሚጥስ ነው።

በብርሃንና ሰላም ማተሚያ ድርጅት ታተመ